ጅማ ዩኒቨርስቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በዳውሮኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ፍተሻ

በቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 10ኛ ክፍል (ተተኳሪነት)

በ

ኪዳኔ ዘለቀ

በአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2015

ጅማ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርስቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በዳውሮኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ፍተሻ

በቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 10ኛ ክፍል (ተተኳሪነት)

በአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ኪዳኔ ዘለቀ

ዋና አማካሪ ዶ/ር ለማ ንጋቱ

ረዳት አማካሪ ዶ/ር ማንያለው አባተ

ሰኔ 2015

ጅማ ኢትዮጵያ

## የአጥኚው ማረጋገጫ

በዳውሮኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ፍተሻ በቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 10ኛ ክፍል (ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርስቲ የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበውን ይህን ጥናታዊ ሥራ ለመሥራት በርካታ የመረጃ ምንጮችን የተጠቀምኩ ሲሆን እነዚህን ምንጮች በአግባቡ በዋቢ ውስጥ ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ሥራ የራሴ ወጥ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም-------------------------------------------------------

ፊርማ-----------------------------------------------------

ቀን-------------------------------------------------------

# ምስጋና

ከሁሉም በፊት ሠላም፣ጤና፣ማስተዋል፣ጥበብና በረከት ሰጥቶ የእድል በር ከፍቶ በሠላም አስጀምሮ በሠላም እንዳጠናቅቅ የረዳኝን ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህም በመቀጠል አስተምሮ ለዚህ ደረጃ ያደረሰኝን የጅማ ዩኒቨርስቲ ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል እጅጉን አመሰግናለሁ፡፡ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከጎኔ ሆነው በመከታተል የተዛቡ ሀሳቦች ተስተካክለውና የአሠራር ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንዲጓዙ በማድረግ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ለረዱኝ ለውድ አማካሪዬ ለዶ/ር ለማ ንጋቱና ለዶ/ር ማንያለው አባተ እጅግ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠልም የትምህርት እድል ሰጥተው የሥራ ጊዜን ከነሙሉ ደመወዝ ፈቅደው በተጨማሪም ያቅማቸውን ያህል ስንቅ እያቀበሉ ለተባበሩኝ ለቶጫ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት፣ ለቶጫ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤትና መረጃን ለመሰብሰብ በተንቀሳቀስኩበት ወቅት ተማሪዎችንና መምህራንን በማስተባበር የማቴሪያል ድጋፍንም በማድረግ ለተባበረኝ ለቶጫ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤትና ለሌሎችም መንግስታዊ ተቋማት ከፍ ያለ ምስጋና አለኝ፡፡

በመቀጠልም የቤተሰብ ኃላፊነት ተሸክማ በሞራልም በኢኮኖሚም ለረዳችኝና አይዞህ እያለች እያበረታታች የጀመርኩትን ትምህርት እስካጠናቅቅ ድረስ ከጎኔ ላልተለየችኝ ለውዷ ባለቤቴ ለመ/ርት ወጋየሁ ታምራት እንዲሁም የልጅነት ጊዜያቸውን ሰውተው ከሁሉም ነገር ተቆጥበው ትምህርቴን እስካጠናቅቅ ድረስ ለታገሡኝ ለውድ ልጆቼ ለዘርዓብሩክ ኪዳኔ፣ለዳግማዊ ኪዳኔ፣ለቤተልሔም ኪዳኔና ለአስፋወሰን ኪዳኔ እጅግ ልባዊ ምስጋና አለኝ፡፡

## አጠቃሎ


የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በዳውሮ ዞን ቶጫ ወረዳ በቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ በዳውሮኛ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህንንም ዓላማ ለማሳካት ጥናቱ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተከትሎ ተከናውኗል፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በመማር ላይ በሚገኙ 335 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን ከነዚህ ተማሪዎች መካከል በእጣ ንሞና (Random Sampling) 100 ተማሪዎች ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡ በእጣ ንሞና ለተመረጡ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅና የጽሑፍ ፈተና በማቅረብ የጥናቱ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የመጠይቁ አስተማማኝነትም በኩዶር ሪቻርድሰን የመጠይቅ አስተማማኝነት መፈተኛ ቀመር ተሰልቶ 0.77 የሆነ የአስተማማኝነት ብቃት ደረጃን ሰጥቷል፡፡ ከተጠኚዎች የተሰበሰበው መረጃ በመጠናዊ የምርምር ዘዴ የተተነተነ ሲሆን በትንተና መሠረት የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ተጠኚ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ መኖሩ ነው፡፡ የተጠኚዎችን አመለካከት ለመለየት በጽሑፍ መጠይቅ መልክ በቀረቡ በአምስቱም የአመለካከት መለኪያዎች አማካይነት የተገኘና 2.95 ሆኖ የተመዘገበው ውጤት በአማርኛ ቋንቋ ላይ የተጠኚዎች አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ አስችሏል፡፡ ይህ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያሳዩት አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ይዛመድ እንደሆን ለማረጋገጥ በክፍል ደረጃቸው በመማር ላይ ከሚገኙበት መማሪያ መጽሐፍ 40 ጥያቄን የያዘ የጽሑፍ ፈተና ተዘጋጅቶ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም 38.65 የሆነ የፈተና አማካይ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ሲጠቃለል ከሁለቱ ተለዋዋጮች የተገኘው ውጤት ማለትም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያስመዘገቡት የአመለካከት አማካይ ውጤት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ተዛምዶ መኖር አለመኖሩን ለማረጋጥ በተዘምዶ ቀመር ስልት/correlation/ ተሰልቶ **0.955** የሆነ ከፍተኛ ጥምረት አሳይቷል፡፡ ይህም ለጥናቱ መሪ ጥያቄ ትርጉም ያለውን ምላሽ ያስገኘ ከመሆኑም ባሻገር አመለካከት የቋንቋ ትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ መኖሩንና ይህም በውጤት ላይ መንፀባረቁን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ሁሉም የትምህርት ባለድርሻ አካላት ችግሩን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጠቃሹ ትምህርት የተማሪዎችን ፍላጎት ባማከለ፣የአካባቢያቸውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበና ችግራቸውን በሚፈታ መልኩ እንዲቀርብ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚጠበቅባቸው የጥናቱ ግኝት ይጠቁማል፡፡ ይህንንም አጥኚው በአስተያየት ገጽ ላይ ለመጠቆም ሞክሯል፡፡


›

Contents


የአጥኚው ማረጋገጫ ............................................................ 1
ምስጋና ............................................................ III
አጠቃሎ ............................................................ IV
የሠንጠረዥ ማውጫ ............................................................ VII
ምዕራፍ አንድ ............................................................ 1
1.መግቢያ ............................................................ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ............................................................ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............................................................ 5
1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ............................................................ 6
1.4 የጥናቱ ዓላማ ............................................................ 6
1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ ............................................................ 6
1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ............................................................ 7
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ............................................................ 7
1.6 የጥናቱ ወሰን ............................................................ 8
1.7 የጥናቱ ውሱንነት ............................................................ 8
1.8 የምህፃረ-ቃላትና ቁልፍ ቃላት ብያኔ ............................................................ 10
ክለሳ ድርሳናት ............................................................ 11
2.1.1 የአመለካከት ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች ............................................................ 11
2.1.2 የአመለካከት ምንነት ............................................................ 11
2.1.3 የአመለካከት ባህርያት ............................................................ 16
2.1.4 የአመለካከትና የቋንቋ ትምህርት ግንኙነት ............................................................ 17
2.1.5 የመማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ በተማሪዎች አመለካከት የሚኖረው ሚና ............................................................ 19
2.1.6 በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ መምህራን የሚኖራቸው ሚና ............................................................ 21
2.1.7 የአመለካከትና የውጤት ዝምድና ............................................................ 23
2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ............................................................ 26
ምዕራፍ ሶስት ............................................................ 30
3.3 የመረጃ ምንጮች /ተጠኚዎች/ ............................................................ 31
3.4 የጥናቱ አካላይ ............................................................ 31
3.4.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ............................................................ 31
3.4.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ............................................................ 31
3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ............................................................ 32
3.5.2 የመጠይቁ ስርጭትና አሞላል ............................................................ 37

የጽሑፍ ፈተና ........................................................................................................37
3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ..........................................................................................38
የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ............................................................................40
4.1 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ የአመለካከት ውጤት ትንተና.................................40
4.1.1 ተማሪዎች በአምስቱም መለኪያዎች ያሳዩት አመለካከት ውጤት ትንተና....................41
4.1.3 ከተማሪዎች የጽሑፍ ፈተና የተገኘ ውጤት ትንተና ....................................................52
ምዕራፍ አምስት ........................................................................................................ 61
5.ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ፣ ግኝትና የመፍትሔ ሀሳቦች.................................................. 61
5.1 ማጠቃለያ .............................................................................................................61
5.3 የጥናቱ ግኝቶች .....................................................................................................64
5.4 የመፍትሄ ሀሳቦች ................................................................................................66
አባሪ 1 ..................................................................................................................... 71
አባሪ 2 ..................................................................................................................... 73
አባሪ 3 ..................................................................................................................... 76
አባሪ 4 ..................................................................................................................... 77
አባሪ 5 ..................................................................................................................... 78

## የሠንጠረዥ ማውጫ


**ይዘት** **ገጽ**

ሠንጠረዥ 1፡ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ለሚጀምርበት ለሚያበቃበት ክፍል ደረጃ ላይ ስላላቸው አመለካከት የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ትንተና---------------------41

ሠንጠረዥ 2 ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስላላቸው ፍላጎት፣ጉጉት፣ ስለተሳትፎውና ስለውጤት የሰጡት ምላሽ ትንተና-------------------------------42

ሠንጠረዥ 3፡ ተማሪዎች በቋንቋ አጠቃቀም ላይ የሰጡት ምላሽ ትንተና ------------------------------------------------------------------45

ሠንጠረዥ 4፡ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀትና አቀራረብ ላይ የሰጡት ምላሽ ትንተና-----------------------------------------------------------------------------46

ሠንጠረዥ 5፡ ተማሪዎች ስለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ የሰጡት ምላሽ ትንተና---47

ሠንጠረዥ 6፡ ተማሪዎች ለተለያዩ የፈተና ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ ትንተና-------------------------------------------------------------------- 52

ሠንጠረዥ 7፡ ለምሳሌያዊ አነጋገሮች የተሰጠ ምላሽ ትንተና---------------------------------53

ሠንጠረዥ 8 ተማሪዎች በትርጉም የማይገናኙትን እንዲለዩ ለቀረበ ፈተና የሰጡት ምላሽ ትንተና-------------------------------------------54

ሠንጠረዥ 9 ተማሪዎች ለፈሊጣዊ አነጋገር ፈተና የሰጡት ምላሽ ትንተና-----------------------------------------------------------------------54

ሠንጠረዥ 10 ከተማሪዎች ለተቃራኒ ፊች የተሰጠ ምላሽ ትንተና---------------------------55

ሠንጠረዥ 11 የእያንዳንዱ ተጠኚ የአመለካከት ውጤትና የፈተና ውጤት-----------------56

# ምዕራፍ አንድ

# 1.መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ጥያቄዎች፣የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ውሱንነቶችና ከዚህ ጥናት አኳያ የቁልፍ ቃላትና ምህፃረ-ቃላት ብያኔዎችን አካቶ ይዟል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ተማሪዎች ባደጉበት ማህበረሰብ ውስጥ አፍ የፈቱበትን ቋንቋ ዘወትር ስለሚጠቀሙና የቋንቋውን ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህልንም ጭምር ለምደው ስለሚያድጉ የሁለተኛ ቋንቋ የአነጋገር ስልትና አጠቃቀምን በቶሎ ላይረዱ ይችላሉ፡፡ይህም ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት ጫና ከመፍጠሩም ባሻገር በሁለተኛ ቋንቋ የተሠሩ ስራዎችን፣ ሳይንሳዊ ግኝቶችን፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶችንና ሌሎች መረጃዎችን ለመጠቀም በሚያደርጉት ጥረት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ከዚህም በመነሳት አጥኚው በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች በቋንቋው ላይ ያላቸው አመለካከት ምን ሊሆን እንደሚችል ተጽእኖው ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል ለመመርመር ተነሳስቷል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት አፋቸውን በዳውሮኛ ቋንቋ የፈቱና የቋንቋውን ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህል ለምደው ያደጉ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ የሚል ሲሆን የተካሄደውም በደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ በዳውሮ ዞን ቶጫ ወረዳ ቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በመማር ላይ በሚገኙ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

ሰዎች የእለት ተእለት ተግባራቸውን ለማከናውንና ያለሙትን ጉዳይ ከግብ ለማድረስ በየትኛውም አቅጣጫ ሲንቀሳቀሱ የየራሳቸው የሆነ አመለካከትን በውስጣቸው ሰንቀው ይጓዛሉ፡፡ ከዚህም ስንነሳ አመለካከት ከሰው ልጆች አእምሮ ውስጥ ፈጽሞ ሊጠፋ የማይችል ፣ እስከ ዘለቄታው አብሮ የሚኖር ፣ የሰውን ልጅ ማንነትና ባህሪይ የሚገልጽ ፣ የሰውን ልጅ ለእድገትም ለውድቀትም ሊዳርግ የሚችልና ነገር ግን ከአካባቢያዊ ሁኔታና ከአዋዋል በመነሳት ሊቀየር ወይም ሊሻሻል የሚችል መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡ይህም ማለት አመለካከት በሰው ልጅ አካሄድ ላይ ተጽእኖ ሊያደርስ የሚችልና ራሱም ቢሆን በተጽእኖ ስር የሚገኝ በግልጽም በድብቅም በተለያዩ መንገዶች በሰዎች ላይ ሊንጸባረቅ

የሚችል ነገር ነው፡፡ ተማሪዎችም እንዲህ ያለውን አመለካከት ይዘው ወደ ትምህርት ቤት መቅረባቸው አይቀረው ጉዳይ ከመሆኑም ባሻገር በሚማሩበት ትምህርት ላይም ይኸው አመለካከትን በግልጽ ሊያንጸባርቁ ይችላሉ፡፡ ደግሞም አመለካከትና የቋንቋ ትምህርት የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት መልካም አተያይ ካላቸው በትምህርቱ የተሻለ ውጤት ያስመዘግባሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ መጥፎ አተያይ ካላቸው በዚያ የትምህርት ዓይነት ዝቅተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ይሆናል፡፡ በዚህም ብቻ ሳያበቃ በትምህርቱ ላይ ካላቸው አመለካከት አኳያ ደካማ ውጤት ካስመዘገቡ ትምህረቱን የሚያስተምሩ መምህራንን ጭምር እስከ መጥላት እንደሚደርሱም ይገልጻሉ (Aggarwal 1989፣ Skinner1985)

አንድ ተማሪ በሚማረው የቋንቋ ትምህርትና በቋንቋውም ላይ ቀና አመለካከት፣ እንዲሁም የመማር ፍላጎት እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ (Tigeman፣2009) Berumfit (2010)፤ እና Dubin(2009) "በቋንቋው ትምህርትና ልምምድ ውስጥ ወሳኝ ነገሮች የመማር ፍላጎትና አወንታዊ አመለካት ናቸው" ይላሉ፡፡ አንድ የቋንቋ ተማሪ አመለካከቱ አሉታዊ ከሆነ ቋንቋውን ከልብ አይማርም እንዲያውም ከራሱ አለመማር አልፎ ለሌሎች ወደው ለሚማሩትም ተማሪዎች እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ አወንታዊ አለመለካከት ያለው ተማሪ በንቃት ይማራል፤ ጥሩ ውጤትም ያስመዘግባል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ ተማሪዎች ሁሉ ስለሚማሩት ቋንቋና በቋንቋው ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ የቋንቋ መምህራንና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች የተማሪዎችን አመለካከት አሉታዊ ሊያደርጉ የሚችሉት ነገሮች አጥንተው የመፍትሄ ሀሳብን ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ይህንን በተመለከተ ከላይ የጠቀስናቸው ምሁራን፣ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለማዘጋጀትና ሌሎች ትምህርታዊ ግብዓቶችን ለማደራጀት በቅድሚያ ተማሪዎችና ሌሎች የሚመለከታቸው ሁሉ አመለካከታቸው መጠናት እንዳለበት ያስረዳሉ (Fergusons፣2010)፡፡ ይሁንና የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት የተማሪዎች ፍላጎትና አመለካከት ሳይጠና መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻህፍት እስካሁን ድረስ ሲዘጋጁ ቆይተዋል በማለት የፋርጉሰንን ሀሳብ በመጥቀስ ኢዮብ ፀጋዬ (2010) ለኤም ኤ ዲግሪ መመረቂያ ባዘጋጀው ጽሑፍ አቅርቧል፡፡ ይህ ደግሞ የቋንቋው ትምህርት የሚፈለገውን አላማ እንዳይመታ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ ለምን ቢባል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት በርካታ በሆኑና ይኸው ቋንቋ የፈጠረባቸውን

ችግሮች እየተጋፈጡ ትምህርታቸውን ለመከታተል ይገደዳሉ፡፡ለምሳሌ ስነልሳናዊ ጫና፣ ባህላዊ ጫና፣ ስነትምህርታዊ ጫና.. ወዘተ፡፡ ይህንን አስመልክቶ Mount Ford and Makey (2009)፣ "ትክክለኛ የቋንቋ ኮርስ ለማዘጋጀት በሙሉ የሚመለከታቸውን ሰዎች በግልጽ ማነጋገር ተገቢ ነው ይህ ካልሆነ ግን ውጤቱ ከንቱ ነው" ሲሉ ይናገራሉ፡፡ እንደገና Ferguson (2010፣ 5) “ብዙ የትምህርት መርሐ-ግብሮች የሚከሽፉት የተመሰረቱለትን ህዝብ አመለካከት ግምት ውስጥ ስለማያስገቡ ነው” በማለት ሀሳባቸውን ይገልፃሉ፡፡ አክለውም "በኢትዮጵያ የአመለካከት ጥናት ትኩረት እንዳልተደረገለትና የመርሐ ትምህርቱ አዘገጃጀትም በበቂ ሁኔታ ጥናት ላይ ያልተመሰረተ መሆኑ ግልጽ ነው” በማለት ያቀረቡትም ሀሳባቸውን የሚደግፍ ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው በአገራችን የአመለካከት ጥናት ከትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅት አስቀድሞ አለመደረጉ በዋናነት ትልቅ ክፍተት ሲሆን የትምህርት መማሪያዎች በስራ ላይ ከዋሉ በኋላም ስለመሳሪያዎቹ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ለሚሰነዘሩ አስተያየቶችና ተማሪዎችም በቀረበላቸው የትምህርት መማሪያ ላይ ያላቸውን አመለካከት አጥንቶ ማሻሻያዎችን ለማቅረብ አለመሞከሩ ደግሞ ሁለተኛው ክፍተት ነው፡፡ በዚህ ክፍተት ውስጥ ሆነው ነው እነዚህ ተጠኚ ተማሪዎች አፍ ከፈቱበት ቋንቋ ውጭ የሆነውን ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ላይ የሚገኙት፡፡ ሌላው ማስተዋል ያለብን ጉዳይ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲማሩና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን ሲማሩ የአቀባበል ደረጃቸው ላይ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ Spolsky (2014) የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል፡፡ "የአፍ መፍቻ ቋንቋን በተመለከተ ማንኛውም ጤነኛ ሰው ቢያንስ እስከ መግባባት ደረጃ ድረስ ችሎታ ይኖረዋል፡፡ የሁለተኛ ቋንቋን በተመለከተ ግን ቋንቋውን ከማይችሉ እስከ ከፍተኛ ችሎታ ካላቸው ድረስ በርካታ ልዩነቶች ይስተዋላሉ፡፡ በነዚህ የቋንቋ ትምህርት አቀባበል ልዩነቶች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ነገሮች የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ፣ ዕድሜ፣ አጠቃላይ ዕውቀትና አመለካከት ናቸው" ይላሉ፡፡ በስፖሊስኪ አገላለጽ በቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ ተጽዕኖ ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ አመለካከት መሆኑን እንረዳለን፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Chasten (2012) “ተማሪዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በሚመጡበት ጊዜ ከሚኖሩበት አካባቢ በተለያዩ አመለካከቶች ራሳቸውን ሞልተው ይመጣሉ፡፡ ከነዚህ አመለካከት ጥቂቶች ለጥሩ ውጤት የሚያግዙ ሲሆኑ ጥቂቶቹ

አመለካከቶች ደግሞ ትምህርቱን የሚያዳክሙ ናቸው" ይላሉ፡፡ በሌላም በኩል Chasten (2014) በሁለተኛው ቋንቋ ላይ መሆን ስላለበት አካሄድ የሚከተለውን ጽፈዋል፡፡

"ተማሪዎች ስለ ቋንቋው፣ ስለ ቋንቋው ተናጋሪዎች አዎንታዊ፣ አሉታዊ ወይም ድብልቅ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጡ ከሆነ የመማር ፍላጎታቸውም ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ቋንቋውን ማወቅ ለወደፊቱ ውጤታማ የሚያደርጋቸው መሆኑን ካመኑ ጊዜያቸውን ሰውተው ተግባቦታዊ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤አመለካከታቸውም የበለጠ ቀናና ከፍ ያለ ይሆናል" ይላሉ፡፡ ከዚህ አገላለጽ የምንረዳው ተማሪው በቋንቋ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ካለ ለቋንቋና ቋንቋው ለሚወክለው ባህል አድናቆት ይኖራቸዋል፡፡ ደግሞም ቋንቋውን ለመማር በከፍተኛ ንቃት የሚነሳሱ ይሆናል፡፡ ከሁሉም በላይ ተማሪው ለቋንቋው ትምህርት በጣም የሚጓጓ ይሆናል፡፡ በቋንቋ ላይ የሚታይ ቡድናዊና ግላዊ አዎንታዊ አመለካከት በቋንቋው ትምህርት ከፍተኛ ውጤት እንዲገኝ ያደርጋል፡፡ ይህንን ሀሳብ Spolsky (2013) ሲያጠናክር "ተማሪው ለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች አዎንታዊ አመለካከት ካለው ለቋንቋውም ትምህርት አዎንታዊ ውጤት ይኖረዋል" ይላል፡፡ በሌላም በኩል ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት የሚያገኙት ውጤት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ምክንያቱም ጥሩ ውጤት አዎንታዊ ተጽዕኖ ሲኖረው ዝቅተኛ ውጤት አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡

ስለዚህ ይህን ምክንያት መነሻ በማድረግ ይህ ጥናት ለወደፊቱ ያገለገል ዘንድ የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎትና አመለካከት በማጥናት ይህም አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል ፈትሾ በማየት ግኝቱን ለሚመለከታቸው አካላት ለማቅረብ ያለመ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት አፋቸውን በዳውሮኛ ቋንቋ የፈቱ የቋንቋውን አነጋገር ስልትና የቋንቋውን ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህል ለምደው ያደጉ በብሄረሰቡ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? ይህ አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶስ ምን ይመስላል? የሚለውን መመርመር ነው፡፡ ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ ከላይ ለተጠቀሱ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸው እንደመሆኑ መጠን እንዲሁም የራሱ የሆነ የአነጋገር ስልትና ባህላዊ የአፈታት ትርጉም ያለው በመሆኑ እነዚህ ተማሪዎች በዚህ ቋንቋ በሚማሩበት ወቅት ብዙ ስነልሳናዊ ጫና ፣ ባህላዊ ጫናና ስነትምህርታዊ ጫናዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ይህ ጥናትም ከላይ የተጠቀሱ ችግሮችን በመፈተሽ ለችግሮቹ የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ይቻል ዘንድ ተማሪዎች ስለአማርኛ

ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል በጥናት ማረጋገጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ተጠቃሹ ቋንቋ ባሁኑ ወቅት የፌደራል መንግስትና የደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መንግስት የሥራ ቋንቋ በመሆን እያገለገለ የሚገኝና ይህ ጥናት በተካሄደበት ክልልም ከሶስተኛ ክፍል እስከ አስረኛ ክፍል ድረስ  እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ሆኖ እየተሰጠ የሚገኝ ቋንቋ ነው፡፡ከዚህም ባሻገር በዚህ ቋንቋ በበርካታ ምሁራን የተሠሩና የተጠኑ እጅግ አስደማሚ የሆኑ የአእምሮ ሀብቶች  ስላሉ በጥናቱ ግኝት መሠረት መፍትሄ በማበጀት ተማሪዎች የእውቀቱ ተጠቃሚዎችና ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል፡፡

### 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

***የመጀመሪያው ምክንያት*** ተማሪዎች ባደጉበት ማህበረሰብ ውስጥ አፍ የፈቱበትን   ቋንቋ ዘወትር ስለሚጠቀሙና የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህልንም ጭምር ለምደው ስለሚያድጉ የሁለተኛ ቋንቋ የአነጋገር ስልትና  አጠቃቀምን በቶሎ ላይረዱ ስለሚችሉ በዚህ ምክንያት በሁለተኛ ቋንቋ ላይ ያላቸው የአጠቃቀም ብቃት እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ላይሆንላቸው ይችላል፡፡ ይህ በሁለተኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት በቋንቋው የተሠሩ ስራዎችን፣ እውቀቶችንና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶችንና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ተማሪው በተገቢው ለመረዳት የሚያደርገው ጥረት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ከዚህም በመነሳት አጥኚው በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች በቋንቋው ላይ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ተነሳስቷል፡፡

***ሁለተኛው ምክንያት*** ደግሞ አጥኚው ከአሁን ቀደም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ በሚል ርዕስ ዙሪያ የተሠሩ ጥናቶችን ለመዳሰስ ባደረገው ሙከራ ወንድወሰን በየነ (1989) ሀዲይኛ አፈ-ፈት በሆኑ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ፣ አበበ ሺፈራው(1990) አዲስ አበባ ሰበታ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኦሮምኛ አፈ-ፈት በሆኑ ተማሪዎች ላይ የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች እንደሠሩ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ በዳውሮኛ ቋንቋ አፈ-ፈት በሆኑ ተማሪዎች ላይ ምንም አይነት የተካሄደ ጥናት ባለማግኘቱ በዚህ ዙሪያ  ጥናትና ምርምር በማድረግ ተጠቃሽ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸው  አመለካከት

ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ማወቁ ለተማሪዎቹ ጠቀሜታው የጎላ ሊሆን እንደሚችል በመረዳት ሁኔታው ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ተነሳስቷል፡፡

**ሶስተኛው ምክንያት** አጥኚው ይህ ጥናት በተካሄደበት የአማርኛ ቋንቋ መምህር ስለሆነ በተጠቃሹ ቋንቋ የተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆሉን ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም ለውጤቱ ማሽቆልቆል ምክንያቱ ተማሪው በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለው አመለካከት እንደሆነ በጥናት ለማረጋገጥ ተነሳስቷል፡፡

የጥናቱ ትኩረት በዳውሮኛ ቋንቋ አፌ-ፈት የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል መፈተሽ ስለሆነ አጥኚው ለጥናትና ምርምር ሥራው በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡ ምክንያቶችን ዓላማው አድርጎ ተነስቷል፡፡

### 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

የዚህ ጥናት መሪ ጥያቄዎች ከዚህ ቀጥለው የቀረቡ ናቸው፡፡

1- በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ ይኖረው ይሆን?

2- አመለካከት የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት ውጤት የመተንበይ ድርሻ ይኖረው ይሆን?

3- የትምህርቱ አቀራረብና የማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች ለትምህርቱ ባላቸው አመለካት ላይ ተጽእኖ አሳድሮ ይሆን?

የሚለውን የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች /Basic Research Questions/ መሠረት አድርጎ ጥናትና ምርምሩ ተካሂዷል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዳውሮኛ አፍ-ፈት የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን አጠቃላይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ዝርዝር ዓላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

- በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ መኖሩን መፈተሽ፣
- አመለካከት የተማሪዎችን  የቋንቋ ትምህርት ውጤት የመተንበይ ድርሻ መኖሩን መፈተሽ፡፡
- የትምህርቱ አቀራረብና የማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች ለትምህርቱ ባላቸው አመለካከት ላይ ተጽእኖ አሳድሮ እንደሆን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

### 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

በትምህርትነት እንዲቀርብ በተፈለገው ቋንቋ ላይ የተማሪዎች አመለካከት ቀና እንዲሆንና ወደታለመው ግብ ደርሶ በተማሪዎች አእምሮ የሚጠበቀውን የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ በቀጥታ የተማሪው የራሱ አተያይ አወንታዊ መሆን ትልቅ ድርሻ አለው፡፡  በመሆኑም ከዚህ ጥናት በሚገኘው ውጤት በዋናነት ተጠቃሚ የሚሆኑት፡-

1. ተማሪዎች፡- ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸውን ፍላጎትና አመለካከት ለሚመለከተው ክፍል በማሳወቅ ቀጣይ ለሚማሩ ተማሪዎች በፍላጎታቸው መጠን እንዲቀርብላቸው በማድረግ፣
2. መምህራን፡- የተማሪዎቻቸው አመለካከት በቋንቋ ትምህርት ላይ ምን እንደሚመስል ለይተው በማወቅና በዚያው ልክ የትምህርት አሰጣጥ ስልት ቀይሰው በማቅረብ ተማሪዎቻቸው በታላሚው ቋንቋ ትምህርት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችሉ የሚያደርግ መረጃ ይሰጣቸዋል፣
3. የትምህርት መሳሪያ ዝግጅት ክፍልም በታላሚው ቋንቋ ዙሪያ ያለውን የተማሪዎች ፍላጎትና አመለካከት በማሰስ የታለመውን ግብ ለመምታት በሚያስችል መልኩ የትምህርት መሳሪዎች ለማዘጋጀት መረጃ ይሰጣል፡፡
4. በዚህ ርእስ ዙሪያ ወደፊት ጥናትና ምርምር ማድረግ የሚፈልጉ አጥኚዎች   እንደመነሻ ሆኖ በማገልገል ረገድ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

ጥናቱ መሠረት ያደረገው በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱና የቋንቋውን የአነጋገር ስልት/ንበት/ ለምደው ያደጉ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል በመፈተሸና ግኝቱን መሠረት በማድረግ የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም ላይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ይህ ጥናት ለመምህራን፣የማስተማሪያ ቁሳቁስ ለሚያዘጋጁ ክፍሎች እንዲሁም በዳውሮኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ስላለው ተዛምዶ ሠፊ ጥናት ለማካሄድ ለሚፈልጉ አካላት ከላይ የተገለጹትን ጠቀሜታዎች በማስገኘት ረገድ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በሌላ በኩል የአማርኛ ቋንቋ በአገር ደረጃ ሠፊ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ በመሆኑ በተገቢው ማጥናት ቀደም ሲል በአማርኛ ቋንቋ የተሠሩና አሁንም በመሰራት ላይ የሚገኙ በርካታ የእውቀት መስኮችን ከማስገብየት አኳያም ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

አንድ ጥናት በስፋት ተጠንቶ የተነደፈውን ዓላማ ከግብ በማድረስ ተግባር ላይ እንዲውልና ጥናቱም ችግር ፈቺ እንዲሆን በተገቢው ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ አጥኚ ከጥናቱ ዓላማ አኳያ እቅዱን ከግብ ለማድረስ ለጥናታዊ ምርምር ስራ የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ በጀትን መጥኖ ሥራ ላይ ለማዋል፣ ጊዜውን በተገቢ ተጠቅሞ ጥናቱን ሳይጓተት ለማጠናቀቅ ይችል ዘንድ የጥናቱን ወሰን መገደብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ይህ ጥናት ትኩረቱን ያሳረፈው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በዳውሮ ዞን ቶጫ ወረዳ ቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱና የቋንቋውን አነጋገር ስልትና ባህል ለምደው ያደጉ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውሱንነት

በምርምር ስነዘዴ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ አብዛኞቹ ፀሐፍት እንደሚገልጹት ይብዛም ይነስ ደረጃው ቢለያይም ማንኛውም ምርምራዊ ተግባር የራሱ የሆኑ ውስንነቶች ወይም እጥረቶች ሊኖሩበት እንደሚችሉ ይጠቁማሉ ፡፡ ስለዚህ የአጥኚው የመጀመሪያ ተግባር እነዚህን ውስንነቶች አስቀድሞ በመለየት መረዳት ይሆናል፡፡ ችግሮቹም ሊወገዱ የሚችሉ ከሆኑ ለማስወገድ መሞከርና ማስወገድ የማይችላቸው ከሆኑ በጥናቱ ላይ ሊፈጥሩ

የሚችሉትን ማንኛውንም አሉታዊ ተጽእኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ጥንቃቄ የተሞላባቸው መፍትሔዎችን አስቀድሞ በመፈለግ ምላሽ መስጠት ይሆናል፡፡ይሁንና ከላይ በተቀመጠው ልክ በአንድ ጥናታዊ ስራ ላይ እነዚህን ሁሉ ሂደቶች አልፈው ሊከሰቱ የሚችሉ ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ ውስን ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ስለሚገመት በዚህን ወቅት የአጥኚው ቀጣይ ተግባር መሆን ያለበት  እነዚህን ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ የጥናቱን ውስንነቶች በጥናቱ ውስጥ አካቶ በማቅረብ አንድም የጥናቱ ግኝቶች ከእነዚህ ውስንነቶች ጋር ተገናዝበው እንዲታዩ ማድረግና በቀጣይም ለሚከናወኑ ተዛማጅ ወይም አዲስ ጥናታዊ ስራዎች ትምህርት ይሆን ዘንድ እጥረቶቹን አስቀድመው በመረዳት መፍትሔ እና የተሻለ መደምደሚያ ላይ መድረስ ይችሉ ዘንድ በግብአትነት እንዲያውሏቸው መጠቆም ይሆናል ዳዊት ፍሬሕይወት፡፡ (2008) አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፡ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ከቀረበው ጽሑፍ የተወሰደ፡፡

በመሆኑም ለዚህ ጥናትና ምርምር  ስራ በተደረገው የመረጃ አሰባሰብ ወቅት አጥኚውን ያጋጠሙ ውስንነቶች ከዚህ ቀጥለው በዝርዝር የቀረቡ ናቸው፡፡

- አንደኛው ጥናትና ምርምሩ የተካሄደበት ቦታ ከዩኒቨርስቲው በ220 ኪሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ስለሆነ ይህም መረጃን ለመሰብሰብ በተደረገው ምልልስ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል፡፡

- ሁለተኛው ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት 10ኛ ክፍል በቁጥር ስድስት ሴክሽን ስለሆነ ከስድስቱም ክፍል በዕጣ ንሞና የተመለመሉ ተጠኚ ተማሪዎች ከመደበኛ የትምህርት ሰዓት ውጭ በመምጣት የጽሑፍ መጠይቅንም ሆነ ፈተናውን ስለሚሠሩ የጊዜ እጥረት ችግር አጋጥሟል፡፡

ምንም እንኳ እነዚህ የተጠቀሱ ውስንነቶች ቢኖሩም አጥኚው የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለችግሩ መፍትሄ በማፈላለግ ለምርምር ስራ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ ዓላማን ከግብ ለማድረስ ችሏል፡፡

### 1.8 የምህፃረ-ቃላትና ቁልፍ ቃላት ብያኔ

ቀጥሎ ለቀረቡት የምህፃረ-ቃላትና ቁልፍ ቃላት ብያኔ የተሰጠው ከዚህ ጥናት አኳያ ነው፡፡

ደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ → ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት

ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ →ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች ክልላዊ መንግስት

አመለካከት →አንድ ሰው ስለአንድ ነገር የሚኖረው ቀረቤታ፣ውዴታ፣ጥላቻ፣ግምት አተያይ፣ ቀና ወይም ቀና ያልሆነ ውስጣዊ አስተሳሰብ (Gagne፣1976) (Cronbach ፣1954)

አዎንታዊ አመለካከት → አንድ ሰው ስለአንድ ነገር ያለው የመውደድ፣ የመደገፍ፣ የመቀበል፣የመልካም አተያይ...ወዘተ ዝንባሌ ነው፡፡Morgan (1986)

አሉታዊ አመለካከት →አንድ ነገር በመጥፎ አተያይ ማየት፣የመቃወም፣ የመጥላት፣ የመንቀፍ... ወዘተ ዝንባሌ ነው፡፡(Cronbach፣1954)

ታላሚው ቋንቋ →ተማሪው በትምህርትነት እንዲማረው ወይም እንዲያውቀው የተፈለገ ቋንቋ/ ከዚህ ጥናት አኳያ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ውጭ ሌላ ሁለተኛ ቋንቋ/

## ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 የንድፈ ሀሳቦች ፍሰት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ለመቅረጽና የጥናቱን አቅጣጫ ለማሳየት የሚያስችሉ ወሳኝ የሆኑ ንድፈ ሀሳቦች ሠፍረዋል፡፡ እነዚህም የአመለካከት መሠረተ ሀሳብ ፣ የአመለካከት ምንነት፣የአመለካከት ባህሪያት፣አመለካከትና የቋንቋ ትምህርት ግንኙነት፣ የመማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ በተማሪው አመለካከት ላይ የሚኖረው ሚና፣ በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ መ/ራን የሚኖራቸው ሚና፣ አመለካከትና የውጤት ዝምድናና የአመለካከት ተጽእኖዎች መነሻቸው ምን እንደሆነ በቅደም ተከተል አጠር ተደርጎ ቀርቧል፡፡

#### 2.1.1 የአመለካከት ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች

ከ1950 እ.ኤ.አ ጀምሮ የሰውን አእምሮ፣አስተሳሰብና አመለካከት ለማጥናት በርካታ የስነልቦና ምሁራን ጥናትና ምርምር ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ Cronbach (1954) Gardner(1958), Skinner (1985), Morgan(1986) ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን የአመለካከት ምንድነው? አመለካከት እንዴት ይመሠረታል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ጥናቶችን አካሂደዋል፡፡

#### 2.1.2 የአመለካከት ምንነት

አመለካከት ለአንድ ነገር ያለን ጥሩ ወይም መጥፎ ዝንባሌ ነው፡፡አመለካከት እንዲህ ነው ብሎ ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠትም ያስቸግራል፡፡ የአመለካከት ጽንሰ ሀሳብ የሚመነጨውም በግለሰብ ጠባይ ውስጥ ከሚታይ ስርዓት መሆኑንና የአንድ ግለሰብ የአመለካከት ጥራት የሚፈረጀውም በዓይን ከሚታይና ከሚሰማው ግለሰቡ ለግምገማ ከሚሰጠው ምላሽ መሆኑን የብሪታኒካው ኢንሳይክሎፒዲያ (1986) ይገልጻል፡፡

Gagne (1976) ሲገልፁ "የሰው ልጆች በአጠቃላይ ለነገሮች ወይም ለክስተቶች የሚኖራቸው በጎ ወይም መጥፎ አስተያየትን አመለካከት ይሉታል፡፡ይህ ማለት አመለካከት ለተለያዩ ሰዎች ወይም ሁኔታዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአስተሳሰብ ሁኔታ ነው፡፡ይህን ሀሳብ ለማጠናከር Morgan (1986፣ 382-384) ሲገልፁ፡-

አመለካከት በግለሰቦች ገለፃ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ለአንድ ነገር የሚሰጡትን ግምገማ የሚወክል ነው" ይላሉ፡፡ በመቀጠምልም "ማንኛውም ግምገማ ወይም ስሜት የሚቀሰቅስ ነገር ለአንድ ሁኔታ ወይም ነገር አመለካከት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዘው ለአንድ ነገር የሚኖረን ግምት የመውደድ የመጥላት፣ የመደገፍ የመንቀፍ፣ የመስማማት ያለመስማማት፣ አዎንታዊና አሉታዊ በሆኑ ምላሾች ይገለፃሉ"ሲሉም ያብራራሉ፡፡እንግዲህ ከዚህ በላይ በጥቅስ ውስጥ የቀረበውን ሀሳብ ስንመረምር አመለካከት የሰዎችን ውስጣዊ ፍላጎትና ጥልቅ ስሜቶች ሁሉ የሚገለጽበት መሆኑን እንረዳለን፡፡

የስነልቦና ምሁራን አመለካከትን ሲገልጹ፣ "አመለካከት አንድን ነገር መፈለግ ወይም አለመፈለግ፣ መውደድና መጥላት፣ መቀበልና አለመቀበል ማለት ነው ፡፡ ነገር ግን አመለካከት ከዚህ ሰፋ ያለ ትርጉም እንዳለው Cronbach (1954) ይገልጻሉ፡፡እንደሳቸው አገላለጽ አመለካከት ማለት ራስን ከአንድ ነገር ወይም ሀሳብ ጋር አዛምዶ መመልከትና ነገሩን መቀበል ወይም አለመቀበል ማለት ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች የተወሰኑ ወይም ተጨባጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በማንኛውም አመለካከት ውስጥ መቀበል ወይም አለመቀበል ይኖራል ፡፡“ በማለት ሀሳቡን ያብራራሉ (Cronbach 1954 , 325-326) ፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንገነዘበው አመለካከት ከሰው ልጆች ፍላጎትና አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡አንድን ነገር ስንወድ ወይም ስንጠላ ለዚያ ለምንወደውና ለምንጠላው ነገር አመለካከታችን የራሱ የሆነ ተጽእኖ እንዳለው እንረዳለን ፡፡አመለካከት እንዲሁ በቀላሉ ፍቺው ይህ ነው ብሎ ለመናገር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም በሰው አእምሮ ውስጥ ያለውን ስሜት መግለጫም ነውና አመለካከት ከስነልቦና ባህሪ አንፃርም ሊታይ ይችላል፡፡

Caller Encyclopedia (1975፡203) አመለካከትን እንደሚከተለው ሲያብራራ "አመለካከት ከስነልቦና ጉዳይ ጋር የተያያዘ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ያለው ነገር ነው፡፡አንድ ሰው ለአንድ ነገር የሚሰጠው ምላሽ ከስነ ልቦናዊ ሁኔታ ጋር ይያያዛል፡፡ግንኙነቱ ከስነልቦናዊ ጉዳዮች ጋር ሊሆን ይችላል፡፡ለምሳሌ ለነገሮች ፣ ለሀረጎችና ለአባባሎች የሚኖረውን ግንዛቤ ...ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ስለሆነም የተለየ ሥራ ወይም ስለ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ስለ ተባበሩት መንግስታት የራሳችን የሆነ አመለካከት ይኖረናል፡፡አንድን ነገር መውደድ ወይም መጥላት፣ መቀበል ወይም አለመቀበላችንን ለመግለጽ ስንፈልግ

ለዚያ ጉዳይ ያለን አመለካከት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል" በማለት ይገልጻል፡፡

ከዚህ የምንረዳው አመለካከት ሰፊ ሀሳብን የሚገልጽ ጽንሰ ሐሳብ ነው፡፡ስለዚህ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ምን ዓይነት አመለካት አላቸው የሚለውን ለማወቅ ከአንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከት የለብንም፡፡ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ከስነ ልሳን ሁኔታ ፣ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አንፃር መመልከት እንዳለብን ነው፡፡ Openihem (1984፡106 ፣ Gardner 1958፡8) "አመለካከት ከሰዎች ውስጣዊ ስሜት፣ ፍላጎትና ምኞት ፣ ግምት ጋር የተያያዘ ስለሆነ በባህሪው ውስብስብ፣ረቂቅና በዓይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ ነገር ነው" ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

ይህንን ሀሳብ (ያለው 2001፣62) ሲያጠናክሩት፡- "አመለካከት ረቂቅ የሆነ በግልጽ በዐይናችን ልናየው፣ በጆሯችን ልንሰማውና በእጃችን ልንዳስሰው የማንችል ነገር ግን መኖሩን የምናውቅና በተለያዩ መንገዶች እንደሚከሰት የምንረዳው ስውር ወይም ድብቅ ነገር ነው፡፡ለምሳሌ መነሳሳት፣ ፈጠራ፣ እውቀት፣ ፍላጎት፣ጭንቀት የመሳሰሉት ወዘተ እንዳሉ እናውቃለን፡፡እነዚህም ነገሮች በባህሪያችን ላይ ተጽእኖ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም በእለት ተእለት ክንዋኔዎች ላይም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ" በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከእነዚህ ምሁራን ገለጻ ስንነሳ አመለካከት በአስተሳሰባችን ፣በማህበራዊ ኑሯችን ፣ በእለት ተእለት ተግባራችን እንዲሁም ከሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት የሚያሳድረው ተጽእኖ ከፍተኛ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

Simith(1971፡82) "አመለካከትን ሲገልጹ ይማሩታል፣ከተማሩት ደግሞ ያስተምሩታልም እንደ ቋንቋ ሁሉ አመለካከትን የሚማሩትና በልምድ የሚያዳብሩት እምነት፣ አተያይም ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመለካከት አብሮን የተፈጠረ ሳይሆን በትምህርትና በልምድ የሚዳብር ነው በቋንቋ ትምህርት ሂደትም ምንም እንኳን ተማሪው በመጀመሪያ ጥሩ አመለካከት ወይም ገለልተኛ የሆነ ግምት ይዞ ቢገባም በትምህርቱም ሆነ ከክፍል ውጭ በሚያጋጥሙት ነገሮች ምክንያት ለቋንቋው ያለው አመለካከት ይለወጣል፡፡ ስለዚህ አመለካከት በሚያጋጥሙን ነገሮች ሁሉ የመለወጥ ባህሪ ሊያሳይ ይችላል፣ ሊበላሽም ሆነ ሊስተካከል የሚችል ይሆናል፡፡ ስለሆነም አመለካከት ሁኔታዊና ተለዋዋጭ ነው ማለት ይቻላል" በማለት አስተያየቱን አቅርቧል፡፡ ይህም የሚያመለክተው አመለካከት ተማሪዎች

ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት እንዲነሳሳ ወይም እንዲቀንስ ከፍተኛ ተጽእኖ ሊያደርግ የሚችል መሆኑን ነው፡፡

ይህንንም ሀሳብ በማጠናከር Cronbach (1954:310) ሲገልፁ "አመለካከት ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓላማ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ለምሳሌ፡- የቋንቋ ትምህርት ከሰዎች ጋር ለመግባባት ፣ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር የሚኖረንን አመለካከት ለመለወጥ ይረዳል፡፡ አመለካከት በተለይ በማህበራዊ ሳይንስ ላይ ያተኩራል፡፡ አመለካከት በትምህርት ሊስተካከልና ሊሻሻልም ይችላል፡፡ከዚህ ምክረ ሀሳብ አመለካከት ሊለወጥ፣ ሊሻሻል እንደሚችልና በተለይ ለማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን እንረዳለን፡፡ተማሪዎች አንድን ቋንቋ የመውደድ ወይም የመጥላት ሁኔታ ካለምክንያት እንዲሁ ተነስተው የሚፈጥሩት ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያትነት የሚጠቀሱ በርካታ ተውላጦች አሉ፡፡ እነዚህ ተውላጦች በመባል የሚታወቁት ቋንቋውን እንደሚማረው ተማሪ ፣ እንደየቋንቋው ትምህርት ውስብስብነት፣ ቤተሰባዊ ዳራ፣ የተማሪው ስነልቦናዊ ሁኔታ፣ ከፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ የሚመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ" በማለት ገልፀዋል፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች አንድን ቋንቋ ለመውደድ ወይም ለመጥላት የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉ ከፍ ሲል ምሁራኑ ከጠቀሱት ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በላይ የቀረበውን ሀሳብ በመደገፍ Spolsky (1989:15) ቋንቋን ስለመማር አስመልክተው ሲገልፁ "ቋንቋ መማር ማስተማር ተግባር ከማህበራዊ አውድ ውጭ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡በማህበራዊ አውድ ውስጥ ከሚጠቀሱት ተውላጦች መካከል የቋንቋው ባህል፣ ቤተሰብ፣ አካባቢ፣ት/ቤት፣ መንግስት ይገኙባቸዋል"ይላሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በእነዚህ ተውላጦች ውስጥ ሆነው አፋቸውን የፈቱበትን ቋንቋ አነጋገር ስልትና የቋንቋውን ባህል ለምደው ስለሚያድጉ ይኸው ተጽእኖ ሁለተኛ ቋንቋ ላይ ጫና በማሳደር ለቋንቋው ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህም በተጠቀሰው ቋንቋ ከሚያስመዘግቡት ውጤት ጋር ባለው ተዛምዶ ሊገለጽ ይችላል፡፡አመለካከት በትምህርት የሚገኝ በተለያዩ ሰዎች ወይም ሁኔታዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአስተሳሰብ ሁኔታ ነው፡፡ Nunan (1976 ፡ 407) "አመለካከት በቀጣይነት የሚቀሰም በተወሰነ የመነሳሳት ደረጃ ላይ የሚታይ የማሰብ፣ የማድረግ፣ ወይም የውስጣዊ ስሜት ሁኔታ ነው" ይላሉ፡፡ Woduslus (1985፣46) "አመለካከት በትምህርት ይቀሰማል፣

በልምድ ሂደት፣ በቀጥታ ትምህርት ፣ በመምህርና ተማሪ ግንኙነት፣ በልጅና ወላጅ ግንኙነት ወዘተ. ይዳብራል” ይላሉ፡፡ እንግዲህ እነዚህን ሀሳቦች በአጭሩ ስናጠቃልል አመለካከት በአዎንታዊነትም ሆነ በአሉታዊነት ከአካባቢ በትምህርት የሚቀሰም፣ በልምድ ሂደትና በተለያዩ ግንኙነቶች የሚዳብር፣ የተወሰነ ደረጃ ያለው የማሰብና የማድረግ ውስጣዊ ስሜት ነው፡፡ አመለካከትን ከሁኔታዎች አካሄድ በመነሳት ገምተን እንዲህ ሊሆን ይችላል እንላለን እንጂ እውነታው ግን እንዲህ አይደለም፡፡ ሆኖም ከሀሳብ አገላለጽ፣ ከቃላዊ ሪፖርት፣ ከሚንጸባረቅ ጠባይና ከሚታዩ ምልክቶች በመነሳት ሊታወቅ ይችላል፡፡

ከዚህም ባሻገር አመለካከት ከማንነታችን የማይነጠል ወሳኝ ነገር መሆኑን Kiwisky(2014) እንደሚከለተው ይገልፃሉ፡፡ “አመለካከት በአስደናቂ ሁኔታ ሰዎችን  ለመለካት ሁልጊዜ ከኛ ጋር ሆኖ በቋሚነት በጠባያችንና በትምህርታችን ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ የማንኛውም ሰው ህይወት ከአመለካከት ውጭ ሊሆን አይችልም" ሲሉ ያብራራሉ፡፡ በመሆኑም አመለካከትና ሌሎች ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች በትምህርት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ቀላል እንዳልሆነ ከተለያዩ ምሁራን ጥናታዊ ጽሁፎች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በዚህም የሰው ልጅ ከአመለካከቱ የተነሳ አስተዋይ ፣አዋቂ፣ ብልህ፣ ተስማሚ፣ ምቹ፣ቀና…ወዘተ ሊባል እንደሚችልና በተቃራኒው ደግሞ ደካማ፣ግትር፣ ግድየለሽ፣ አላዋቂ ..ወዘተ ሊባል እንደሚችል እንረዳለን፡፡አመለካከት ውስጣዊ

ስሜት ሁኖ ለረጅም ጊዜ በሰዎች ጠባይ ላይ ተጽዕኖ በማድረግ ኃይሉን መግለጽ የሚችል ነገር ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አንድ ሰው ለአንድ ነገር ያለው መነቃቃት ወይም አለመነቃቃት ከአመለካከቱ ጋር የተያያዘ መሆኑን እንረዳለን፡፡ Chasten (2013) “ከፍተኛ ፍላጎት፣ ዝግጅት፣ ተሳትፎና ትምህርት የመቅሰም ብቃት በውስጣዊ የመነቃቃት ባህሪይ ይወሰናሉ” ይላል፡፡

Harmer(1991) "አመለካከት ሰዎች አንድን ተግባር እንዲፈጽሙ የሚያነሳሳ ውስጣዊ ስሜት ነው" በማለት ሲገልፁ ይህንን ፅንሰ ሀሳብ Brown (1987) ሲያጠናክር "አመለካከት በሰው ልጆች ላይ የሚታይ ተፈጥሯዊ የሆነ አንድን ነገር ለመተግበር የሚያስችል ውስጣዊ ፍላጎት ነው" ሲሉ  ያብራራሉ፡፡ይህም የሚያሳየን አመለካከት የተለያዩ ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ አንድ ነገር ለምንና እንዴት እንደሚተገበር የሚያሳይ የባህሪይ ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል ግፊት መሆኑን ነው፡፡

### 2.1.3 የአመለካከት ባህርያት

አመለካከት ሁኔታዊና ተለዋዋጭ እንደሆነ የስነ-ልቦና ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ አመለካከት ስነ-ልቦናዊ ይዘት ያለው፣ ከሰዎች ውስጣዊ ስሜት፣ ፍላጎት፣ እምነት.. ወዘተ ጋር የተያያዘ ስለሆነ በባህሪው ውስብስብ፣ ረቂቅና ድብቅም ነው፡፡ Cronbach (1954:325) ይህንኑ ሲገልፁ "አንዳንድ አመለካከቶች በጣም ስር የሰደዱ በመሆናቸው ለማወቅ በጣም ያስቸግራሉ፡፡ አንዳንድ አመለካከቶች ደግሞ በጣም ድብቅ በመሆናቸው በየጊዜው ከምናያቸው ባህሪያት በመነሳት ለማወቅ ያስቸግራሉ፡፡" ስለሆነም የአመለካከትን ባህሪያት ለማወቅ የሰውን ልጅ አእምሮ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ የሰው ልጅ ምን እንደሚፈልግ፣ ምን እንደሚጠላ፣ ውስጣዊ ስሜቱን ፣እምነቱን ሁሉ መረዳት ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ በጣም ረቂቅ ፣ ውስብስብና በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ከዚህ በላይ ከቀረበው ሀሳብ መራዳት ይቻላል፡፡Pein(2010) አመለካከት ግትርና ቋሚ ሳይሆን እንደሁኔታው ሊሻሻል፣ ሊስተካከልና ሊቀየር የሚችል መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ አንድ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያንፀባርቀው አሉታዊ አመለካከት በልዩ ልዩ የአቀራረብ ስልት ወደ አዎንታዊነት ሊቀየር ይችላል፡፡

እንደ Gardner (1985፡8) "አመለካከት አብዛኛውን ጊዜ ከዳበረ ልምድና ባህርይ ጋር ተያይዞ የሚገኝ በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ ሊገለጽ የሚችል ሌላ ጊዜ ደግሞ በጣም ድብቅ የሆነ ባህርይ ያለው ሆኖ ይስተዋላል፡፡ ይሁን እንጂ በቀጥታ ከጉዳዩ ጋር ሊገናኝ ከሚችል ሁኔታ ጋር አገናኝቶ ወይም እንዲወጣ የሚገፋፋውና የሚያነሳሳው አጋጣሚ ሲገኝ በቃል፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ ወይም በገሃድ ሊታይ በሚችል ድርጊትና የባህርይ ግልጠት ሊታወቅ ይችላል፡፡"ከላይ ከቀረበው የምሁራን ሀሳብ የምንረዳው አመለካከት ከሰው ልጆች ፍላጎትና አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ አንድን ነገር ስንደግፍ ወይም ስንነቅፍ ለምንወደውና ለምንጠላው ነገር አመለካከታችን የራሱ የሆነ ተጽእኖ እንዳለው እንገነዘባለን፡፡ ከዚህም ስንነሳ  አመለካከትን እንዲህ ነው ብለን በቀላሉ ፍቺውን ለመናገር በጣም አስቸጋር ነው፡፡ለምን ቢባል በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ያለውን ስሜት መግለጫ ከመሆኑም ባሻገር  ስነልቦናዊ ይዘት ያለው ከሰው ልጆች ውስጣዊ ስሜትና እምነት ጋር በቀጥታ የተያያዘ በመሆኑ በባህሪው ረቂቅ፣ድብቅና ተለዋዋጭም ነው፡፡

### 2.1.4 የአመለካከትና የቋንቋ ትምህርት ግንኙነት

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ፍላጎትና አመለካከት አስፈላጊ መሆናቸውን በርካታ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ bromFit (2012)፣ Dubin (2013) በቋንቋ ትምህርትና ልምምድ ውስጥ ወሳኝ ነገሮች ፍላጎትና አዎንታዊ አመለካከት መሆናቸውንና በቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ሊያስመዘግቡ እንደሚችሉ ይገልፃሉ፡፡ Spolsky (2013) "በቋንቋ ትምህርት ላይ ዋነኛው ጉዳይ ተማሪው ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች የሚኖረው አመለካከት ነው" ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ጽንሰ ሀሳብ ስንነሳ ለሰው ልጅ ያለው አመለካከትና ሥነልቦናዊ ሁኔታ በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል እንዳልሆነ ከላይ በዝርዝር ከቀረበው የምሁራን ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደ Elay(2009) አገላለጽ ደግሞ ጥሩ የቋንቋ ትምህርት እንዲካሄድ መነቃቃት፣ አጠቃላይ ዕውቀት፣ ውጤት መሻትና የክፍል ተሳትፎ አስፈላጊ ሲሆኑ፣ በክፍል ተሳትፎ ላይ ተጽዕኖ ከሚያደርጉት በርካታ ነጥቦች አንዱ አመለካከት ነው፡፡ በሌላ በኩል ከአመለካከት ጎን ለጎን መነቃቃት ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ በጥሩ ሁኔታ የተነቃቃ ወይም አዎንታዊ አመለካከት ያለው ተማሪ የተሻለ ውጤት ሲኖረው በአሉታዊ ሁኔታ የተነቃቃ ተማሪ ውጤቱ ዝቅተኛና የማይጠቅም ሆኖ ይመዘገባል፡፡

WIlga (2012) የውጭ ቋንቋ ትምህርትን ከማስተዋወቃችን ወይም ከመጀመራችን በፊት ተማሪዎቹ ስለዚህ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት፣ በዚያን ወቅት ቋንቋውን መማር ለምን እንዳስፈለገንና ከቋንቋው ትምህርት የሚያስገኙት ጥቅም በቅድሚያ መታወቅ እንዳለበት ትናገራለች፡፡ ዊልጋ ለውጭ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ሰጥታ ትናገር እንጂ ጽንሰ ሀሳቡ ለሁሉም ቋንቋዎች ይሰራል፡፡

Dubin (2013) “ማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ከመከናወኑ በፊት ማህበረሰቡና ተማሪው ስለ ቋንቋው ያላቸው አመለካከት በጥራትና በጥልቀት መጠናት አለበት” ትላለች፡፡ ከዚህ ጋር በጣም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ Makey and Mount (2012) ጥሩ የቋንቋ ኮርስ ለማዘጋጀት በቅድሚያ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር መደበኛ ግንኙነት ማድረግ ተገቢ መሆኑን ይጠቁሙናል፣ ይህ ካልሆነ ውጤቱ ብላሽ እንደሚሆን ያሰምሩበታል፡፡ ስለዚህ ከማንኛውም የቋንቋ ትምህርት በፊት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ህብረተሰቡና የትምህርት ባለሙያዎች አመለካከታቸው መጠናት አለበት፡፡

ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት የሚያገኙት ውጤት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ጥሩ ውጤት አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸው ጥሩ ውጤት እንዲያገኙና እንዲቀሳቀሱ (motivation) የየራሳቸውን ዘዴ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ማለት ግን ተማሪዎቹ ሁሉ ጥሩ እንዲያመጡ ተብሎ ከደረጃ በታች የሆነ በጣም ቀላል ፈተና ይሰጥ ማለት አይደለም፤ በጣም ቀላል ፈተና መሆኑ ራሱ እንዳይቀሳቀሱና አሉታዊ አመለካት እንዲያድርባቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡ (Harmer 2012፣ Stern 2014፣ Littlewood 2014)፡፡ የተማሪዎችን ውጤት አስመልክቶ ፣ Harmer (2015) "ጥሩ ውጤት ማግኘት አለማግኘት በተማሪው እጅ ቢሆንም መምህሩ በሂደቱና በአፈፃፀሙ ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል" ይላል፡፡

አመለካከትን ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አኳያ ስንመለከት እንደ ትምህርት ውጤት መገለጫ ሆኖም ያገለግላልGardner (1985)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር አመለካከት ከውጤት ጋር ብቻ ሳይሆን ከቋንቋ መማር ሂደት ጋርም ግልጽ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ እንደ ጋርድነር አገላለጽ ቋንቋን ለማወቅ መጣር፣የመማር ዓላማን የማሳካት፣ ምኞትን ከግብ ላይ ድረስ መትጋት ቋንቋ ለመማር የሚያስችሉ የጥሩ አመለካከቶች ቅንጅት ናቸው፡፡ ይህም የሰዎችን ፍላጎት፣ ስሜት፣ ጉጉት የሚያንፀባርቅ ከውስጣዊ ወይም ከውጫዊ ግፊት በመነሳት ቀና አመለካከትን፣አዎንታዊ ምላሽን እና ጥሩ ውጤትን የሚያስገኝ አንድን ድርጊት እንዲፈፀም የሚያበረታታ ሂደት መሆኑን ያመለከታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ግለሰቡ ቋንቋውን ለመማር ካለው ምኞትና ከተግባር ለሚያገኘው እርካታ ሲል የሚያከናዉነው ስራ ወይም የሚያደርገው ጥረት እንደሆነ ይስተዋላል፡፡

በመማር ማስተማሩ ሂደትም በተማሪዎች ላይ የባህርይ ለውጥ እንዲታይ አመለካከት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል Bill (2000)፡፡ እንደ ቢል አገላለጽ የቋንቋ ትምህርትን በአዎንታዊ አመለካከት የሚማር ተማሪ በሚማረው ትምህርት ዙሪያ ግንዛቤን፣ ትውስታንና አዕምሯዊ ዕድገትን ያገኛል፤ ምክንያቱም ውስጣዊ ተነሳሽነት ያለው ተማሪ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ስለሚኖረውና ከፍተኛ ጥረት ስለሚያደርግ ያለመውን ለመፈጸም ድፍረት ይኖረዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ካለመው ግብ ይደርሳል፡፡ ከዚህም ድምዳሜ በመነሳት የቋንቋ ትምህርት ለመማር አመለካከት እንደ አንድ መሳሪያ ተደርጎ የሚወሰድ ለተማሪዎች እጅግ አሰፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ይህ

አስተያየት በህብረተሰቡም ሆነ በመምህራን ዘንድ ተቀባይነት ያለው አመለካከት ነው ፡፡ ፀጋዬ አረጋይ (1996) ፣ Spolsky(1989) እና Nunan (1996) ጠቅሰው "አመለካከት በቋንቋ ተስተምህሮ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀጥተኛ ሳይሆን ተጽእኖ ሊያመጣ ወደሚችል ማነቃቂያ የሚያመራ ነው" በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2.1.5 የመማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ በተማሪዎች አመለካከት የሚኖረው ሚና

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የተማሪን አመለካከት በመቀየር በኩል ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡በመሆኑም መጻህፍት በሚዘጋጁበት ጊዜና ከመዘጋጀታቸውም በፊት የተማሪዎችን አመለካከት ጠንቅቆ ማወቅ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህንን በማስመልከት Mursia (2010) “የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ከማዘጋጀታችን በፊት ተማሪዎቹ ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካት አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት መታወቅ አለበት” ትላለች፡፡ ይህችው ሴት ስለመማሪያ መጻህፍት አመለካከትን የማስቀየር ኃይል አላቸው፡፡ ስለዚህ ጥሩ መጻህፍት በአዎንታዊ መልክ ሲቀሰቅሱ መጥፎዎቹ ደግሞ በአሉታዊነት ይቀሰቅሳሉ ትላለች፡፡ መማሪያ መጻህፍት በአባሪዎች፣ በቃላት ዝርዝርና በስዕላ ስዕል ከታጀቡ የተማሪዎችን ስሜት ወደ አዎንታዊ አመለካከት እንደሚስቡና እንደሚማርኩ Mursia (2013) ትናገራለች፡፡ Canning sworth (2015)

አንድ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ዝርዝርና ኤንዴክስ መያዝ እንደሚገባው ይናገርና “እነዚህም መምህሩና ተማሪዎች የተፈለገውን ነገር ቶሎ ብለው ማግኘት እንዲችሉ ይረዷቸዋል” ይላል፡፡ ስለዚህ አንድ መማሪያ መጽሐፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ የቃላት ዝርዝር፣ ኢንዴክስ፣ ስዕላ ስዕሎችንና አባሪዎችን አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡ መማሪያ መጻህፍት ከውጫዊ መልካቸውና ከቅርጻቸው ጀምረው እስከ ውስጣዊ የአፃፃፍ ስልትና ስዕላዊ ቅንብሮች ድረስ ጥሩ ቅርጽ የያዙና ተማሪዎችን መሳብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ይህን አስመልክቶ Shelden (2012) መማሪያ መጽሀፍ አጠቃላይ ሁኔታው የሚስብ መሆን እንዳለበትና አንድ ደራሲ፣ መማሪያ መጽሀፍ ውጤታማ እንዲሆን ቅርጹ፣ የአፃፃፍ ስልቱና ስዕላዊ ቅቦቹ ሁሉ አስፈላጊ መሆናቸውን ማወቅ ተገቢው መሆኑን ይገልፃል፡፡

በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ የመማሪያ መጻህፍት ተጠቃሚዎች በቀለማት ያሸበረቀና የሚያነቃቃ መጽሀፍ እንደሚፈልጉ ፀሐፊው ይጠቅስና ደራሲያን መጽሀፍ በሚያዘጋጁበት ጊዜ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው ያብራራል፡፡ ነገር ግን በብዙ መንገዶች ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ ጉዳዮች አስፈላጊውን ትኩረት እንደማያገኙና የመጽሀፍ ዋነኛ ባለቤት የሆኑት ተማሪዎችም እንደማይታወሱ ያስረዳል፡፡ በመሰረቱ ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ውጭ የሚዘጋጅ መጽሀፍ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም፡፡

እንዲያውም ተማሪዎች በመጽሀፉም ሆነ በትምህርቱ ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲያሳድሩ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ መሰረታዊ የሆኑ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡ እንደ ሸልደን (2014) አገላለጽ አንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

- በቂ የቋንቋ ዕውቀቶችን የያዘና ተማሪዎችን በደንብ የሚመራ፣

- ለተማሪው ነፃነት ሰጥቶ የሚያሰራ፣

- ከተማሪዎች ፍላጎትና ዝንባሌ አኳያ የተዘጋጀ፣

- ከተማሪዎች የአጭርና የረጅም ጊዜ ዓላማ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ፣

- የቋንቋ ዘርፎችን በሚገባ አመጣጥኖ የሚይዝ፣

- ከጊዜ ጋር የተመጣጠነ፣

- የተማሪዎችን ግላዊ ስሜት የሚጠብቅና የሚማርክ፣

- ቅደም ተከተሉ የተስተካከለ፣

- በምዕራፍና በክፍለ ትምህርት የተከፋፈለ፣

- ለክፍል ውስጥ የትምህርት ሂደት የተመቻቸ፣

- ተማሪዎችን ለውይይትና ለችግር ፈቺነት የሚጋብዝና እንዲሁም የተማሪውን ዕድሜና የክፍል ደረጃ ባማከለ መልኩ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

አንድ የቋንቋ ተማሪ መማሪያ መጽሐፉን በግሉ ማግኘትና እንደ ልቡ መጠቀም መቻል አለበት፡፡ ካለመማሪያ መጽሀፍ የቋንቋ ትምህርት ተፈላጊውን ግብ ሊመታ አይችልምና፡፡ ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ መማያ መጻህፍት ለሁሉም ተማሪዎች በግል መዳረስ ይኖርባቸዋል፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ለሁሉም ተማሪ ቢዳረስ መልካም ውጤት እንደሚኖው Cayload (2014) ሲጽፍ "የመጻህፍትና የሌሎች ትምህርታዊ ቁሳቁሶች ችግር ካለ የትምህርቱ ተቀባይነትና ውጤት ዝቅ ይላል፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ በግሉ መጽሀፍ ካገኘ ግን የትምህርቱ ተቀባይነትና ውጤቱም ከፍ ይላል" በማለት ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተጽዕኖ የማድረግ ኃይል ያላቸው

መሆናቸው ታውቆ በዝግጅት ላይ ትኩረት ሊሰጣቸውና ለያንዳንዱ ተማሪ በግል መዳረስ መቻል ይኖርባቸዋል፡:

### 2.1.6 በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ መምህራን የሚኖራቸው ሚና

በርካታ መምህራን ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲወዱና አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፡፡ ስለሆነም በተለያየ መልክ ይቀስቅሳሉ፣ ይመክራሉ፣ ያበረታታሉ፣ ለማሳወቅ ይጥራሉ፡፡ Woduslus (2012) እንደሚለው "ባዶ ቃላት ወይም ንግግር ብቻውን በተማሪዎቸ ላይ የአመለካከት /የባህሪይ/ ለውጥ አያመጣም፡፡ ተማሪዎች ራሳቸው በትምህርቱ እንቅስቃሴ ተሳትፈው በመምህሩ አቀራረብና በትምህርቱም መሳብ መቻል ይኖርባቸዋል፡፡ መምህር ተማሪው በቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንዲያሳድር ለማድረግ ትልቁ ወሳኝ አካል ነው ቢባል የተጋነነ አይሆንም" በማለት ይገልፃሉ፡፡

Spolsky (1969) Harmer (1990) "ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የቀረበው ተማሪ ትምህርቱን በሙሉ ፍላጎት መከታተል ይችል ዘንድ ሁኔታዎችን ምቹ ከሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት መካከል ከፍተኛ ድርሻ እንዲወስድ የሚጠበቀውና ከተማሪዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው መምህር በመሆኑ የመማር ማስተማሩን ድባብ ለማመቻቸት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል" ሲሉ ያብራራሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው መምህራን ተማሪዎች የቋንቋውን ትምህርት ሲከታተሉ በምን ዓይነት አመለካከት ውስጥ ሆነው እንደሆነ፣በትምህርት ሂደት ውስጥ ተሳትፏቸው ምን እንደሚመስል፣ ለቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብና ለመምህራን እንዲሁም ለማስተማሪያ ስልት ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል፣በቋንቋው ላይ ያላቸው አመለካከትና ቋንቋውን ሲማሩ ያነገቱት ዓላማ ምን እንደሚመስል በማጤን ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የሚስማማ ስልት በመቀየስ በቀና አተያይ ትምህርቱን ማቅረብ እንደሚጠበቅበት ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የትምህርት ሂደቱ አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል፡፡ ስለዚህ መምህራን ተማሪው ደከም ባለበት ቦታ ቆም ብለው በማሰብና የተሻለ ዘዴ በመቀየስ ተማሪውን መርዳት፣ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካት ቀና እንዲሆን  በማድረግ ሙያዊ ግዴታውን የመወጣት ኃላፊነት አለበት ሲሉ Harmer(1990) ይገልፃሉ፡፡

Right (1987፡47) "የክፍል ውስጥ ትምህርት የቡድን ሥራ ነው፡፡ በመማር ማስተማር ክንውን ውስጥ ተማሪው ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆንና ተማሪ ከተማሪ እንዲሁም ተማሪ ከመምህሩ ጋር ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር ፣ ተማሪ ራሱ ከሚሠራው እንዲማር የማድረግ ኃላፊነት የመምህሩ ነው" በማለት ይገልጻሉ፡፡

Spolsky (2012) የመምህራን አመለካከት ለተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ወሳኝ መሆኑን የጠቀሰ ሲሆን አዜብ (2014) "የመምህሩ አመለካከት በወጣቶች ስብዕና ጥሩ ወይም መጥፎ ተጽዕኖ ሊያደርገው ይችላል" በማለት የ(Spolsky)ን ሀሳብ የሚያጠናክር ሀሳብ አቅርባለች፡፡ እንደገና ዳንኤል (2015) "በቂ ዕውቀት ያለውና በደንብ የሚያስተም ዝነኛ መምህር በተማሪዎቹ ተመስጦና ተሳትፎ እንዲሁም ባህርይ ላይ ጥሩ ተጽዕኖ ያደርጋል" ይላል፡፡ Harmer (2015) እና Woduslus (2010) መምህሩ ተማሪዎችን በአቅራረቡ የሚስብና የሚማርክ፣ ስብዕናቸውን የሚጠብቅና የሚንከባከባቸው ከሆነ ተማሪዎች እንደሚወዱትና እንደሚያከብሩት ብሎም በትምህርቱ ላይ አዎንታዊ አመለካትን በማሳደር ከልብ እንደሚማሩ ይገልጹና በሌላ በኩል መምህር ነጭናጫና ተሳዳቢ፣ እንዲሁም ተደባዳ ከሆነ ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲጠሉና አሉታዊ አመለካከት እንዲያድርባቸው እንደሚያደርግ ያስረዳሉ፡፡ ከላይ በተከታታይ ሀሳባቸውን የሰጡት ምሁራን ሁሉ አንድ መምህር በተማሪዎች አመለካከት ላይ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ያመለክታሉ፡፡ ስለዚህ መምህር ሙያውን አፍቃሪና ከልብ የሚሰራ፣ ሀቀኛና ተማሪዎቹን የሚወድ ጥሩ አርአያ መሆን የሚችል ሰው መሆን አለበት፡፡ ይህ ከሆነ በተማሪዎች ላይ አዎንታዊ አመለካትን ሊያሳድር ይችላል፡፡ ይህንን አስመልክቶ Harmer (2013) ለተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት ሲባል አንድ የቋንቋ መምህር ማድረግ የሌለበትንና ማድረግ የሚኖርበትን እንደሚከተለው አስቀምጧል፡፡

- ሙያዊ ስነምግባርን በማክበርና ስብዕናውን በመጠበቅ አርአያ መሆን አለበት፡፡
- የትምህርቱ አቀራረብ ማራኪ እንዲሆን በጣም የሚጥር መሆን አለበት፣
- ተማሪዎችን በእኩል ዓይን የሚመለከት፣ ለችግራቸው መፍትሄ የሚሰጥ፣ ትምህርታቸውን እንዲወዱ የሚመክርና የሚያበረታታ የቅርብ ሰው መሆን አለበት፣
- በኃይለ ቃል የሚናገር፣ ሳይዘጋጅ የሚገባ ፣ በሆነው ባልሆነው የሚቆጣ መሆን የለበትም

- ትምህርቱን አሰልቺ ማድረግ የለበትም፣ /በድግግሞሽ፣ ምቹ ዘዴ ባለመምረጥ/

- ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ መናገር እንዲችሉ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ማስተማር የሚችል መሆን አለበት፡፡

### 2.1.7 የአመለካከትና የውጤት ዝምድና

አመለካከት በተማሪዎች ውጤት ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ እንዳለው የስነ-ልቦና ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ በት/ቤቶች ውስጥ በመምህራንም ሆነ ህብረተሰብ ዘንድ የተለመደ አስተያየት ሲሰነዘር ይደመጣል፡፡አንድ ተማሪ በታላሚው ቋንቋ ላይ ጥሩ አመለካከት ካለው በትምህርቱም ጥሩ ውጤት ያስመዘግባል፣ መጥፎ አመለካከት ካለው ደግሞ ውጤቱ ደካማ ይሆናል የሚል አስተያየት ይሰማል፡፡ Spolsky(1989)፣ Skinner (1985) እና Buglisky (1971) ከዚህ በላይ የቀረበውን ሀሳብ በመደገፍ ሲገልጹ ተማሪዎች ለአንድ ትምህርት ጥሩ አመለካከት ካላቸው ትምህርቱን ለመማር ከፍ ያለ መነቃቃት ያሳያሉ፣ ፍላጎታቸውም ከፍ ይላል፡፡ ለትምህርቱም ጥሩ አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡ ይህንንም ሀሳብ ታደለ(1990፡14) ሲያጠናክር፡- አመለካከት አንድ ሰው ከሚገጥመው ወይም በውስጡ ከሚያልፍበት ነገር ጋር በሚያደርገው ተራክቦ ስለ ጉዳዩ የሚኖረው ግምት ቅርበትና ርቀት ፣ ውዴታና ጥላቻ ነው፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደትም ተማሪ የሚገጥመውና በውስጡ የሚያልፍበት ማለትም የቋንቋው መምህር፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣አጠቃላይ የትምህርቱ ሥርዓትና ሌሎች ማህበራዊ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ ከነዚህ ጉዳዮች ጋር በሚያደርገው መስተጋብርና የመማር እንቅስቃሴ የሚመነጭ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከትን ያዳብራል፡፡ያዳበረው አመለካከት ደግሞ ተማሪው በትምህርቱ ሂደት ከሚያደርገው የመማር ጥረትና ከሚደርስበት ውጤት ጋር ይገናኛል በማለት ገልጿል፡፡ ከዚህ የምንረዳው አመለካከት ሰው በኑሮው ሂደት ከሚገጥመው ሁኔታ ወይም ነገር ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የመውደድም ሆነ የጥላቻ ስሜት ይኖረዋል፡፡ እንደዚሁም ተማሪው የቋንቋን ትምህርት ሲማር ከሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ፣ ከትምህርቱ ስርዓትና ከሌሎችም መሰል ጉዳዮች ጋር በሚያደርገው ግንኘነት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከትን ያዳብራል፡፡ ይህም በተዘዋዋሪ መንገድ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

የአመለካከትና የውጤት ዝምድና አስመለክተው ሌሎች የመስኩ ምሁራን ጥናት አቅርበዋል፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ Muler (1971፡290)ነው፡፡ እንደ ሙለር አገላለጽ ተማሪዎች ለሚማሩት በቋንቋ ፣ትምህርቱ የሚሰጥበት ሁኔታ፣ ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰቦችና ለባህላቸው ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ድርሳናትም የሚያመለክቱት ይህንኑ ነው፡፡ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ከአማካይ የተማሪዎች ውጤት (GPA) ከዝቅተኛው ውጤት ጋር ጥምረት ሲያሳይ፣ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ደግሞ ከከፍተኛው ውጤት ጋር ዝምድና አሳይቷል፡፡

ስለዚህ መምህራን አመለካከት በቋንቋ ትምህርት እና በውጤታቸው ላይ ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ተገንዝበው ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት በጎ አመለካከት ካላቸው ደግሞ የፈተና ውጤታቸውም ጥሩ ይሆናል፡፡ስለአመለካከት መነቃቃት ምንነትና ከቋንቋ ትምርት ጋር ስላላቸው ተዛምዶ በርካታና ተደጋጋሚ ጥናት ካደረጉ ምሁራን ውስጥ ጋርድነርና ተባባሪዎቹ (Gardner 1985፣ Dubin 1986፣ Onoda 1976፡152) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የሙለርን ሀሳብ በመደገፍ ሲገልፁ፡- ለቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ከከፍተኛ ውጤት አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ደግሞ ከዝቅተኛ ውጤት ጋር ዝምድና እንዳለው በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡

Ulia and others (1985፤473) የተማሪዎችን አመለካከት ከራስ መተማመን ጋር አጣምረው ባጠኑት ጥናት ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ መልካም አመለካከት ካላቸው በትምህርቱ ንቁ ተሳታፊ ከመሆናቸውም በላይ በራሳቸው ላይ መተማመን ስሜት ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች ደግሞ ለቋንቋው ትምህርት ጥሩ አመለካከተግ ስለሚኖራቸው ውጤታቸው ከሌሎች ተማሪዎች የተሻለ መሆኑን በጥናታቸው ደርሰውበታል፡፡ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት የሚያገኙት ውጤት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ጥሩ ውጤት አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸው ጥሩ ውጤት እንዲያገኙና እንዲቀሳቀሱ (motivation) የየራሳቸውን ዘዴ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ማለት ግን ተማሪዎቹ ሁሉ ጥሩ እንዲያመጡ ተብሎ ከደረጃ በታች የሆነ በጣም ቀላል ፈተና ይሰጥ ማለት አይደለም፤ በጣም ቀላል ፈተና መሆኑ ራሱ እንዳይቀሳቀሱና አሉታዊ አመለካት እንዲያድርባቸው

ሊያደርግ ይችላል፡፡ (Harmer 2012፣ Stern 2014፣ Littlewood 2014)፡፡ የተማሪዎችን ውጤት አስመልክቶ ፣ Harmer (2015) "ጥሩ ውጤት ማግኘት አለማግኘት በተማሪው እጅ ቢሆንም መምህሩ በሂደቱና በአፈፃፀሙ ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል" ይላል፡፡

አመለካከትን ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አኳያ ስንመለከት እንደ ትምህርት ውጤት መገለጫ ሆኖም ያገለግላል Garder (1985)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ብቻ ሳይሆን ከቋንቋ መማር ሂደት ጋርም ግልጽ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ እንደ ጋርድነር አገላለጽ ቋንቋን ለማወቅ መጣር፣የመማር ዓላማን የማሳካት፣ ምኞትን ከግብ ላድረስ መትጋት ቋንቋ ለመማር የሚያስችሉ የጥሩ አመለካከቶች ቅንጅት ናቸው፡፡ ይህም የሰዎችን ፍላጎት፣ ስሜት፣ ጉጉት የሚያንፀባርቅ ከውስጣዊ ወይም ከውጫዊ ግፊት በመነሳት ቀና አመለካከትን፣አዎንታዊ ምላሽን እና ጥሩ ውጤትን የሚያስገኝ አንድን ድርጊት እንዲፈፀም የሚያበረታታ ሂደት መሆኑን ያመለክታል፡፡

የተማሪው ቀደምት ልምዶችም በትምህርቱ ላይ ተጽዕኖ እንዲያደርጉበት Harmer (2013) እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡ ... ምናልባት ተማሪው ቀደም ሲል ይህንን ቋንቋ ተምሮ ያቋረጠ ከሆነና አሁን እንደገና እንዲማር ከተደረገ የበፊት ገጠመኙ መንፀባረቅ ይጀምራል፡፡ በፊት ሲማር እንዴት ከብዶት እንደሆነ አሁን ትምህርቱን ገና ሳይጀምር "እኔን ይከብደኛል፣ አልችልም" በማለት ከወዲሁ አሉታዊ አመለካከት ይዞ ትምህርቱን ይጀምራል፡፡ በአንፃሩ ድሮም የሚወደውና ጥሩ ውጤት ያስመዘገበበት ከሆነ አሁንም በአዎንታዊ አመለካከት ሊነሳሳ ይችላል፡፡ Chasten (2009) "በክፍል ውስጥ ንግግርን ለመማርና ከሌሎች ጋር ለመግባባት ተማሪዎች አዎንታዊ የግል ሀሳብና የመተባበር አመለካከት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የሌሎችን ሀሳብ ለማዳመጥና የራሳቸውንም ሀሳብና ስሜት ለመግለጽ ፍቃደኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል" ይላል፡፡

ስለዚህ አመለካከት ከተማሪዎች የትምህርት እንቅስቃሴና ውጤት ጋር የጠበቀ ግንኙነትና ተዛምዶ እንዳለው በርካታ የመስኩ ምሁራን በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡በት/ቤቱ የሚገኙ መምህራንም ሆኑ የትምህርት ባለሙያዎች አመለካከት ከቋንቋ ትምህርት ጋር የጠበቀ ዝምድና እንዳለው ተገንዝበው ትኩረት ሊሰጡት ይገባልም ይላሉ፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች አፍ የፈቱበትን ቋንቋ አጠቃቀም ስልት ለምደው ስለሚያድጉ ይህ ተጽእኖ ሁለተኛ ቋንቋ ላይ ጫና በማሳደር ለቋንቋው ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ

እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህም በተጠቀሰው ቋንቋ የሚያስመዘግቡት ውጤት ጋር ባለው ተዛምዶ ሊገለጽ ይችላል፡፡ አጥኚው ከላይ ከተጠቀሱ የክለሳ ድርሳናት በተለይ አመለካከትና የቋንቋ ትምህርት ግንኙነት፣ አመለካከትና የውጤት ዝምድና፣ የትምህርቱ አቀራረብና የመምህራን የማስተማሪያ ስልት በተማሪዎች አመለካከት ላይ የሚኖረው ሚና ከሚሉ ርዕሶች ለጥናቱ የዋሉ የጽሑፍ መጠይቆች ለመምህራንና ለተማሪዎች የተዘጋጁ ሲሆን የጽሑፍ ፈተና ግን በከመማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ ለተማሪዎች ተሰጥቷል፡፡

## 2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን አራት የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፎችን ለማየት ተሞክሯል፡፡ እነዚህ ፅሑፎች ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር የተደረጉ ጥናቶች ሲሆኑ እነዚህንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

1. አበበ ከበደ፡ (2003) ፡ "የመሠናዶ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበ ጥናት ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የመሠናዶ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና የሚል ሲሆን የጥናት ዝርዝር ዓላማዎችም የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል የሚለውን ማረጋገጥ፤ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት በውጤታቸው ላይ ተጽእኖ አሳድሮ እንደሆነ መመርመር፤ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ በሚሰጡ ፈተናዎች ላይ አለመካተቱ ቋንቋን ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነት አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሮ እንደሆነ ማረጋገጥ፡የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ፈተና ላይ አለመካተቱ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ የፈጠረውን ስሜትና በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ያለውን ግንኙነት መመርመር፤ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚኖራቸው አመለካከት ላይ የትምህርት ቤቱ ርዕሳነ መምህራንና የት/ቤቱ አስተዳደር ተጽእኖ መኖሩን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡አጠናን ዘዴ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም ተማሪዎቹ ለቋንቋ ትምህርቱ፣ ለመምህሩና ለመማሪያ መጽሐፉ አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸውና ይህም በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ ተገልጿል፡፡ ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትንና አመለካከትን መሰረት አድርጎ መከናወኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል፡፡ ከተመዘገበው ውጤት አንጻር ግን ይለያል፡፡ ይህን ጥናት ከዚህ ጥናት ልዩ የሚያደርገው የመጀመሪያው የአበበ ከበደ ጥናት የመሠናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው

ዝምድና ምን እንደሚመስል መመርመር የሚል ሲሆን ይህ ጥናት ግን አፋቸውን በዳውሮኛ ቋንቋ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው የልዩነት ነጥብ የአበበ ከበደ ጥናት ከ12 ዓመታት በፊት በ2003 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን ይህ ግን የአሁን ጊዜ ጥናት ነው፡፡ ሶስተኛው ልዩ የሚያደርግ ነጥብ የአበበ ከበደ የአጠናን ዘዴው ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ሲሆን ይህ ጥናት ግን መጠናዊ የምርምር ሥነዘዴን ተከትሎ የተሠራ ነው፡፡

2. ወንድወሰን በየነ፡ (1989) ፡ "የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና ምን ይመስላል"በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟኒት ያቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማም ከርእሱ ጋር አንድ የሆነና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና መመርመር ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎቹም ተጠኚ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት መመርመር፤ ተማሪዎች ለመምህራቸውና ለሚያስተምሩት ስልት የሚሰጡትን ግምት ማወቅ፤ ተማሪዎች በመማሪ መጽሐፍ ያላቸውን አተያይ አጥንቶ መረጃ ማግኘት፤ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ በሚኖራቸው አመለካከት ወላጆች፣ ባለእንጀሮችና ማህበረሰቡ የሚያደርሱትን ተጽእኖ ከተማሪው ማረጋገጥ፤የተማሪዎች አመለካከት በፈተና ውጤታቸው ላይ ምን ያህል እንደሚንጸባረቅ ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡ የተጠቀመው የአጠናን ስነዘዴ መጠናዊ ምርምር ነው፡፡የወንድወሰን ጥናት ውጤት ተማሪዎች ለመማሪያ መጽሐፍ አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው፣ለመምህራን ዝቅተኛ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸውና የተማሪው ወላጆች፣ ባልንጀሮችና ማህበረሰቡ ተማሪዎች አማርኛ ለቋንቋው ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዲቀርጹ አጋዥ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋንና አመለካከትን መሰረት አድርጎ መከናወኑ ከዚህ ጥናት ተመሳሳይ ያደርገዋል፡፡ ከተመዘገበው ውጤት አንጻር ግን ይለያል፡ ይህ ጥናት ከዚህኛው ጥናት ጋር ተቀራራቢ ቢሆንም በሁለቱ መካከል ልዩነት አለ፡፡የመጀመሪያው ልዩነት የወንድወሰን ጥናት አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ በሆኑ 12ኛ ክፍልተማሪዎች ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ዳውሮኛ የሆነ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ሌላው የወንድወሰን ጥናት ያተኮረው በቀድሞ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን ይ ጥናት ግን ባሁኑ ሰዓት በመማር ላይ በሚገኙ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ሶስተኛው የወንድወሰን ጥናት የተካሄደው ከ25 ዓመት በፊት ሲሆን ይህ ጥናት ግን የአሁን ጊዜ ጥናት በመሆኑ በሁለቱ ጥናት መካከል የሠፋ ልዩነት አለ፡፡

3. ኢዮብ ፀጋዬ፡ (2010) "በጅማ ዞን ሶኮሩ ወረዳ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት ትንተና፡፡" በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርስቲ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበ ጥናት ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሰኮሩ ና በደነባ ከተማ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት / Attitude/ መተንተን የሚል ሲሆን ይህ ጥናት ግን በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ

የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ የሚል ስለሆነ ከኢዮብ ፀጋዬ ጥናት ጋር አይገናኝም በሁለቱ መካከል ልዩነት አለ፡፡ ሌላው የኢዮብ ፀጋዬ ጥናት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ስላላቸው አመለካከት ብቻ የሚያጠና ሲሆን ይህ ጥናት ግን አመለካከት ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ስለሚፈትሽ በሁለቱ መካከል ልዩነት አለ፡፡ የኢዮብ አጠናን ስነዘዴው ቅይጥ የጥናት ዘዴ ሲሆን ይህ ግን መጠናዊ የምርምር ዘዴ በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡ የኢዮብ ፀጋዬ ጥናት የተካሄደው ከ 6 ዓመት በፊት በ2010 ዓ.ም ሲሆን ይኸኛው ግን የአሁን ጊዜ ጥናት መሆኑ በሁለቱ መካከል ልዩነት እንዲኖር አድርጓል፡፡ የኢዮብ ጥናት ዝርዝር ዓላማም፡- የአማርኛ ቋንቋና የቋንቋው ትምህርት በተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነቱ ምን ያህል እንደሆነ መመርመር፤ የተማሪው እኩዮች ስለ አማርኛና ስለተማሪው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት ያላቸውን አመለካከት መተንተን፤ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስልጠናቸው፣ በትምህርት አቀራረባቸው ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት ለመቀስቀስ ያላቸውን አቅም መተንተን፤ የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ከተማሪዎች ፍላጎት አኳያ ያላቸውን ተቀባይነት መመርመር፤ ትምህርት ቤቶች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ድጋፍ ሰጪ ነገሮችና የማስተማር ዘዴዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምቹ መሆን አለመሆናቸውን መመርመር የሚሉ መሆናቸው ከዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማ ልዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ውጤትን በሚመለከት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን እንደሚወዱ፣ ከሌሎች ቋንቋዎች ይልቅ እንደሚፈልጉና ወላጆችም ልጆቻቸው በአማርኛ ቋንቋ እንዲማሩ ፍላጎታቸው እንደሆነ እንዲሁም የመማሪያ መጻሕፍት ሲዘጋጅ ትምህርቱ በልብወለድ፣ በጭውውት፣ በቅኔና በምሳሌያዊ አነጋገር ወዘተ ማካተት እንዳለበት ይገልጻል፡፡

4. ተዋበች ተክሌ (2003) በከፍኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ 10ኛ ተማሪዎችን ተተኳሪ አድርገው ያካሄዱት ጥናት ውጤት እንዳመለከተው አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት ተተኳሪ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዳለቸው አሳይቷል፡፡ ይሁንና በሌላ በኩል የጥናቱ ውጤት ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማስተማር ስልትና ለመማሪያ መጽሐፉ ግን አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ጠቁሟል፡፡ ይህ ጥናት በተመሳሳይ የአማርኛ ቋንቋን መሰረት አድርጎ የተከናወነ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር እንዲመሳሰል ያደርገዋል፡፡ ይሁንና ከጥናቱ ዓላማና ውጤት አንጻር እንዲሁም ጥናቱ በካፍኛ ቋንቋ ላይ መካሄዱ ከዚህ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡ ይህ ጥናት የአስረኛ ክፍል ዳውሮኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎችን ተተኳሪ አድርጎና እነኚህ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ጥናት ነው፡፡

ወንድወሰን በየነ፣ አበበ ከበደና ተዋበች ተክሌ በተለያየ ዓመት ባደረጉት ጥናት ዋነኛ ዓላማቸው አድርገው የተነሱት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው፡፡ ይህም ከዚህ ጥናት ጋር ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ፣ በክፍል ደረጃ፣ በአፍ-ፈት ቋንቋና በጊዜ ቆይታ የሠፋ ልዩነት

መኖሩ ይስተዋላል፡፡ ወደ ዝርዝር ዓላማ ስንመጣ ከላይ የቀረቡ ሁለቱም አጥኚዎች ዝርዝር ዓላማቸውን በሚመለከት ተጠኚዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ላለው ተዛምዶ ምን እንዲመስል ለመለየት አጋዥ ይሆናሉ ብለው ያቀረቡት ዝርዝር ዓላማዎች ከዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማ ጋር ሲነፃፀሩ ልዩነት አላቸው፡፡

ኢዮብ ፀጋዬ በ2010 ዓ.ም ባካሄደው ጥናት ዋነኛ ኣላማ አድርጎ የተነሳው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት መተንተን ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ ለተጠኚዎች ያቀረባቸው ዝርዝር ዓላማዎችም ከዚህ ጥናት ዓላማ አይገናኙም፡፡ ውጤታቸውን በሚመለከትም ተጠኚዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ላለው ተዛምዶ መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ላቀረቡት መላምቶች መልስ የሚሰጡ ስለሆነ ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍና አጠናን ዘዴ

ይህ ምዕራፍ አጠቃላይ የጥናቱ ዘዴ አከዋወን የሚቀርብበትና የሚወሰንበት እንደመሆኑ መጠን የጥናቱ ንድፍ፣ የጥናቱ ቦታና ተሳታፊዎች አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች ትክክለኛነትና አስተማማኝነት፣ እና የመረጃ አተናተን ዘዴ የሚሉት ጉዳዮች በዝርዝር ተዳስሰውበታል፡፡

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ የመፈተሽ ዓላማ ያለው ነው፡፡ ይህንንም ዓላማ እውን ለማድረግ ገላጭ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተከትሎ ተከናውኗል፡፡

### 3.2 የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱን ለማካሄድና መረጃዎችን ለመሰብሰብ አጥኚው የተጠቀመበት ዘዴ መጠናዊ የምርምር ዘዴ ነው፡፡ ጥናቱ በአመለካከትና ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚፈትሽ በመሆኑ ገላጭ ተዛምዶን ተከትሎ ተከናውኗል፡፡ መጠናዊ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ዋናው ምክንያትም በዳውሮኛ አፍ-ፈት የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና  ምን እንደሚመስል በትክክል ለመለየት የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም መጠናዊ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሆነ ለመለየት ሊነሱ የሚችሉ በርከት ያሉ ምክንያቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ዋና ዋና ከሆኑት ምክንያቶች መካከል ይበልጥ አጥኚው በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ብሎ የሚያስባቸውን የተወሰኑ መለኪያዎች በመምረጥ ለጥናቱ የተጠቀመ በመሆኑ ነው፡፡ይህ የምርምር ዘዴ የተማሪዎችን አመለካከት ለመለካት፣በተማሪዎች ውጤት ላይ የሚንጸባረቁ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመመርመርም ያስችላል፡፡ ስለሆነም ለጥናት ሥራ ጠቃሚ ሆኖ ስለተገኘ ይህ መጠናዊ የምርምር ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በሌላም በኩል በመጠናዊ የምርምር ዘዴ ለጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ተአማኒነት ያላቸውና ከአጥኚው ግል ስሜት የፀዱ እንዲሁም የጥናቱ ርዕስ በሆነው በአመለካከትና በውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ በቀጥታ ለመግለጽ የሚያስችሉ በመሆናቸው ነው፡፡ የችግሩን ስፋትና አስቸጋሪነት በሚገባ ለማብራራትና ለመግለጽም ያስችላል፡፡  በመሆኑም

በዚህ ዘዴ የተሰበሰቡ መረጃዎች ይህንን ዘዴ ተከትለው ችግሩ ምንድርነው ? ለችግሩ መፍትሄውስ ምንድርነው? ችግሩን መቅረፍ የሚቻለውስ እንዴት ነው? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እያስነሱና መልስ እየሰጡ ተተንትነዋል፡፡

### 3.3 የመረጃ ምንጮች /ተጠኚዎች/

ለዚህ ጥናት ዋና የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉት በደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ በዳውሮ ዞን ቶጫ ወረዳ ቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ አፋቸውን በዳውሮኛ ቋንቋ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

### 3.4 የጥናቱ አካላይ

የጥናቱ አካላይ የሆኑት በደ/ም/ኢ/ህ/ክልላዊ መንግስት በዳውሮ ዞን ቶጫ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና አንድ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፋቸውን በዳውሮኛ ቋንቋ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የትምህርት ቤትና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ሁኔታም እንደሚከተለው ተከናውኗል፡፡

#### 3.4.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ በናሙናነት በቶጫ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃና አንድ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መካከል በአመቺ የናሙና ዘዴ (Convienece sampling method) የቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጧል፡፡ የቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያት በቁጥር በርካታ ተማሪዎች በመማር ላይ የሚገኙበት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከመሆኑም ባሻገር ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ በወረዳ ውስጥ አገልግሎት እየሰጠ የቆየ አንጋፋ ትምህርት ቤት በመሆኑም ነው፡፡ ሌሎቹ ትምህርት ቤቶች በቅርብ ጊዜ በ2014 ዓ.ም አዲስ የተከፈቱና የያዙት ተማሪዎች ቁጥርም እጅግ ዝቅተኛ ስለሆነ በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱም ፡፡ ከተመረጠው ተምህርት ቤት ለጥናቱ አፋቸውን በዳውሮኛ ቋንቋ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተወሰደዋል፡፡ ይህ ክፍል የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱ በተካሄደበት ክልልም ሆነ አካባቢ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው ከ3ኛ እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ስለሆነና በ11ኛና 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለማይሰጥ ከ3ኛ እስከ 10ኛ ድረስ ካሉት ክፍሎች ውስጥ በዕድሜም ሆነ በአእምሮ በሳል የሆኑና ለጥናቱ በቂ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚገመቱ ተማሪዎች የሚገኙበት ክፍል ስለሆነ ነው፡፡

#### 3.4.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ በቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚገኙ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ፣ የዚህ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማዕከላዊ ደረጃ ላይ የሚገኙና አንጻራዊ በሆነ መልኩ

በዕድሜና በትምህርት በሳል ተማሪዎችና ቁጥራቸውም የጥናቱን ተአማኒነትን ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ በመሆናቸው ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ትምህርት ቤት ሶስት መቶ ሠላሳ አምስት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንድ መቶ አርባ ተማሪዎች ወንዶች ሲሆኑ አንድ መቶ ዘጠና አምስት ተማሪዎች ሴቶች ናቸው፡፡ የተጠኚ ተማሪዎችን አመራረጥ በተመለከተ እነዚህን ተማሪዎች በሙሉ በጥናቱ ውስጥ ለማካተት ከቁጥራቸው ብዛት የተነሳ አስቸጋሪ ስለሆነና የጊዜ ብክነትንም ስለሚያስከትል በእጣ ንሞና /Random sampling/ የንሞና ዘዴ እያንዳንዱ የጥናቱ አካላይ አባል ናሙና ውስጥ ሆኖ ለመመረጥ እኩል እድል እንዲኖረው ተደርጎ ምርጫው ተከናውኗል፡፡ በዚህ ዘዴም የጥናቱ አካላይ ሆነው የቀረቡ ተጠኚ ተማሪዎች በተቀመጡበት አኳያ ቁጥር ከተሰጣቸው በኋላ በየአስር ቁጥር ልዩነት ሶስት ተማሪዎች በናሙናነት የተመረጡ ሲሆን ከጠቅላላ 335 የጥናቱ አካላይ ከሆኑ ተማሪዎች ውስጥ ከመቶ ሠላሳ ፐርሰንት (30%) ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ በዚህ መሰረት ቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቱ ውስጥ በመማር ላይ ከሚገኙ ሶስት መቶ ሠላሳ አምስት (335) የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል አጥኚው 100 ተማሪዎችን በእጣ የንሞና አመራረጥ ዘዴ መርጧል፡፡

### 3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የአማርኛ ቋንቋ ለተጠኚ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋና ያውም ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ በትምህርትነት የሚሰጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እነዚህ ተማሪዎች በቋንቋው ላይ ያላቸውን አመለካከት ለመፈተሽ የጽሑፍ መጠይቅና አመለካከታቸው ከውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና ለመፈተሽ ደግሞ ባሁኑ ሰዓት በመማር ላይ ከሚገኙበት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀ የጽሑፍ ፈተና በመስጠት በመካከላቸው ያለውን ተዛምዶ የሚመረምር ነው፡፡

መለኪያውን በሚመለከትም Dubin፡ (1986፣15) እንደሚሉት የአመለካከት መለኪያዎች በጣም አስቸጋር፣ ከበድ የሚሉና ጥንቃቄ የሚሹ ናቸው፡፡አመለካከት ከሰዎች ባህርይ ጋር የተወሳሰበና ከሱም የሚመነጭ በመሆኑ መለኪያው ፍፁም ሊሆን ይችላል ማለት ያስቸግራል፡፡ በመሆኑም እስካሁን አመለካከትን ለመለካት በጥቅም ላይ ከዋሉ መሳሪያዎች ውስጥ የጽሑፍ መጠይቅና የቃለመጠይቅ ይጠቀሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህም የተጠያቂውን ውስጣዊ ስሜትና እምነት ፈልቅቀው የማውጣት ፍፁም ኃይል አላቸው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም ተጠያቂዎች አንዳንድ ጊዜ ግልጽ ሆነው

የሚያምኑበትንና የሆኑትን ሳይሆን ጠያቂው ይፈልገዋል ብለው የገመቱትን ወይም የራሳቸውን ውጫዊ አስተያየት ብቻ የሚገልፁበት ሁኔታ ስለሚያጋጥም ነው፡፡ስለዚህም ነው አመለካከትን ማጥናት ከባድም ውስብስብም የሚሆነው፡፡ ይሁን እንጂ የሚቀርቡት መጠይቆች በጥንቃቄ ተዘጋጅተው ለማወቅ በሚፈለገው ጉዳይ ላይ ያነጣጠሩ ሆነው በአዘገጃጀታቸውም ተሰበጣጥረው የተዘጋጁ ከሆነ የታለመውን ጉዳይ ሊያሳኩ ይችላሉ ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

እንግዲህ እንደ ጥናቱ መለያየት ሁሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችም ሊለያዩ ስለሚችሉ ጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የተማሪዎችን አመለካከትና ይህ አመለካከት በውጤታቸው ላይ ሊያሳድር የሚችለውን አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ተጽእኖ ለመለካት የሚያስችልና ለጥናቱ ምቹ የሆነ ዘዴ መምረጥን ነው፡፡

Taron and Yall (2013)፣kichen (2014)፣ Spolsky (2010) " የተማሪዎችን አመለካከት ለማወቅ ግልፅ የሆነው መንገድ እነሱን መጠየቅ ነው" ይላሉ፡፡ በዚህም መሠረት አጥኚው የተማሪዎች አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመለካት ሁለት ተላውጦዎችን ተጠቅሟል፡፡ እነዚህም፡-

1. ለተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ ስላላቸው ትኩረት፣ ስለትምህርቱ አቀራረብ ፣ ስለቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ ስልትና የመምህራን የትምህርት አሰጣጣቸው ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ የጽሑፍ መጠይቆች እንዲሞሉ ማድረግ
2. በትምህርት ሂደት ላይ የተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ውጤት ከአመለካከታቸው ጋር ተዛምዶ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ከክፍላቸው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የጽሑፍ ፈተና አዘጋጅቶ መስጠት የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህን መረጃ ለመሰብሰብ የተመረጡ ስልቶችን ከግብ ለማድረስ የተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በቁጥር ሁለት ሲሆኑ እነዚህም የጽሑፍ መጠይቅና የጽሑፍ ፈተና ናቸው፡፡ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች ለመመለስ በሚያስችሉበት ሁኔታ ለደረጃው በሚመጥን መልኩ ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡ እነዚህም በሊከርት የመጠይቅ መመዘኛ ስኬል የቀረቡ የጽሑፍ መጠይቆችና ተማሪዎች

ባሉበት ደረጃ ላይ ከሚገኝ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅተው የቀረቡ የጽሑፍ ፈተናዎች ናቸው፡፡

### የጽሁፍ መጠይቅ

Dubin and alshichen (1986፣17) "የአመለካከት ጥያቄዎች ዝግ መሆን ይኖርባቸዋል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ በዚህ መሰረት የጽሁፍ መጠይቆቹ ለቋንቋ ትምህርት የአመለካከት መለኪያ ምቹ እንደ መሆናቸው መጠን ከቋንቋ ትምህርት አጠቃቀምና ባህሪያት ጋር ቅርበት አላቸው ተብለው የሚገመቱ በቁጥር 15 የጽሑፍ መጠይቆች ለተማሪዎች ቀርበዋል፡፡ ለተማሪዎች የቀረቡ መጠይቆች በሀሳብ ደረጃ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የተሰበሰቡ መረጃዎች ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመካከት ለማወቅ የሚያስችል ሀሳብን የያዙ ናቸው፡፡ ለቀረቡ የጽሑፍ መጠይቆች መልሶቹ አምስት አማራጮች እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ የቀረቡ መጠይቆች በሙሉ አዎንታዊ ሀሳብ ያላቸው ሲሆኑ የመጠይቁ አማራጭ መልሶችና ወካይ ቁጥሮች ከዚህ ቀጥሎ ተብራርተዋል፡፡

**የአዎንታዊ መጠይቅ አማራጭ መልሶችና ወካይ ቁጥሮች**

በጣም እስማማለሁ--------------------5

እስማማለሁ------------------------------4

ለመወሰን እቸገራለሁ-----------------3

አልስማማም-----------------------------2

ፍፁም አልስማማም-------------------1

**የአሉታዊ መጠይቅ አማራጭ መልሶችና ወካይ ቁጥሮች**

በጣም እስማማለሁ---------------------1

እስማማለሁ------------------------------2

ለመወሰን እቸገራለሁ------------------3

አልስማማም-----------------------------4

ፍፁም አልስማማም-------------------5

በመሆኑም ከተማሪዎችና ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በሙሉ በዚህ መልኩ ተመዝነው የሚተነተኑ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት በጥናቱ ለተካተቱ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅና የጽሑፍ ፈተና ቀጥሎ የቀረቡ የጥናቱ መሪ ጥያቄዎችን ለመመለስ በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅተዋል፡፡/ከሠንጠረዥ 1-11 ድረስ ያለውን ይመልከቱ/

1- በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ ይኖረው ይሆን? ለሚለው ለጥናቱ መሪ ጥያቄ ሁለቱንም ተላውጦዎች ለመመዘን በጽሑፍ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች አማካይ ውጤትና የፈተና አማካይ ውጤት አንድ ላይ ተሰልቶ ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል/ከሠንጠረዥ 1-10 ድረስ ያለውን ይመልከቱ/፡፡
2- አመለካከት የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት ውጤት የመተንበይ ድርሻ ይኖረው ይሆን? ለሚለው የጥናቱ መሪ ጥያቄ ከመለኪያ አንድ እስከ መለኪያ አራት ድረስ የቀረቡ መጠይቆች ምላሽ የሚሰጡ ይሆናል/ከሠንረዥ 1-3 ድረስ ያለውን ይመልከቱ/፡፡
3- የትምህርቱ አቀራረብና የማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች ለትምህርቱ ባላቸው አመለካከት ላይ ተጽእኖ አሳድሮ ይሆን? ለሚለው የጥናቱ መሪ ጥያቄ በመለኪያ አራትና አምስት ስር የቀረቡ መጠይቆች ምላሽ የሚሰጡ ይሆናል/ሠንጠረዥ4- 5 ይመልከቱ/፡፡

### 3.5.1.1የመረጃዎች ስሌታዊ አሠራር /ቀመር/

በዚህ ስር መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ በጽሑፍ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡ አረፍተ ነገሮች ከያዙት ነጥብ አኳያ እያንዳንዱ መላሽ ያገኘው ነጥብ ተለይቶ ይመዘገባል፡፡ ከእያንዳንዱ መላሽ በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ የተገኙ ነጥቦች ተደምረው ከአምስቱ የስምምነት ነጥብ የተገኘው አማካይ ነጥብ ይሰላል፡፡ የአማካይ ነጥቡንም አሠራር ስንመለከት ለምሳሌ የመምህራን የትምህርት አሰጣጥን በሚመለከት በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ላይ 100 ተሳታፊዎች የተለያየ ምላሽ ሰጥተዋል እንበል፡፡በምላሹም፡-

በጣም እስማማለሁ 25 መላሾች

እስማማለሁ 15 መላሾች

መወሰን ያስቸግረኛል 8 መላሾች

አልስማማም 40 መላሾች እና

ፍፁም አልስማማም 12 መላሾች መልሰዋል እንበል፡፡

በምዕራፍ ሶስት እንደተገለፀው ይህ በመጠይቁ ውስጥ ተካትቶ የቀረበ መለኪያ በመሆኑ በጣም እስማማለሁ /5/፣

እስማማለሁ /4/፣

መወሰን ያሥቸግረኛል /3/፣

አልስማማም /2/፣

ፍፁም አልስማማም /1/ ነጥብ ዋጋ ይኖራቸዋል፡፡

ከዚህም በመነሳት አማካይ ነጥብን ለማግኘት የስምምነቱን ነጥብ በድግግሞሹ ብዛት ማባዛትና መደመር ከዚያም ለመላሾቹ ቁጥር ማካፈል ይሆናል፡፡

ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሠረት የመላሾቹ ቁጥር 100 ስለሆነ

$$\frac{25x5+15x4+8x3+40x2+12x1}{100}$$

$$= \frac{125+60+24+80+12}{100}$$

$$= \frac{301}{100}$$

$$= 3.01$$ አማካይ ውጤት ነው፡፡

በመሆኑም ከተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በሙሉ በዚህ መልኩ ተተንትነዋል፡፡ በዚህም መሠረት የጽሑፍ መጠይቅ በጥናቱ ለተካተቱ ተማሪዎች የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች ለመመለስ በሚያስችል መልኩ በሊከርት ስኬል መመዘኛ ስልት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ የተመዘገበው ውጤት 2.5 እና በላይ ከሆነ አዎንታዊ አመለካከት መኖሩን እንዲሁም ከ2.5 በታች የሆነ ውጤት ከተመዘገበ አሉታዊ

አመለካከት መኖሩን የሚገልጽ ይሆናል፡፡ በዚህ መልክ የተገኘው አማካይ ውጤት ተማሪዎች በጽሑፍ ፈተና ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት ጋር ተዛምዶ መኖር አለመኖሩ የሚፈተሽ ይሆናል፡፡

### 3.5.2 የመጠይቁ ስርጭትና አሞላል

የመጠይቁን ስርጭትና አሞላል በሚመለከት አጥኚው ለጥናቱ የተመረጠው ትምህርት ቤት አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ ከጅማ ዩኒቨርስቲ የተጻፈውን የትብብር ደብዳቤ ይዞ ወደ ትምህርት ቤቱ በመንቀሳቀስ ከትምህርት ቤቱ ባለድርሻ አካላት ጋር ሀሳብ ተለዋውጦ ቅድመ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ ሠርቷል፡፡ መጠይቁ ከመሞላቱ በፊት ከትምህርት ቤቱ መጠይቁን እንዲሞሉ በእጣ ንሞና ለተመረጡ ተማሪዎች አጠቃላይ የመጠይቁን አሞላል ሁኔታ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ተማሪዎች መጠይቁን የሞሉት እዚያው ከትምህርት ቤቱ አዳራሽ ውስጥ ተሰብሰበው ነው፡፡ ይህ እንዲሆን የተደረገውም፡-

1. ተማሪዎች መጠይቁን ወደ የቤታቸው ይዘው ከሄዱ የመጠይቁ ወረቀት ሊቀደድባቸው ወይም ሊበላሽባቸው ይችላል ከሚል ግምት በመነሳትና
2. መጠይቁን ከክፍል ውጭ ይዘው ከሄዱ ብዙዎቹ ተማሪዎች ተነጋገረው ተመሳሳይ መልስ ብቻ በመምረጥ ሞልተው ሊያቀርቡ ይችላሉ ከሚል ስጋት በመነሳት ነው፡፡

ይህ አጥኚው የተጠቀመበት በግንባር ቀርቦ መጠይቁን የማስሞላት ስልት የመረጃ ደህንነትና የማቴሪያል ብክነትን ከመቆጣጠሩም በላይ መረጃውን በቀላሉ እዚያው ሆኖ አጋጣሚ ያልገባቸው ነጥብ ካለም ጥያቄዎቹን እየመለሰ እንዲሞሉ ለማስቻል ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

**የጽሑፍ ፈተና**

ፈተና ሰዎች ስለአንድ ነገር ያላቸውን እውቀትና ችሎታ ለመፈተሽ እንዲሁም ፍላጎታቸውንና ዝንባሌያቸውን ለማወቅ የሚረዳ ነው፡፡ ስለሆነም ፈተና ማለት የተወሰኑ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የተማሪዎችን ወይም የተፈታኞችን እውቀት፣ ችሎታ፣ የባህሪ ሁኔታና ለውጥ አስመልክቶ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል መሳሪያ ነው (Bekman 1990)፣ (ያለው 2009)፡፡

ይህ የጽሑፍ ፈተና ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ አመለካከታቸውን ከገለጹ በኋላ የተገኘው መረጃ አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ከተማሪ ውጤት ጋር ዝምድና አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ለመለየትና ለጥናቱ መሪ ጥያቄ መልስ መስጠት አለመስጠቱን ለማረጋገጥ ስለተፈለገ ነው፡፡ምክንያቱም በተማሪዎች የትምህርት ውጤት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም ከነገሮቹ መካከል አንዱ አመለካከት ስለሆነ አጥኚው ለዚህ ጥናት ተጠቅሞበታል፡፡ ፈተናውም በቀጥታ በቀላል እጣ ንሞና ለተመረጡ ተጠኚ ተማሪዎች ስለፈተና አሰራር ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ እነዚህ ተማሪዎች በመማር ላይ ከሚገኙበት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ መምህራቸው እስከሸፈነበት ገጽና ይዘት ድረስ ካለው የተዘጋጀ ሲሆን በፈተና የሚያስመዘግቡት ውጤት በቋንቋው ላይ ካላቸው አመለካከት ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ የሚውል ይሆናል፡፡ ከዚህም በመነሳት ተጠኚ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ በተለይ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት በትምህርቱ ከሚያስመዘግቡት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል ለመለካት የሚያስችል ፈተና በተለይ በአራቱ ቋንቋ ክሂሎች ላይና በስነጽሑፍ ዘርፍ ላይ በመመርኮዝ ባሉበት ደረጃ ከሚገኝ ከአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በዝግ ጥያቄ መልክ 40 ጥያቄ ተዘጋጅቶ ተሰጥቷቸዋል፡፡(የፈተናውን ሙሉ ይዘት ከአባሪ 3 ይመልከቱ/፡፡

## 3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከተጠኚ ተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በሁለት ተለዋዋጮች ይከፈላሉ የመጀመሪያው ተላውጦ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ መረጃ የሚሰጥ የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ተላውጦ ደግሞ ይህ አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ዝምድና መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ የሚረዳ የጽሑፍ ፈተና ነው፡፡ እነዚህም መረጃዎች ከተማሪዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የመለያ ኮድ ተሰጥቶት በኤስ ፒ ኤስ ኤስ ኤግዜል እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በዚህ ልክ የየጥያቄዎቹ አማራጭ መልሶች በምን ያህሉ ተጠኚዎች እንደተመረጡ ተለይተው ከታወቁ በኋላ ለአማራጮቹ መለያ ኮድ ተሰጥቷቸው ተመዝግበዋል፡፡ በተገኘው ውጤት ላይም የመቶኛና የአማካይ ነጥብ ስሌት

ተሰርቷል፡፡በመቀጠልም እያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ በሁለቱ ተለዋዋጮች ያስመዘገበው ውጤት ተለይቶ ከታወቀና ከተመዘገበ በኋላ በተዛምዶ ስታቲስቲካዊ ስልት ቀመር /correlation/ በተገቢው እንዲሰላ ተደርጓል፡፡ ከሁለቱ ተላውጦዎች የተገኙ መረጃዎች በመጠይቁ ላይ በሰፈሩት ቅደም ተከተል መሰረት እንደየባህሪያቸው ሁኔታ በመቶኛና በአማካይ ነጥብ እየተገለጹ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ይህም የአመለካከት አማካይ ውጤት ከፈተና ውጤታቸው ጋር በንጽጽር ታይቶ አመለካከት ከውጤቱ ጋር ይዛመዳል ወይስ አይዛመድም በሚል ልየታ ተደርጓል፡፡ ከጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ጋርም ተገናዝቧል፡፡

## ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

በዚህ ምእራፍ ውስጥ የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ ተካትቷል፤፤ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ስለሚጀምርበትና ስለሚያበቃበት ክፍል ደረጃ ላይ ያላቸው አመለካከት፣ በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸው ፍላጎት፣ጉጉት፣ ተሳትፎ፣ ወደፊት በቋንቋው ለመቀጠል ስላላቸው ዓላማ፣በአማርኛ ቋንቋ አነጋገር ስልትና በዳውሮኛ ቋንቋ አነጋገር ስልት ላይ ያላቸው አመለካከት፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ላይ ያላቸው አመለካከት፣ በመምህራን የትምህርት አሰጣጥ ስልት ላይ ያላቸው አመለካከትና ይህም ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል ከዚህ በመቀጠል በዝርዝር ቀርቧል፤፤

### 4.1 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ የአመለካከት ውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የተማሪዎች አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና መፈተሽ ነው፡፡ ከታለመው ውጤት ላይ ለመድረስ አጥኚው የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ተጠቅሟል፡፡እነዚህ መሳሪያዎችም የጽሑፍ መጠይቅና የጽሑፍ ፈተና ናቸው፡፡በዚህም መሠረት በምዕራፍ ሶስት እንደተገለጸው አስራ አምስት ጥያቄዎችን ያዘለ የጽሑፍ መጠይቅ ለ100 የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ቀርቦ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ተማሪዎች እንዲሞሉ የቀረቡ መጠይቆች በአምስት መለኪያዎች የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ እነዚህም ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጡ ይሆናል፡፡

1. ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለሚጀምርበትና ስለሚያበቃበት ክፍል ደረጃ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
2. የተማሪዎች የመማር ፍላጎት፣ ጉጉት፣ ተሳትፎ ፣ የሚያስመዘግቡት ውጤትና ወደፊት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመቀጠል ያላቸው ዓላማ ላይ ምን ይመስላል?
3. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አነጋገር ስልትና አፍ በፈቱበት በዳውሮኛ ቋንቋ አነጋገር ስልት ላይ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
4. ተማሪዎች ስለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
5. ተማሪዎች በመምህራን የትነምህርት አሰጣጥ ስልት ላይ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ በቀረቡ መለኪያዎች አማካይነት ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው እያንዳንዱ ተማሪ ያስመዘገበው የአመለካከት ውጤት ተቆጥሮ ተመዝግቧል፡፡ የተገኘው ውጤትም በአማካይና በመቶኛ ተሰልቷል፡፡ ተጠኚ ተማሪዎች ከዕድሜ አንፃርም መረጃውን የሞሉ በሙሉ 16 ዓመትና በላይ በመሆናቸው ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ከፆታ አንፃርም ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት ለጥናቱ የተመለመሉ የወንድ ተማሪዎችና የሴት ተማሪዎች ቁጥር ተቀራራቢ፣ ተመጣጣኝና የፆታ ተሳትፎንም ያመዛዘነ ነው፡፡

በጥናቱ የተሳተፉ አንድ መቶ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ አፋቸውን የፈቱት በዳውሮኛ ቋንቋ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን እንደሚችልና ይህም አመለካከት በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ እንደሚኖረው በምእራፍ ሁለት ላይ ለመግለጽ ተሞክሯል (ክሮንባች 1954)፡፡ ከዚህም በመነሳት የዚህ ጥናት ዓላማ በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ያለመ ስለሆነ ለዚህ ርዕሰ ጉዳይ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ የመረጃዎች ስሌታዊ አሠራር ስልትን ተከትሎ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 4.1.1 ተማሪዎች በአምስቱም መለኪያዎች ያሳዩት አመለካከት ውጤት ትንተና

በዚህ ንዑስ ስር ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት ማለትም ትምህርቱን ስለጀመሩበትና ስላጠናቀቁበት ክፍል ደረጃ፣ በትምህርቱ ላይ ስላላቸው ፍላጎት፣ ጉጉት፣ ስለሚያደርጉት ተሳትፎ፣ ስለሚያስመዘግቡት ውጤት፣ ስለቋንቋ አነጋገር ስልት /ንበት/ ተጽእኖ ፣ ስለመማሪያ መጽሐፍ አቀራረብና ስለመምህራን የትምህርት አሰጣጥ ስልት ያላቸው አመለካት ምን እንደሚመስል አስተያየታቸውን እንዲገልፁ በጽሑፍ መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በዝርዝር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ይህም በአምስት ሠንጠረዦች ተከፍሎ ሠንጠረዥ 1፣ ፣ሠንጠረዥ 2 ፣ ሠንጠረዥ 3 ሠንጠረዥ 4 እና ሠንጠረዥ 5 ላይ ተብራርቶ እንደሚከተለው ቀርቧል፤፤

ሠንጠረዥ 1፡ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ስለሚጀምርበትና ስለሚያበቃበት ክፍል ደረጃ ባላቸው አመለካከት ላይ የሰጡት ምላሽ ትንተና

| ተ/ቁ | ጥያቄ | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ መሰጠቱ በአስረኛ ክፍል ላይ ማብቃቱ በቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ ምንም ዓይነት ጫና አላሳደረብኝም፡፡ | 16 | 16% | 17 | 17% | 11 | 11% | 49 | 49% | 7 | 7% | 2.86 |

ከሠንረዥ 1 እንደምንረዳው ተማሪዎች በተራ ቁጥር 1 የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ መሰጠቱ በአስረኛ ክፍል ላይ ማብቃቱ በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ ጫና አሳድሮ እንደሆነ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ 16(16%) በጣም እስማማለሁ፣ 17(17%) እስማማለሁ፣ 11(11%) ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ 49(49%) አልስማማም፣ 7(7%) ፍፁም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ባጠቃላይ 33(33%) ተማሪዎች የቋንቋው ከ3ኛ ክፍል መጀመሩና አስረኛ ክፍል ላይ ማብቃቱ ተጽእኖ አላሳደረብንም በማለት አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ ፣ 11(11%) ለመወሰን እንደተቸገሩ ገልፀዋል፡፡ ሌሎቹ 56 (56%) ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ መሰጠቱና በአስረኛ ክፍል ላይ ማብቃቱ በቋንቋ አጠቃቀማቸው ላይ ጫና እንዳሳደረባቸው በመግለጽ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡አማካይ ነጥቡ 2.86 ነው፡፡ ስለዚህ 56% የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ መሰጠቱና በአስረኛ ክፍል ላይ ማብቃቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ጫና እንዳሳደረባቸው ለመጠይቁ በሰጡት ምላሽ ጠቁመዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተገኘው አማካይ ነጥብ 2.86 በመጠይቁ ላይ ተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት መኖሩን ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ2 ተማሪዎች በአማርኛቋንቋ ትምህርት ላይ ስላላቸው ጉጉት ፣ ተሳትፎ ፣ ስለውጤታቸው እርካታና ችሎታ ባላቸው አመለካከት የሰጡት ምላሽ ትንተና

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ፍላጎት ስላለኝ ክፍለጊዜውን እጅግ በጉጉት እጠብቃለሁ፡፡ | 20 | 20% | 14 | 14% | 12 | 12% | 45 | 45% | 9 | 9 % | 2.91 |
| 3 | በአማርኛ ትምህርት ክ/ጊዜ ላይ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች የበለጠ እሳተፋለሁ፡፡ | 23 | 23% | 15 | 15% | 9 | 9% | 39 | 39% | 14 | 14 % | 2.94 |
| 4 | የአማርኛትምህርትን ትኩረት ሰጥቼ ስለምከታተል ያስመዘገብኩት ውጤት አርኪ ነው፡፡ | 24 | 24% | 12 | 12% | 10 | 10% | 40 | 40% | 14 | 14 % | 2.92 |
| 5 | የአማርኛ ትምህርት ክ/ጊዜ ካመለጠኝ እንደሚጎዳኝ ስለማውቅ እጠነቀቃለሁ፡፡ | 15 | 15% | 23 | 23% | 10 | 10 | 41 | 41% | 11 | 11 % | 2.90 |
| 6 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ገፍቼ ደራሲ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ | 18 | 18% | 20 | 20% | 12 | 12% | 36 | 36% | 14 | 14 % | 2.92 |
| 7 | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውስጣዊ ስሜት አለኝ ፡፡ | 18 | 18% | 14 | 14% | 20 | 20% | 41 | 41% | 7 | 7 % | 2.95 |

ሠንጠረዥ 2 ተራ ቁጥር 2 በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜን በጉጉት ስለመጠበቅ አለመጠበቃቸው ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ 20(20%) በጣም እስማማለሁ ፣ 14(14%) እስማማለሁ፣ 12( 12%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 45(45%) አልስማማም፣9(9%) ፍፁም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ባጠቃላይ 34(34%) ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን 54(54%) ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

አማካይ ነጥብ 2.91 ነው፡፡ ስለዚህ በዚህኛው መለኪያ መሠረት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካት እንዳላቸው ትምህርቱንም በጉጉት እንደሚከታተሉ የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር 3 ስር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ ስለሚያደርጉት ተሳትፎ ለቀረበላቸው ጥያቄ 23(23%) በጣም እስማማለሁ፣ 15(15%) እስማዘማለሁ፣ 9(9%) መወሰን ያስቸግረኛል፣ 39(39%) አልስማማም ፣ 14(14%) ፍጹም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አጠቃላይ 38(38%) ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 53(53%) ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 2.94 ነው፡፡ ይህም ነጥብ አዎንታዊ በመሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ቢሆንም አመለካከታቸው አዎንታዊ እንደሆነ የሚያመለክት ሆኖ እናገኛለን፡፡

በተራ ቁጥር 4 ላይ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ትኩረት ሰጥተው ስለመከታተላቸውና ያስመዘገቡት ውጤትም አርኪ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ 24(24%) በጣም እስማማለሁ፣ 12( 12% ) እስማማለሁ፣10(10%) ለመወሰን ያስቸግራል፣40 (40%) አልስማማም ፣ 14(14%) ፍፁም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ባጠቃላይ 36(36%) ተማሪዎች ትምህርቱን ትኩረት ሰጥተው እንደሚከታተሉና ያስመዘገቡት ውጤትም አርኪ እንደሆነ ሲገልፁ 10 ተማሪዎች ለመወሰን መቸገራቸውን እንዲሁም 54(54%) ተማሪዎች እንደማይስማሙና ውጤታቸው አርኪ እንዳልሆነ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 2.92 ነው፡ ይህም ውጤት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ እንደሆነ ነጥቡ ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር 5 ላይ የአማርኛ ትምህርት ክ/ጊዜ በትክክል መከታተል አለመከታተላቸውን ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ 15(15%) በጣም እስማማለሁ፣ 23 (23%) እስማማለሁ፣ 10(10%) ለመወሰን መቸገራቸውን ሲገልፁ 41(41%) አልስማማም፣ 11(11%) ፍፁም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 2.90 ነው፡፡ በዚህም መጠይቅ መሠረት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያደርጉት ክትትልና ያላቸው አመለካከትም አዎንታዊ እንደሆነ አሳይተዋል፡፡

በተራ ቁጥር 6 ላይ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ገፍተው ደራሲ የመሆን ፍላጎት ስለመኖሩ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ 18(18%) በጣም እስማማለሁ፣ 20(20%) እስማማለሁ፣ 12 (12%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 36 (36%) አልስማማም፣ 14(14%) ፍፁም አልስማማም በማለት የመለሱ ሲሆን ባጠቃላይ 38 (38%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 12 (12%) ለመወሰን መቸገራቸውን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም 50 (50%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 2.92 ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ገፍተው ደራሲ የመሆን ፍላጎት አዎንታዊ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር 7 ላይ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውስጣዊ ስሜት ስለመኖሩ ለመጠየቅ በቀረበላቸው ጥያቄ 18 (18%) በጣም እስማማለሁ፣14(14%) እስማማለሁ፣ 20 (20%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 41(41%) አልስማማም፣ 7(7%) ፍፁም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 2.95 ነው፡፡ ይህም 48% የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ስሜት እንዳላቸው ያመለክታል፡፡ ከዚህም በመነሳት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ እንደሆነ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 3 ተማሪዎች አፍ በፈቱበት በዳውሮኛ ቋንቋ አነጋገር ስልት /Pronounciation/ እና በአማርኛ ቋንቋ አነጋገር ስልት/Pronounciation/ ላይ እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል የሰጡት ምላሽ ትንተና

| ተ/ቁ | ጥያቄ | አማራጭ | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 8 | አፍ የፈታሁበት የዳውሮኛ ቋንቋ አነጋገር ስልት /Pronounciation/ በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ ምንም ተጽእኖ አላሳደረብኝም፡፡ | 12 | 12% | 14 | 14% | 21 | 21 % | 46 | 46% | 7 | 7% | 2.78 |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ የአነጋገር ስልት /Pronounciation/ | | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቢያስቸግረኝም የአማርኛ ቋንቋ ጽሑፎችን ሳነብና ሲናገር ምንም አልሸማቀቅም፡፡ | 15 | 15% | 19 | 19% | 13 | 13 % | 46 | 46% | 7 | 7% | 2.89 |

ሠንጠረዥ 3 በተራ ቁጥር 8 አፍ የፈቱበት ቋንቋ የአነጋር ስልት በአማርኛ ቋንቋ ላይ ተጽእኖ ማሳደር አለማሳደሩን ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ 12 (12%) በጣም እስማማለሁ ፣ 14 (14%) እስማማለሁ፣ 21(21%) መወሰን ያስቸግረኛል፣ 46 (46%) አልስማማም፣ 7 (7%) ፍፁም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 2.78 ነው፡፡ ይህም አፍ የፈቱበት ቋንቋ የአነጋገር ስልት በአማርኛ ቋንቋ ላይ የሚያሳድረው ጫና እምብዛም እንዳይደለ በግልፅ ያመለክታል ፡፡

ተራቁጥር 9 ላይ የአማርኛ ቋንቋ ንበት/Pronounciation/ ላይ መቸገር አለመቸገራቸውን ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ 15(15%) በጣም እስማማለሁ፣ 19(19%) እስማማለሁ፣13 (13%) መወሰን እቸገራለሁ፣ 46 (46%) አልስማማም፣ 7 (7%) ፍፁም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 2.89 ነው፡፡ ይህ አማካይ ውጤት 2.89 ሆኖ መመዝገቡ በተማሪዎች ዘንድ የአማርኛ ቋንቋ የአነጋገር ስልት/ንበት/ እና የዳውሮኛ ቋንቋ አነጋገር ስልት /ንበት/ አንድ ላይ የሚፈጥሩት ግጭት በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ የሚፈጥረው ጫና እምብዛምም እንዳይደለና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይም አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው የሚያመለክት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡የዚህ መለኪያ የተጠቃለለ አማካይ ውጤት 2.83 መሆኑ የተማሪዎች አመለካከት አዎንታዊ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 4 ተማሪዎች ስለመማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ ምቹ መሆን አለመሆን ላይ ስላላቸው አመለካከት የሰጡት ምላሽ ትንተና

| ተ/ቁ | ጥያቄ | አማራጭ | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ በጣም ምቹና ቀለል ተደርጎ በሚገባን መልኩ የተዘጋጀ ነው ፡፡ | 20 | 20% | 15 | 15% | 12 | 12% | 46 | 46% | 7 | 7% | 2.95 |

ከሠንጠረዥ 4 እንደምንረዳው በዚህ መለኪያ ስር የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ዝግጅትና አቀራረብ በጣም ምቹና ቀለል ተደርጎ በሚገባቸው መልኩ የተዘጋጀ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ በቀረበላቸው ጥያቄ 20(20%) በጣም እስማማለሁ፣ 15 (15%) እስማማለሁ፣ 12 (12%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 46 (46%) አልስማማም፣ 7 (7%) ፍፁም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 2.95 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ባጠቃላይ የዚህ መለኪያ አማካይ ውጤት ሲታይ በመጠይቁ ላይ ተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 5 ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ትምህርት አሰጣጥ ላይ ስላላቸው አመለካከት የሰጡት ምላሽ ትንተና

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | % | 4 | % | 3 | % | 2 | % | 1 | % | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ መ/ራን የትምህርት አቀራረብ በጣም የሚያቃቃ ነው፡፡ | 26 | 26% | 27 | 27% | 15 | 15% | 26 | 26% | 6 | 6% | 3.41 |
| 12 | መ/ራን ተማሪዎች በፍላጎታቸው መሠረት ተደስተው እንዲማሩ ይመክራሉ፡፡ | 28 | 28% | 21 | 21% | 16 | 16% | 19 | 19% | 16 | 16% | 3.26 |
| 13 | መ/ራን ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲወዱ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ | 25 | 25% | 20 | 20% | 15 | 15% | 21 | 21% | 19 | 19% | 3.11 |
| 14 | መምህራን ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ለተማሪዎች እድል ይሰጣሉ፡፡ | 34 | 34% | 13 | 13% | 6 | 6% | 21 | 21% | 26 | 26% | 3.08 |
| 15 | መ/ራን ተማሪዎችን ለማብቃት በአማርኛ ቋንቋ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ | 30 | 30% | 15 | 15% | 10 | 10% | 26 | 26% | 19 | 19% | 3.11 |

ከሠንጠረዥ 5 እንደምንረዳው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት አቀራረብ ላይ ያላቸው አስተያየት ምን እንደሚመስል ለማረጋገጥ በሚል በተራ ቁጥር 11 ላይ

የአማርኛ ቋንቋ መ/ራን የትምህርት አቀራረብ አነቃቂና ማራኪ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ በቀረበላቸው መጠይቅ 26 (26%) በጣም እስማማለሁ፣ 27 (27%) እስ ማማለሁ፣ 15(15%) መወሰን ያስቸግረኛል፣ 26(26%) አልስማማም፣ 6(6%) ፍፁም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ካጠቃላይ ተማሪዎች መካከል53 (53%) አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን 32 (32%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 3.41 ነው፡፡ ይህ ውጤት የሚያሳየው በመ/ራን የትምህርት አቀራረብ ላይ ችግር ሙሉ በሙሉ የለም ባይባልም ለተማሪዎች ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን ነው፡፡

በተራ ቁጥር 12 ላይ መ/ራን ተማሪዎች በፍላጎታቸው መሠረት ተደስተው እንዲማሩ ማድረግ አለማድረጋቸውን ለማረጋገጥ በቀረበላቸው መጠይቅ 28 (28%) በጣም እስማማለሁ፣ 21 (21%) እስማማለሁ፣ 16 (16%) መወሰን ያስቸግረኛል፣ 19 (19%) አልስማማም፣ 16(16%) ፍፁም አልስማማም በማለት ሲመልሱ ባጠቃላይ 49 (49%) አዎንታዊ ምላሽ 35 (35%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥብ 3.26 ነው፡፡ ነጥቡ ተማሪዎች በመምህራን ትምህርት አሰጣጥ ስልት ላይ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር 13 ላይ መምህራን ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን እንዲወዱ ጥረት ማድረግ አለማድረጋቸው ለማረጋገጥ በቀረበላቸው መጠይቅ 25 (25%) በጣም እስማማለሁ፣ 20(20%) እስማማለሁ፣ 15 (15%) መወሰን ያስቸግረኛል፣ 21(21%) አልስማማም፣ 19(19%) ፍፁም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ከጠቅላላዎች 45 (45%) ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን 40 (40%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል አማካይ ነጥብ 3.11 ነው፡፡ በዚህ መጠይቅም አዎንታዊ ሆኖ የተመዘገበው ውጤት የሚያሳየው መምህራን ተማሪዎቻቸው የአማርኛ ቋንቋን እንዲወዱና ትምህርቱንም በተገቢው እንዲከታተሉ እንደሚያደርጓቸው ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር 14 ላይ መምህራን በመማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎቻቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከፍ ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ማድረግ አለማድረጋቸውን ለማረጋገጥ በቀረበላቸው መጠይቅ 34 (34%) በጣም እስማማለሁ፣ 13(13%) እስማማለሁ፣ 6(6%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 21 (21%)አልስማማም ፣ 26(26%) ፍፁም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ካጠቃላይ ተማሪዎች መካከል 47 (47%) ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን 6(6%) ለመወሰን መቸገራቸውን ሲገልፁ 47(47%) ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ

ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥቡ 3.08 ነው፡፡ይህም ወደ አማካይ ነጥብ ስንመጣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለማብቃት ጥረት እንደሚያደርጉ የሚያሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡የተማሪዎች አመለካከትም አዎንታዊ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በተራ ቁጥር 15 ላይ መምህራን ተማሪዎች ለማብቃት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ማድረግ አለማድረጋቸውን ለማረጋገጥ በቀረበላቸው መጠይቅ 30(30%) በጣም እስማማለሁ፣ 15(15%) እስማማለሁ 10(10%) ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 26 (26%) አልስማማም፣ 19 (19%)ፍፁም አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ መጠይቅ ስር ካጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ 45 (45%) ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 10 (10%) ተማሪዎች ለመወሰን መቸገራቸውን እንዲሁም 45 (45%) ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ነጥቡ 3.11 ነው፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው በአጠቃላይ መምህራንን በሚመለከት ለቀረበላቸው መጠይቆች አብዛኞቹ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ እንደሰጡና መምህራንም በትምህርት ዝግጅታቸውና በአቀራረባቸው ተማሪዎችን ለመርዳት ጥረት እንደሚያደርጉ የሚያመለክት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ መለኪያ ስር በቀረቡ መጠይቆች የተመዘገበው አማካይ ውጤት 3.19 መሆኑን የተማሪዎች አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን ያመለክታል፡፡

#### 4.1.2.1 የተጠቃለለ የተማሪዎች አመለካከት ውጤት

ከዚህ በላይ በአምስቱም መለኪያዎች ስር በዝርዝር በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ መሠረት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለሚጀምርበትና ለሚያበቃበት የክፍል ደረጃ ያላቸው አመለካከት፣ ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው እይታ፣ የሁለተኛ ቋንቋ አጠቃቀም ስለሚያሳድርባቸው ተጽእኖ፣ በመማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ ላይ ያላቸው አመለካከትና በቋንቋ መ/ራን የትምህርት አሰጣጥ ላይ ያላቸው አመለካከት በአምስቱም መለኪያዎች ከፍሎ ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ የአመለካከት መለኪያ የተመዘገበውን ውጤት ጠቅለል በማድረግ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

**መለኪያ አንድ፡-** ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለሚጀምርበትና ስለሚያበቃበት የክፍል ደረጃ በሚመለከት ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ሲሆን የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት **2.86 ነው፡፡**

**መለኪያ ሁለት**፡- ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው እይታ በሚመለከት ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ያላቸው አመላከት አዎንታዊ ሲሆን የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት 2.92 **ነው**፡፡

**መለኪያ ሶስት**፡- ተማሪዎች የቋንቋው የአነጋገር ስልት/ንበት/ሰለሚያሳድርባቸው ተጽእኖ በሚመለከት ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ሲሆን የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት 2.83 **ነው**፡፡

**መለኪያ አራት**፡- ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀትና አቀራረብን በሚመለከት ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ላይ ያሳዩት አመለካከት አዎንታዊ ሲሆን የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤትም 2.95 **ነው**፡፡

**መለኪያ አምስት**፡- ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ መ/ራን ትምህርት አሰጣጥን በሚመለከት በቀረበላቸው መጠይቅ ላይ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ሲሆን የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት 3.19 ነው፡፡

የሁሉም መለኪያዎች የተጠቃለለ የአመለካከት አማካይ ድምር ውጤት 2.95 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በመጨረሻም ከዚህ ከተጠቃለለ አማካይ ውጤት ላይ የተደረሰው እያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ በአስራ አምስቱ መጠይቆች ያስመዘገበው ድምር ውጤትና በእያንዳንዱ መጠይቅ ላይ አንድ መቶ ተማሪዎች ያስመዘገቡት የአመለካከት አማካይ ውጤትን በማስላት ነው፡፡ እንደ ውጤቱ በዳውሮ ዞን ቶጫ ወረዳ ቶጫ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ አፋቸውን በዳውሮኛ ቋንቋ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ መሠረት ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በጥናቱ የተገኘው አጠቃላይ ድምር አማካይ ውጤት 2.95 መሆኑ በሁሉም ተጠኚዎች ዘንድ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

ይህንን ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ለመለካት የተጠቀምነው ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ ከላይ የተገለጸው ውጤት የተገኘውም በዚህ መጠይቅ አማካይነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለተመዘገበው ውጤት ትክክለኛነት በአገልግሎት ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አመለካትን ለመለካት አስተማማኝ ስለመሆኑ ተፈትሾ ሊረጋገጥ

ይገባል፡፡በመሆኑም የመጠይቁ አስተማማኝነት ቀደም ብሎ በትልመ ጥናት ወቅት ቀርቦ ተገቢነቱ ተገምግሞ በዚያ ላይ ውስን ማሻሻያ ተደርጎበት ለዋናው ጥናት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም የመጠይቁ አስተማማኝነት እንደገና አሁን ከተመዘገበው ውጤት በመነሳት "የኩዶር ሪቻርድሰን የመጠይቅ አስተማማኝነት መፈተኛ ቀመር '21'" መሠረት ሲሰላ የሚከተለውን ውጤት ያስገኛል፡፡

$$\frac{N}{N-1}\left(\frac{1-X(N-X)}{N(SX)}\right)$$ (ሜህሪንስና ሌህማን(1991)

ምልክቶች ውክልና

N = የጥያቄዎች ብዛት /15 X 5/

X = አማካይ ውጤት /45.5100/

SX = መደበኛ ልይይት /8.63455/

በዚህ ቀመር መሠረት እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

$$= \frac{75}{74}\left(\frac{1-45.5100(75-45.5100)}{75(8.63455)2}\right)$$

$$= \frac{75}{74}\left(\frac{1-45.5100(29.49)}{75(74.555)}\right)$$

$$= \frac{75}{74}\left(\frac{1-1342.0899}{5591.625}\right)$$

$$= \frac{75}{74}(1-024001)$$

$$= 1.01351(0.75999)$$

$$= 0.77$$

ይህ ውጤት የቀረበው መጠይቅ 0.77 የሆነ ከፍተኛ የአስተማማኝነት ብቃት እንዳለው ያሳያል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው አስተማማኝ መሆን ደግሞ የተሰበሰበው መረጃና

የተገኘው የተማሪዎች የአመለካከት ውጤትም አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

### 4.1.3 ከተማሪዎች የጽሑፍ ፈተና የተገኘ ውጤት ትንተና

የተማሪዎች አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና ለመፈተሽ ከአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅቶና የፈተናው ተገቢነትም በሚመለከታቸው አካላት ታይቶ ተገቢ ስለመሆኑ ተረጋግጦ የቀረበላቸውን ፈተና ከአስረኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በእጣ ንሞና /Random sampling/ ንሞና ዘዴ የተመረጡ 45 ወንድ ተማሪዎችና 55 ሴት ተማሪዎች በድምሩ 100 ተማሪዎች የተፈተኑ ሲሆን የተገኘው ውጤትም ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ 6 ፣ሠንጠረዥ 7፣ ሠንጠረዥ 8፣ ሠንጠረዥ 9 እና ሠንጠረዥ10 ተብሎ እንደ ጥያቄው ዓይነት በአምስት ምድብ ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ በመጀመሪያው ሠንጠረዥ የተለያየ ዓይነት 20 ጥያቄዎች፣ በሁለተኛው ሠንጠረዥ ስለ ምሳሌያዊ አነጋገር የሚጠይቁ 5 ጥያቄዎች፣ በሶስተኛው ሠንጠረዥ ስለቃላት ትርጉም ያላቸውን ችሎታ የሚፈትሹ 5 ጥያቄዎች፣ በአራተኛው ሠንጠረዥ ስለፈሊጣዊ አነጋገሮች ለመፈተሽ የቀረቡ 5 ጥያቄዎችና በአምስተኛው ሠንጠረዥ ላይ ደግሞ የተቃርኖ መልስ እንዲሰጡ ተፈልጎ የቀረቡ 5 ጥያቄዎችን ናቸው፡፡ የጠቅላላ ጥያቄዎች ብዛት በድምሩ 40 ነው፡፡ ይህም ወደ መቶኛ ሲቀየር እያንዳንዱ ጥያቄ በ2.5 ተባዝቶ ይያዛል /40X2.5=100/፡፡ በዚህም አኳያ እያንዳንዱ ተጠኚ ያስመዘገበው መልስ በ2.5 ተባዝቶ የተገኘው ውጤት በሠንጠረዡ ውስጥ /በትክክል የተመለሰ/ በሚለው አምድ በጥያቄዎች ትይዩ ቁልቁል ሠፍሯል፡፡ የተገኘው ውጤት በእያንዳንዱ ሠንጠረዥ ስር ከ50% በላይና በታች ተብሎ ተተንትኗል፡

ሠንጠረዥ 6 የተለያየ ዓይነት 20 ጥያቄዎች ቀርቦላቸው የተሰጡ ምላሾች ትንተና

| ተ/ቁ | ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች | የተማሪዎች ምላሽ | | | | በትክክል የተመለሰ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ለ | ሐ | መ | |
| 1 | ቋንቋ ሥርዓታዊ ነው ስንል--- ማለታችን ነው፡፡ | 5 | 20 | 26 | 49 | **49** |
| 2 | የቋንቋ መሠረቱ --------ነው፡፡ | 39 | 25 | 15 | 21 | **39** |
| 3 | ጠንክሮመማር---------------ተግቶመስራት ያስከብራል፡፡ | 15 | 15 | 57 | 13 | **57** |
| 4 | ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ ሁለት ትርጉም የሚሰጡ ቃላት-- | 6 | 8 | 18 | 68 | **68** |
| 5 | አላፊ ጊዜን የሚያመለክተው አረፍተ ነገር የትኛው ነው፡፡ | 7 | 16 | 23 | 54 | **54** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ብዙ ታዳሚዎች በሠርጉ ተገኝተዋል፡፡ ለተሰመረበት ቃል ትርጉሙ --- | 11 | 13 | 8 | 68 | **68** |
| 7 | /እክስቷን ለመጠየቅ ወደ መቀለ ሄደች/የሐረጉ መሪ ቃል------ | 45 | 18 | 27 | 10 | **10** |
| 8 | /እንደ ወንድሟ ጎበዝ/ የዚህ ሐረግ ዓይነት----- ነው፡፡ | 39 | 24 | 11 | 26 | **39** |
| 9 | ግጥም ምን ዓይነት ግጥም እንደሆነ የሚታወቀው በ---------- ተለክቶ ነው፡፡ | 28 | 46 | 14 | 12 | **46** |
| 10 | የሰንኅ መገን ግጥም በየሐረጋቱ ስንት ቀለም ይይዛል? | 16 | 15 | 45 | 24 | **45** |
| 11 | ቀጥሎ ከቀረቡ ዐ.ነገሮች ውስጥ ተራ ዐ.ነገር የትኛ ነው? | 43 | 22 | 26 | 9 | **43** |
| 12 | በአንቀጽ ውስጥ ኃይለቃል---ነው | 15 | 24 | 14 | 47 | **47** |
| 13 | በላይነሽ የብርቱካን ጭማቂ አዘውትራ ትጠጣለች፡፡ የዚህ ዐ.ነገር ዓይነት -------ነው፡፡ | 41 | 12 | 12 | 35 | **41** |
| 14 | ከልቦለድ አላባውያን ውስጥ ታሪኩ የተፈፀመበትጊዜና ቦታ የሚገለፀው በ--------ነው፡፡ | 28 | 40 | 15 | 17 | **40** |
| 15 | አንድን ድርሰት ስንጽፍ በውስጡ ከሌላ ሰው የፈለቀውን ሀሳብ የተጠቀምን መሆኑን ለማመልከት የምንገለገለው ሥርዓት ነጥብ------- ይባላል፡፡ | 37 | 17 | 16 | 30 | **37** |
| 16 | የቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ስንል ----ማለታችን ነው፡፡ | 34 | 23 | 29 | 14 | **29** |
| 17 | ከሚከተሉት አንዱ በማዳመጥ መረጃን ለማግኘት ያስችላል፡፡ | 22 | 11 | 7 | 60 | **60** |
| 18 | ከሚከተሉት አንዱ የከንፈር ድምፅ ነው፡፡ | 53 | 10 | 12 | 25 | **53** |
| 19 | እሮሮ ማለት-----ማለት ነው፡፡ | 35 | 33 | 17 | 15 | **35** |
| 20 | እንደተናካሽ ውሻ እየተቅለበለበ የተናገረው ንግግር አጥንት ይሰብራል፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ በተነፃፃሪ ዘይቤነት የገባው ሐረግ ----የሚለው ነው፡፡ | 17 | 30 | 35 | 18 | **35** |

ከሠንጠረዥ 6 እንደምንረዳው የተለያየ ዓይነት ከ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጁ 20 ጥያቄዎች የተማሪዎች አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ይቻል ዘንድ ለተማሪዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከተሰጣቸው ከ20 ጥያቄዎች ውስጥ በሰባቱ ጥያቄዎች ከ50% በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆን አማካዩም 51.42 ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አማካይ ውጤት በዚህ ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች በቂና አርኪ ውጤት ነው ለማለት አያስችልም ምክንያቱም የተመዘገበው አማካይ ውጤት 51.42 ነው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በቀሪዎቹ አስራ ሶስት የፈተና ጥያቄዎች ያስመዘገቡት ከ50%

በታች የሆነ ውጤት ነው፡፡ በሁሉም 20 ጥያቄዎች የተመዘገበው አማካይ የፈተና ውጤትም 41.15 ነው፡፡ በዚህም አማካዩ 41.15 ይሁን እንጂ በአንዳንድ ጥያቄዎች ላይ በሁሉም ተማሪዎች 10% ምላሽ ተመዝግቧል፡፡

ሠንጠረዥ 7 ከምሳሌያዊ አነጋገሮች ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄች ትንተና

| ተ/ቁ | ለተማሪ የቀረቡ ጥያቄዎች | የተማሪ ምላሾች | | | | በትክክል የተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ለ | ሐ | መ | |
| 21 | ድመት መንኩሳ------------ | 34 | 26 | 21 | 19 | **21** |
| 22 | ፈረሰኛ የወሰደውን---------- አይመልሰውም፡፡ | 44 | 24 | 10 | 22 | **24** |
| 23 | አህያን ፈርቶ-------------- ይመታል፡፡ | 20 | 44 | 16 | 20 | **44** |
| 24 | አለባብሰው ቢያርሱ---------- | 25 | 33 | 22 | 20 | **33** |
| 25 | ሲሮጡ የታጠቁት -------------ይፈታል፡፡ | 17 | 19 | 42 | 22 | **42** |

ከሠንጠረዥ 7 እንደምንረዳው ተማሪዎች በተጠቀሰው ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተካትተው የቀረቡ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ይጠቀማሉ ወይ? የሚለውን ለመለየት ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ከሁለም ተጠኚ ተማሪዎች ዘንድ የተመዘገበው አማካይ የፈተና ውጤት ከ50% በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በፈተና ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 32.8% ነው፡፡ይህም ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን በሚጠቀሙበት ወቅት ሀሳባቸውን አሳጥረውና እጅግ ቀለል አድርገው ለሰሚው አጣፍጠው በግልጽ ለማቅረብ የሚችሉበት የቋንቋ አጠቃቀማቸው ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ የተመዘገበው የፈተና ውጤት ቀደም ሲል ከተመዘገበው ከአመለካከት አማካይ ውጤት ጋር የሚዛመድና ለጥናቱ መሪ ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ የሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 8 በትርጉም የማይገናኘውን እንዲለዩ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ትንተና

| ተ/ቁ | ለተማሪ የቀረቡ ጥያቄዎች | የተማሪ ምላሾች | | | | በትክክል የመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ለ | ሀ | መ | |
| 26 | ሀ/ውበት ለ/ደም ግባት ሐ/ቁንጅና መ/እርድና | 18 | 32 | 13 | 37 | **37** |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 27 | ሀ/ውህደት ለ/ውጥረት ሐ/ህብረት መ/ጥምረት | 11 | 26 | 23 | 40 | **26** |
| 28 | ሀ/ጉልምስና ለ/እርግና ሐ/ሽምግልና መ/እርጅና | 35 | 24 | 21 | 20 | **35** |
| 29 | ሀ/ጅል ለ/ልል ሐ/ሞኝ መ/ቂል | 27 | 31 | 16 | 26 | **31** |
| 30 | ሀ/ከነዳ ለ/ለካ ሐ/ከተረ መ/መተረ | 25 | 23 | 17 | 35 | **35** |

ከሠንጠረዥ 8 እንደምናየው የተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለማረጋገጥ በሚል ታሳቢ ተደርጎ በትርጉም የማይገናኘውን እንዲለዩ በቀረበላቸው ፈተና በሁሉም ተማሪዎች ዘንድ የተመዘገበው ውጤት ከ50% በታች ሲሆን አማካዩም 32.8% ነው ፡፡

ሠንጠረዥ9 ከፈሊጣዊ አነጋገሮች ተዘጋጅተው ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች ትንተና

| ተ/ቁ | ለተማሪ የቀረቡ ጥያቄዎች | የተማሪ ምላሾች | | | | በትክክል የተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ለ | ሐ | መ | |
| 31 | ሀሞቱ ፈሰሰ -------- ሀ/ሰነፈ ለ/ሀሞቱ ተደፋበት ሐ/ ወኔው ተቀሰቀሰ መ/ጀግንነት ተሰማው | 21 | 34 | 20 | 25 | **21** |
| 32 | ሐረግ መዘዘ--- ሀ/ሐረግ ቆረጠ ለ/ሐረግ ጠቀለለ ሐ/ ዘር ቆጠረ መ/ሐረግ ሳበ | 12 | 31 | 27 | 30 | **27** |
| 33 | ሆደባሻ-------- ሀ/አኩራፊ / በቶሎ የሚቀየም ሐ/ ቦርጫም መ/ሀ እና ለ | 20 | 20 | 21 | 39 | **39** |
| 34 | መቀስ አፍ--- ሀ/ምላሱ መቀስ የሆነ ለ/ነገረኛ ሐ/ ምላሱ ፀጉር የሚቆርጥ መ/አኩራፊ | 17 | 41 | 23 | 19 | **41** |
| 35 | ባፍንጫዬ ይውጣ--- ሀ/ይቅርብኝ ለ/አልፈልግም ሐ/አንገሽግሾኛል መ/ሁሉም | 17 | 23 | 13 | 47 | **47** |

በሠንጠረዥ9 ላይ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተካትተው ከሚገኙ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ውስጥ የተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም አቅማቸው ምን ያህል እንደሆነ ለመፈተሽና

ከአመለካከታቸው ጋር ያለውን ቁርኝት ለመለየት ታስቦ 5 የፈሊጣዊ አነጋገር ጥያቄዎች ቀርቦላቸዋል፡፡ በዚህ ጥያቄ ከሁሉም ተፈታኞች ዘንድ የተመዘገበው ውጤት ከ50% በታች ነው፡፡ በዚህኛው ጥያቄ ስር የተገኘው የፈተና አማካይ ውጤት 35% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

ሠንጠረዥ10 ተቃራኒ ፍቺ ያለውን ቃል እንዲለዩ ለቀረበ ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ትንተና

| ተ/ቁ | ለተማሪ የቀረቡ ጥያቄዎች | የተማሪ ምላሽ | | | | በትክል የተመለሱ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ለ | ሐ | መ | |
| 36 | ዕድገት ሀ/ለውጥ ለ/ድቀት ሐ/ ሥላጣኔ መ/ልማት | 20 | 22 | 20 | 38 | **22** |
| 37 | ባላንጣ ሀ/ባላጋራ ለ/ደመኛ ሐ/ወዳጅ መ/ጠላት | 27 | 26 | 20 | 27 | **20** |
| 38 | መፈንደቅ ሀ/መፍነክነክ ለ/መሞላቀቅ ሐ/መፍለቅለቅ መ/ መተከዝ | 18 | 26 | 22 | 34 | **34** |
| 39 | ጦሰኛ ሀ/ቀልደኛ ለ/ትዕቢተኛ ሐ/ጠንቀኛ መ/ነገረኛ | 21 | 21 | 22 | 36 | **21** |
| 40 | ደግ ሀ/ርህሩህ ለ/የዋህ ሐ/ገር መ/ክፉ | 15 | 21 | 13 | 51 | **51** |

በሠንጠረዥ10 ላይ ተማሪዎች ከቀረቡላቸው አማራጮች ውስጥ ተቃራኒ የሆነውን ለይተው እንዲመዘግቡ ተጠይቀዋል፡፡ በዚህም ከቀረቡ 5 ጥያቄዎች መካከል ተማሪዎች በአንዱ ጥያቄ ብቻ ከ50% በላይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በዚህ ጥያቄ የተመዘገበው አማካይ ውጤት 51% ሲሆን በቀሪዎቹ ጥያቄዎች ሁሉም ተፈታኞች ከ50% በታች የሆነ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ አማካይ ውጤትም 29.6% ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 11 የእያንዳንዱ ተጠኚ የአመለካከት ና የፈተና ውጤት**

| ተ/ቁ | የአመለካከት ውጤት | የፈተና ውጤት | ተ/ቁ | የአመለካከት ውጤት | የፈተና ውጤት | ተ/ቁ | የአመለካከት ውጤት | የፈተና ውጤት | ተ/ቁ | የአመለካከት ውጤት | የፈተና ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **1** | 0.85 | 25 | **26** | 1.56 | 37.5 | **51** | 2.43 | 55 | **76** | 2.16 | 47.5 |
| **2** | 2.24 | 45 | **27** | 1.13 | 27.5 | **52** | 2.14 | 50 | **77** | 1.16 | 25 |
| **3** | 1.20 | 27.5 | **28** | 3.06 | 72.5 | **53** | 1.06 | 27.5 | **78** | 1.44 | 35 |
| **4** | 1.79 | 40 | **29** | 2.24 | 50 | **54** | 2.06 | 42.5 | **79** | 2.01 | 55 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **5** | 1.38 | 27.5 | **30** | 1.77 | 47.5 | **55** | 1.16 | 22.5 | **80** | 1.55 | 35 |
| **6** | 1.04 | 20 | **31** | 2.20 | 47.5 | **56** | 2.34 | 60 | **81** | 1.49 | 40 |
| **7** | 1.09 | 20 | **32** | 1.32 | 30 | **57** | 2.41 | 55 | **82** | 1.37 | 30 |
| **8** | 1.03 | 30 | **33** | 2.25 | 55 | **58** | 1.42 | 35 | **83** | 2.37 | 60 |
| **9** | 0.88 | 25 | **34** | 1.92 | 40 | **59** | 2.40 | 57.5 | **84** | 2.09 | 47.5 |
| **10** | 1.44 | 30 | **35** | 1.98 | 55 | **60** | 1.69 | 37.5 | **85** | 1.04 | 27.5 |
| **11** | 1.25 | 22.5 | **36** | 3.15 | 70 | **61** | 2.27 | 40 | **86** | 0.91 | 20 |
| **12** | 1.71 | 37.5 | **37** | 3.08 | 75 | **62** | 2.50 | 60 | **87** | 2.07 | 45 |
| **13** | 0.93 | 22.5 | **38** | 2.45 | 62.5 | **63** | 1.67 | 40 | **88** | 1.57 | 32.5 |
| **14** | 1.14 | 27.5 | **39** | 1.83 | 47.5 | **64** | 1.50 | 40 | **89** | 0.45 | 10 |
| **15** | 1.32 | 30 | **40** | 1.62 | 40 | **65** | 1.58 | 32.5 | **90** | 1.12 | 30 |
| **16** | 1.33 | 27.5 | **41** | 2.29 | 47.5 | **66** | 1.99 | 45 | **91** | 1.54 | 45 |
| **17** | 1.17 | 22.5 | **42** | 2.30 | 52.5 | **67** | 1.70 | 35 | **92** | 2.77 | 67.5 |
| **18** | 1.33 | 35 | **43** | 2.23 | 52.5 | **68** | 1.72 | 40 | **93** | 0.69 | 15 |
| **19** | 2.16 | 52.5 | **44** | 1.42 | 30 | **69** | 2.04 | 45 | **94** | 1.04 | 22.5 |
| **20** | 2.27 | 52.5 | **45** | 1.68 | 32.5 | **70** | 0.84 | 15 | **95** | 1.12 | 25 |
| **21** | 2.04 | 45 | **46** | 1.26 | 30 | **71** | 1.90 | 50 | **96** | 1.60 | 42.5 |
| **22** | 1.25 | 27.5 | **47** | 1.68 | 32.5 | **72** | 1.20 | 27.5 | **97** | 1.28 | 27.5 |
| **23** | 1.26 | 25 | **48** | 1.48 | 35 | **73** | 1.46 | 32.5 | **98** | 1.34 | 37.5 |
| **24** | 1.38 | 27.5 | **49** | 1.10 | 22.5 | **74** | 2.39 | 57.5 | **99** | 0.92 | 30 |
| **25** | 1.62 | 32.5 | **50** | 0.95 | 20 | **75** | 2.03 | 45 | **100** | 2.31 | 57.5 |

በሠንጠረዥ 11 አጠቃላይ 100 ተጠኚ ተማሪዎች በነፍስ ወከፍ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት ለመለየት በቀረበላቸው 15 የጽሑፍ መጠይቆችና በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም የሚያስመዘግቡትን ውጤት ለመለካት በቀረበላቸው ፈተና ያስመዘገቡት ነጥብ አንድ ላይ ተካቶ ቀርቧል፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚው የእያንዳንዱን ተጠኚ የአመለካከትውጤትና የፈተና ውጤት ተዛምዶን በተናጠል በ spss የተዛምዶ ቀመር ስልት ለመለካት እጅግ ሠፊ ጊዜና ብዙ ማቴሪያል ስለሚጠይቅ የመቶ ተማሪዎች አማካይ የአመለካከትና ፈተና ውጤት በመውሰድ 0.955 የሆነ የተዛምዶ ውጤት አግኝቷል፡፡ ነገር ግን በእያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ የተመዘገበው ይህ የአመለካከትና የፈተና ውጤት በሠንረዥ ሠፍሮ መቅረቡ አስፈላጊ ሊሆን ስለሚችል በዚህ መልኩ ቀርቧል፡፡

### 4.1.4 የአመለካከትና የፈተና ውጤት ተዛምዶ

ባጠቃላይ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር በንጽጽር ሲታይ ተስማሚ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተዛምዶ ስልት ቀመር /Correlation/ በ spss soft ware ሲሰላ የአጠቃላይ ተማሪዎች

የፈተና ውጤት ከአመለካከታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ እርስ በርሱ የማይቃረንና የሚዛመድ መሆኑን ከጥናቱ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህ ትንታኔ ውስጥ የፈተና ውጤት በቀጥታ ተማሪዎች በመማር ላይ ከሚገኙበት ከአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ የተሰጠ ሲሆን የአመለካከቱ ደግሞ 100ዎቹ ተማሪዎች ለ15 የጽሑፍ መጠይቆች በተናጠል ያስመዘገቡት ውጤት በአንድ ላይ ተደምሮ አማካይ ነጥብ ተወስዷል፡፡ የተገኙ ውጤቶቹ በተዛምዶ ቀመር ስልት እንደሚከተለው ተሰልተዋል፡፡

የተዛምዶ ቀመር $r=\frac{\sum XY-[\sum X\sum Y]}{\sqrt{[\sum X^2-\frac{(\sum x)^2}{n}[\sum Y^2-\frac{(\sum y)^2}{n}]}}$

x - የተማሪዎች አመለካከት ውጤት

y- የተማሪዎች ፈተና ውጤት

n - የተጠኚዎች ብዛት

$\sum X$=166.32, $\sum Y$= 3847.5

n=100

$\sum XY$=7128.43,

$\sum X^2$=307.72 $\sum Y^2$=166781.3

$$r=\frac{\sum XY-[\sum X\sum Y]}{\sqrt{[\sum X^2-\frac{(\sum x)^2}{n}[\sum Y^2-\frac{(\sum y)^2}{n}]}}$$

$$r=\frac{7128.43-(166.32*3847.5)}{\sqrt{[307.72-\frac{(166.32)^2}{100}]*[166781.3-\frac{(3847.5)^2}{100}]}}$$

r= **0.955**

የተማሪዎች አጠቃላይ አመለካት አማካይ ውጤትና የፈተና አማካይ ውጤት አንድ ላይ በspss ቀመር ስልት ተሰልቶ **0.955** የተዛምዶ ውጤት አሳይቷል፡፡ ለተጨማሪ /አባሪ 4 ይመልከቱ/፡፡ ይህም የተዛምዶ ውጤት በአመለካከታቸውና በፈተና ውጤታቸው መካከል ከፍተኛ ፋይዳ ወይም የጎላ ተዛምዶ ያለውን ጥምረት ያሳየ መሆኑን በጥናቱ ከተገኘው ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ውጤቱ በግልፅ የሚያመለክተው በተማሪዎቹ አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ከፍተኛ ተዛምዶ መኖሩን ነው፡፡ በዚህም የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ያገኙ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.1.5 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አፋቸውን በዳውሮኛ ቋንቋ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ አለው ወይስ የለውም የሚለውን መፈተሸ ሲሆን ጥናቱን ከግብ ለማድረስም አጥኚው የተለያዩ ዘዴዎችና መሳሪያዎችን ተጠቅሟል፡፡ በዚህ ጥናት በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳናት ውስጥ ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ ጥሩ አመለካከት ካላቸው በፈተና ጥሩ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ እንዲሁም አመለካከታቸው ጥሩ ካልሆነ ደግሞ ዝቅተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ምሁራን በጥናታቸው ማረጋገጣቸው ተገልፆአል (Gardner:1985)፡፡

በዚህ ጥናትም ከላይ የቀረቡት ሀሳቦች ትክክለኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ጥናቱ እንዳረጋገጠው ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምንም እንኳ ከተመዘገበው ውጤት አኳያ አዎንታዊ ቢሆንም ዝቅተኛ ነው፡፡ በአማርኛ ቋንቋና በትምህርቱ ላይ ለተማሪዎች ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለመፈተሸ እንደ መመዘኛ በቀረቡት መለኪያዎች ማለትም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለሚጀምርበትና ስለሚያበቃበት ክፍል ደረጃ 2.86 አማካይ ውጤት ፣ በቋንቋው ላይ ስላላቸው ጉጉትና ተሳትፎ፣ ወደፊት በቋንቋው ላይ ስላላቸው ፍላጎትና ስሜት ፣በሚያስመዘገቡት ውጤት ላይ ስላላቸው እርካታ ተማሪዎች 2.92 የሆነ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው የተጠናቀረው መረጃ ይጠቁማል /ሠንጠረዥ "1" እና "2"ን ይመልከቱ/፡፡ ተማሪዎቹ በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱና የቋንቋውን የአነጋገር ስልትና ባህል ለምደው ያደጉ እንደ መሆናቸው ይህ አፍ የፈቱበት ቋንቋ በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ ይኖር እንደሆነ እንዲሁም ከዚህ ጋር በተያያዘ የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለማረጋገጥ በሚጠይቀው መለኪያ ስር በቀረበላቸው መጠይቅ አማካይነት አመለካከታቸው አዎንታዊ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በነዚህ መጠይቆች ላይ የተመዘገበው የአመለካከት አማካይ ነጥብ 2.83 ውጤቱ አዎንታዊ እንደሆነ ያመለክታል /ሠንጠረዥ "3"ን /ይመልከቱ፡፡

በመለኪያ አራት ስር የመማሪያ መጽሐፍን አስመልክቶ በቀረበላቸው መጠይቅ የተመዘገበው የአመለካከት አማካይ ውጤት 2.95 ነው /ሠንጠረዥ "4"ን/ ይመልከቱ፡፡ ውጤቱ አዎንታዊ ቢሆንም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህም የመማሪያ መጽሐፍ ቀለል ተደርጎና የአካባቢያቸውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ቢዘጋጅ በታላሚው ቋንቋ ላይ ያላቸው የአጠቃቀም አቅም ሊሻሻል እንደሚችል የተመዘገበው ውጤት ያስነዝባል፡፡

በመለኪያ አምስት ስር የመምህራን የትምህርት አሰጣጥን በሚመለከት ለቀረበላቸው መጠይቆች 3.19 የሆነ አዎንታዊ አመለካከት ተመዘግቧል፡፡ ይህም አብዛኞቹ ተማሪዎች የአስተማሪዎቻቸው የትምህርት አሰጣጥ በቋንቋ ትምህርት ላይ ባላቸው አመለካከት ውስጥ ተጽእኖ እንደሌለው የሚያመለክት መሆኑን ያሳያል ሠንጠረዥ "5"ን ይመልከቱ፡፡ ይህንን ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ለመለካት የተጠቀምነው ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ ከላይ የተገለጸው ውጤት የተገኘውም በዚህ መጠይቅ አማካይነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለተመዘገበው ውጤት ትክክለኛነት በአገልግሎት ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አመለካትን ለመለካት አስተማማኝ ስለመሆኑ ተፈትሾ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡በመሆኑም የመጠይቁ አስተማማኝነት ከተመዘገበው ውጤት በመነሳት "የኩዶር ሪቻርድስ የመጠይቅ አስተማማኝነት መፈተኛ ቀመር '21'" መሠረት ተሰልቶ 0.77 የሆነ ውጤት በማስገኘቱ አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም ከመለኪያ 1-5 ድረስ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለማረጋገጥ ከቀረቡ መጠይቆች የተገኘው ውጤት ከጥናቱ ርዕስ አኳያ ከፈተና ውጤታቸው ጋር ዝምድና መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ተማሪዎቹ በመማር ላይ ከሚገኙበት የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ የተዘጋጀና 40 ጥያቄ የያዘ የጽሑፍ ፈተና ተሰጥቷቸው 38.65% የሆነ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ በዚህም የዳውሮኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ከሁለቱ ተላዋዋጮዎች የተገኘው ውጤት በ spss የተዛምዶ ቀመር ስልት ተሰልቶ 0.955 የሆነ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ጥምረት አስገኝቷል፡፡ ይህም ለጥናቱ መሪ ጥያቄና ለጥናቱ ዋና ዓላማ ትክክለኛ ምላሽ አስገኝቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5.ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ፣ ግኝትና የመፍትሔ ሀሳቦች

በዚህ የጥናት ክፍል የጥናቱ ማጠቃለያ ፣ መደምደሚያ፣ የጥናቱ ግኝትና አስተያየቶች ይቀርባሉ

### 5.1 ማጠቃለያ

ለዚህ ጥናት መካሄድ መነሻ ነጥብ የሆነው "በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ይኖረው ፍተሻ" የሚለው ነው ፡፡ ይህንን የጥናቱ ዋና ዓላማን መሠረት በማድረግ በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ሲሆን ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በዳውሮ ዞን ቶጫ ወረዳ የቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

ተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለሚጀምርበትና ለሚያበቃበት የክፍል ደረጃ ፣ለቋንቋው ያላቸው ጉጉት፣ ተሳትፎ ፣ በቋንቋው ላይ ወደፊት ስላላቸው ተስፋና በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ ስላላቸው እርካታ፣ ለመማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ትምህርት አሰጣጥ ላይ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለመለካትና ይህም አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ የጽሑፍ መጠይቆች እንዲሞሉና ከክፍሉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጁ ፈተናዎችን እንዲፈተኑ ተደርገዋል፡፡ የተመዘገበው የአመለካከት አማካይ ውጤትና የፈተና አማካይ ውጤት በመካከላቸው ተዛምዶ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በተዛምዶ ቀመር ስልት /spss/ ተሰልቶ 0.955 የሆነ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው የተዛምዶ ጥምረት ተገኝቷል፡፡

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ ከግብ ላይ እንዲደርስ በመጠይቆቹ አማካይነት መልስ የሚፈልጉ ዝርዝር የጥናቱ መሪ ጥያቄዎችም የሚከተሉ ናቸው፡፡

- በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ ይኖረው ይሆን?
- አመለካከት የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት ውጤት የመተንበይ ድርሻ ይኖረው ይሆን?
- የትምህርቱ አቀራረብና የማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች ለትምህርቱ ባላቸው አመለካከት ላይ ተጽእኖ አሳድሮ ይሆን?

የሚለውን የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች /Basic Research Questions/ መሠረት አድርጎ ጥናትና ምርምሩ ተካሂዷል፡፡ እነዚህን የመነሻ ጥያቄዎችና ዝርዝር ዓላማዎችን ለመፈተሽና ለመተንተን በቅድሚያ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለሚጀምርበትና ስለሚያበቃበት የክፍል ደረጃ፣ በቋንቋው ላይ ስላላቸው ጉጉት ተሳትፎ የውጤት እርካታ፣ በቋንቋው አነጋገር ስልት/ንበት/፣ በመማሪያ መጽሐፍ አቀራረብና በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ትምህርት አሰጣጥ ላይ ያላቸውን አመለካከት እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለተማሪዎቻቸው ያላቸውን አስተያየት መለየት ነበር፡፡ በዚህም መሠረት በሊከርት የአፃፃፍ ስልት በቀረቡት መጠይቆች ላይ እያንዳንዱ ተማሪ በአስራ አምስቱ ጥያቄዎች ያስመዘገበው ውጤት እንዲሁም አንድ መቶ ተማሪዎች በእያንዳንዱ መጠይቅ ያስመዘገቡት የአመለካከት አማካይ ውጤት ተለይቷል፡፡ መጠይቁን የሞሉ መቶ ተማሪዎች ከቀረበላቸው አምስቱ መለኪያዎች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለሚጀምርበትና ስለሚያበቃበት የክፍል ደረጃ 2.86 የሆነ አማካይ ነጥብ በማስመዝገብ አዎንታዊ አመለካከት አሳይተዋል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ስላላቸው ጉጉት፣ስለሚያደርጉት ተሳትፎ፣ ስለሚያስመዘግቡት ውጤትና በትምህርቱ ላይ ወደፊት ስላላቸው ፍላጎት በሚመለከት ለቀረበላቸው መጠይቅ 2.92 አማካይ ውጤት በማስመዝገብ አዎንታዊ አመለካከት አሳይተዋል፡፡ ስለአማርኛ ቋንቋ የአነጋገር ስልት፣ አፍ የፈቱበት ቋንቋ የአነጋገር ስልትና የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ በሚመለከት ለቀረበላቸው መጠይቅ 2.83 አማካይ ውጤት በማስመዝገብ የአፍ መፍቻ ቋንቋና የታላሚው ቋንቋ የአነጋገር ስልት የርስ በርስ ግጭት በቋንቋ አጠቃቀም ወቅት ጫና ቢኖርም ለቀረበው መጠይቅ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በሌላም በኩል ስለ አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ (2.95) አማካይ ነጥብ በማስመዝገብ አዎንታዊ አመለካከት አሳይተዋል፡፡ ስለ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ (3.19) አማካይ ነጥብ በማስመዝገብ የመምህራን የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ብዙም ጫና እንደሌለው ስለአስተማሪዎቻቸው ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የእነዚህ መለኪያዎች የተጠቃለለ አማካይ ውጤት 2.95 ሲሆን ውጤቱም የተማሪዎች አመለካከት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ከተማሪዎች የተገኘው ውጤት ከፍ ሲል ለቀረቡ ለጥናቱ መሪ ጥያቄዎች መልስ አስገኝቷል፡፡

የአመለካከትና የፈተና ውጤት ንፅፅርን በሚመለከትም የጥናቱ ዋና ክፍል የሆነውን የተማሪዎች አመለካከትና ውጤት ተዛምዶ ለመፈተሽ ከተማሪዎች በተገኘ የአመለካከትና ፈተና ውጤት መካከል ያለው ጥምረት በተዛምዶ ቀመር ስልት ተሰልቷል፡፡ የተማሪዎች የአመለካከት አማካይ ውጤትና የፈተና አማካይ ውጤት ተዛምዶ ሲፈተሽ ከፍተኛ የሆነ ጥምረት ያስገኘ በመሆኑ በተማሪዎቹ አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ከፍተኛ ተዛምዶ መኖሩን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ የጥናቱ ማጠቃለያ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ዝቅተኛ የሆነ አዎንታዊ አመለካከት ዝቅተኛ ከሆነ የፈተና ውጤት ጋር ተዛምዷል ለማለት አስችሏል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ተማሪዎች በሁለቱም ተለዋዋጮች /በአመለካከትና በፈተና/ ያስመዘገቡት ነጥብ ለጥናቱ የሚጠበቀውን ውጤት አስገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት በተጠኚዎቹ አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ከፍ ያለ ተዛምዶ መኖሩን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ የተገኘው ውጤት "ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ ይኖረው ይሆን?" የሚለው የጥናቱ መሪ ጥያቄ ትክክል መሆኑን ጥናቱ በቀጥታ አረጋግጧል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ተጠኚ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ሲሆን በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመዘገበው የፈተና ውጤትም የተዛምዶ ግንኙነት ማድረጉን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ይህም በምዕራፍ ሁለት ስር በክለሳ ድርሳናት ላይ በአመለካከትና ውጤት መካከል ስላለው ዝምድና ስለማጥናታቸው ከተጠቀሱት ምሁራን ሥራዎች ጋር ተስማምቷል ለማለት የሚያስችል ነጥብ ላይ ደርሷል፡፡የተዛምዶ ቀመር ስሌትም ይህንን ያረጋግጣል፡፡

### 5.2 መደምደሚያ

በዚህ ጥናት ውጤት መሰረት የቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት አማካይ ውጤት 2.95 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ የተማሪዎቹ አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን ከማሳየቱም ባሻገር የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን የማሻሻል ጉጉትና ፍላጎት እንዳላቸውም ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ውጤት መሰረት የቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የፈተና ውጤት (38.65%) ሆኖ መገኘቱ በቁጥር ደረጃ ሲታይ ከአመለካከት አማካይ ውጤት የወረደና ዝቅተኛ ተደርጎ

ሊወስድ የሚችል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የፈተና ውጤት ተማሪዎች በትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊነቱ ከፍ የሚል ከሆነ ሊሻሻል እንደሚችል ያሳያል፡፡ በመጨረሻም በጥናቱ ውጤት ትንተና መሰረት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ መኖሩን፣ አመለካከታቸው በውጤታቸው ላይ በግልጽ የተንጸባረቀ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉና በመጠይቁ ውስጥ የተጠቀሱ ሀሳቦችን በመለየትና የመፍትሄ እርምጃ በመውሰድ የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ማሳደግ እንደሚቻል ጥናቱ ያስገነዝባል፡፡ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ በትምህርት ሂደታቸው ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ትምህርቶች ጨምሮ የራሱ የሆነ ተጽእኖ ማሳደር ይችላል፡፡ የትኛውም ተማሪ ቢሆን ትምህርቱን የሚማርበትን ቋንቋ በአግባቡ መጠቀም ካልቻለ በትምህርቱ የሚያስመዘግበው ውጤት በሚጠበቀው ልክ አይሆንም፡፡ ስለሆነም የቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ መኖሩ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን ሊወስኑ የሚችሉ ጉዳዮችንም መለየትና መፍትሄ መስጠት እንደሚገባ አሳይቷል፡፡ በሌላ መንገድ የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት በሌሎች በተለያዩ ተለዋዋጮች ሊወሰን የሚችል ቢሆን እንኳ የተማሪዎቹ የየራሳቸው አመለካከት የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ ከሁሉም በፊት አመለካከታቸው እጅጉን የተነቃቃ እንዲሆን ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች አመለካከትና በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ ትኩረት ሰጥተው በመስራት የሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ውጤትን ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲያድግ ማድረግ እንደሚችሉ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 5.3 የጥናቱ ግኝቶች

- የጥናቱን ዓላማ መነሻ በማድረግ ተማሪዎች ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅና ጽሑፍ ፈተና በሰጡት ምላሾች ትንተና እንዲሁም መምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሾች ትንተና ላይ በመመስረት በተካሄደው ጥናት አማካይነት የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ በዚህም መሠረት

1. በዳውሮኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ ይኖረው ይሆን?

ለሚለው ለጥናቱ መሪ ጥያቄ በአመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ባለው ተዛምዶ ላይ በተደረገው ፍተሻ ቀጥተኛ የሆነ ዝምድና መኖሩን የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል፡፡ በዚህም 0.955 የሆነ ከፍተኛ የተዛምዶ ጥምረት ተገኝቷል፡፡ ይህ በተማሪዎች የተመዘገበው የአመለካከት አማካይ ውጤትና የፈተና አማካይ ውጤት ዝምድና የሚያመለክተው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊ አመለካከት ማሳደራቸውን ነው፡፡ ይህም ለጥናቱ መሪ ጥያቄ በትክክል መልስ ያስገኘ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተጠኚ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር በቀጥታ የሚዛመድ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በጥናቱ የታቀፉ የሁሉም ተጠኚ ተማሪዎች 38.65 የሆነ ዝቅተኛ የፈተና ውጤት ተመዝግቧል፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያሳዩት የአመለካከት አማካይ ውጤት 2.95 ሲሆን ይህም ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በመካከላቸው ያለው ተዛምዶ በ"spss" ተዛምዶ ቀመር ተሰልቶ **0.955** መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል/አባሪ 4 ይመልከቱ/፡፡

2. አመለካከት የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት ውጤት የመተንበይ ድርሻ ይኖረው ይሆን? ለሚለው ለጥናቱ መሪ ጥያቄ ከተጠኚዎች የተገኘ ምላሽ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለሚጀምርበትና ስለሚያበቃበት የክፍል ደረጃ፣ ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው እይታን በሚመለከት፣ በአፌ-ፈትና ኢአፌ-ፈት ቋንቋዎች የአነጋገር ስልት/ንበት/ን በሚመለከትና በአጠቃላይ ከተላውጠ 1-5 ድረስ ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት 2.95 ሲሆን ውጤቱ ምንም እንኳ አዎንታዊ ቢሆንም ዝቅተኛ ነው፡፡በዚህም መነሻነት ተማሪዎች በሚማሩበት ክፍል ደረጃ ከሚገኝ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ በተሰጣቸው የጽሑፍ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት 38.65 ነው፡፡ይህም ዝቅተኛ ከሆነ አመለካከት የተገኘ ዝቅተኛ ውጤት በመሆኑ አመለካከት የተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ውጤት መተንበይ መቻሉን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡
3. የትምህርቱ አቀራረብና የማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች ለትምህርቱ ባላቸው አመለካት ላይ ተጽእኖ አሳድሮ ይሆን? ለሚለው የጥናቱ መሪ ጥያቄ በተላውጠ አራት ስር ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ አቀራብን በሚመለከት ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ሰጡት ምላሽ 2.95 ሲሆን በተላውጠ አምስት ስር በአማርኛ

ቋንቋ ትምህርት መምህራን የትምህርት አሰጣጥን በሚመለከት ለቀረበላቸው መጠይቆች የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት 3.19 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በሁለቱም መለኪያዎች የተመዘገበው ውጤት የተማሪዎች አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም በትምህርቱ አቀራረብ ላይ 2.05 በሆነ ነጥብ እና በመምህራን የትምህርት አሰጣጥ ስልት ላይ 1.81 በሆነ ነጥብ የተቃውሞ ድምጽ ተስተውሏል፡፡ ይህም በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተጽእኖ ማሳደር የሚችል መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡ ከነዚህ ውጤቶች በመነሳት የጥናቱ መሪ ጥያቄዎችና ዝርዝር ዓላማዎች ተገቢውን መልስ ማግኘት ችለዋል ፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማንም ከታለመለት ግብ ማድረስ ተችሏል፡፡

### 5.4 የመፍትሄ ሀሳቦች

ከጥናቱ ውጤቶች በመነሳት አጥኚው የሚከተሉትን መፍትሄ ሀሳቦች ያቀርባል፡፡

1. በጥናቱ ውጤት መሠረት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ይሁን እንጂ ያስመዘገቡት አማካይ ነጥብ 2.95 ዝቅተኛ ነው፡፡ እንዲሁም ከክፍሉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ በተሰጣቸው ፈተና ያስመዘገቡት ውጤትም 38.65 እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በዚህም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ስላላቸው አመለካከት አስተያት እንዲሰጡ ከቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቆች የተገኘ ውጤትና በፈተና ያስመዘገቡት ውጤት ሁለቱም በግልጽ ተዛምዶ አሳይተዋል፡፡ ስለዚህ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያሳዩት አመለካከትና በትምህርቱም የሚያስመዘግቡት ውጤት የተሻለ እንዲሆን ከት/ቤቱ ቋንቋ መ/ራንና ባለድርሻ አካላት ጀምሮ እስከ ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ድረስ ያሉት በሙሉ ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ የሚያሳዩት አመለካከት በቀጥታ በሚያስመዘግቡት ውጤት ጋር የሚንፀባረቅ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለቋንቋው የተሻለ አመለካከት እንዲኖራቸውና ትምህርቱ ከፍላጎታቸውና ከክፍል ደረጃቸው ጋር ግንኙነት ያለው ተስማሚ የሆነ ይዘት እንዲኖረው በማድረግ ምቹ የማስተማሪያ ስልት ቢቀይሱ የተሻለ ውጤት ሊመዘገብ ይችላል፡፡
2. ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ለተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው እንደመሆኑ መጠን ከፍላጎታቸው አኳያ በሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች በኩል ተጠንቶና ማሻሻያ ተደርጎ ትምህርቱ

የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ቢዘጋጅ የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀማቸውና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት የተሻለ ሊሆን ይችላል የሚል እምነቱ አለ፡፡

3. የቋንቋ አነጋገር ስልትን በሚመለከት ተማሪዎቹ ዳውሮኛ ቋንቋ አፈ-ፈት እንደመሆናቸው መጠን በሚማሩበት ወቅት ከአማርኛ ቋንቋ የአነጋገር ስልት ጋር ከመጋጨት ይልቅ እርስ በርሱ ተደጋጋፊ እንዲሆኑ ለማስቻል መ/ራን ከየትኛውም ባለድርሻ አካል ይልቅ ለተማሪዎች ቅርብ ስለሆኑ በመማር ማስተማር ወቅት ለችግሩ ትኩረት ሰጥተውና የማስተማሪያ ስልታቸውን በተማሪው ግንዛቤ ልክ ቢቀይሱና ከአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታና ከባህላቸው ጋር እያስተያዩ ቢያቀርቡ ለችግሩ መፍትሄ ማበጀት ይቻላል፡፡

4. ስለመማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ላሉበት ክፍል ደረጃ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ቀለል ተደርጎ በሚገባቸው ሁኔታ እንዳልተዘጋጀ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንም የሚመለከታቸው ክፍሎችና የሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ቋንቋው ከላይ ለተጠቀሱ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸው እንደመሆኑ መጠን መጽሐፉን ከልሰውና ለተማሪዎች በሚገባቸው መልኩ ማዘጋጀት እንዳለባቸው የሚጠቁም ነው፡፡ በመሆኑም የሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች የመማሪያ መጽሐፉን አቀራረብን ከተማሪዎች አስተያየት አንፃር መርምረው በማየት ከፍላጎታቸው፣ከአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታና ከክፍል ደረጃቸው ጋር ተቀራራቢ አድርገው ቢያቀርቡ በተማሪው አመለካከት ላይም ሆነ በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ የተፈለገው ለውጥ ሊመጣ ይችላል፡፡

4. ተማሪዎች ስለአስተማሪዎቻቸው የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ ተጠይቀው ከሰጡት ምላሽ ለማወቅ እንደተቻለው የቋንቋ መምህራን የትምህርት አሰጣጥ ባመዛኙ የተሻለ ነው፡፡ የአስተያየቱ አማካይ ነጥብ 3.19 ነው፡፡ ይህም በመ/ራን ትምህርት አሰጣጥ ላይ ስለቋንቋ ትምህርት የደረሰባቸው ጫና ብዙም እንዳልሆነ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለማብቃት እንደሚጥሩ በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ 44% የሚሆኑ ተማሪዎች ተቃውመዋል ስለዚህ መ/ራን የትምህርት አሰጣጣቸውን ሊመረምሩና በተማሪው ላይ የባህርይ ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ የማስተማር ስልታቸውን ሊቀይሱ ይገባል፡፡ በመሆኑም የመ/ራን ቁልፍ ድርሻ ከየትኛውም ነገር አስቀድሞ በእጃቸው ላይ በአደራ መልክ የተሰጡ

ተማሪዎችን በዕውቀት ማነጽና ኃላፊነት የሚሰማቸው አገር ተረካቢ ትውልድ አድርጎ መቅረፅ ስለሆነ መምህራን የማስተማር ስልታቸውን ከተማሪዎቻቸው ፍላጎት ጋር በሚጣጣም መልኩ መቀየስ እንደሚጠበቅባቸው ውጤቱ ይጠቁማል፡፡

5. በመጨረሻም የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ብቃት ከማጎልበት ረገድ የአማርኛ ቋንቋ ይህ ጥናት በተደረገበት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልልም ሆነ የፌደራል መንግስት የሥራ ቋንቋ እንደመሆኑ መጠን የነዚህ ተጠኚ ተማሪዎች አመለካከት በአማርኛ ቋንቋና በትምህርቱ ላይ የተሻለ እንዲሆን የሚመለከተው ክፍል ሊያጤንበት ይገባል፡፡

**ዋቢ መጻህፍት**


ባየ ይማም፡፡ (2000) "የአማርኛሰዋሰው" አዲስ አበባ፣ኃ.የተ.አሳታሚ ማህበር(የታተመ)

ታሪኬ ፋንታዬ ፡፡(1988) "በአዲስ አበባ ከ/ሁ/ደ/ት/ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በቋንቋዎች ተቋም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ታየ ገ/ማርያም ፡፡(1958) "የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ" ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት፡፡

አምሳሉ አክሊሉ፡፡(1976) "አጭር የኢትዮጵያ ስነፅሑፍ ታሪክ" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

አበበ ከበደ፡፡ (2003) "የመሠናደዶ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና"፡፡ አዲስ አበባ የኒቨርስቲ፣ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ኢዮብ ፀጋዬ፡፡ (2010) "በጅማ ዞን ሶኮሩ ወረዳ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት ትንተና" ጅማ ዩኒቨርስቲ፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)፡፡

ወንድወሰን በየነ፡፡ (1989) "የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የፈተናውጤታቸው ዝምድና፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡(2009)"የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር"(የታተመ)፡፡

ዮናስ አድማሱና ሌሎች፡፡ (1966) "አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ" አርትስ

ፋኩሊቲ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ(የታተመ)፡፡

ፀጋዬ አረጋይ ፡፡ (1996) “ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚኖራቸው አመለካከት ላይ ዝምድና ያላቸው ተላውጦች“ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንግስታዊ ባልሆኑ ት/ቤቶች የተካሄደ ጥናት፣ ለኤምኤ ዲግሪ መሚያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ወንድሙ ለማ እና ሙሉጌታ በዛብህ፡፡ (2003) የዳውሮ ህዝብ ታሪክ እስከ 1983 ዓ.ም ፡፡ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት

ዳዊት ፍሬሕይወት፡፡(2008) "አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በሆኑ የዶዶላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተሳታፊነት የተከናወነ ሙከራዊ ጥናት"

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

Aggarwal, J.C (1989), Essentials of Educational Psychology.Reprinted, NewDelhi : Vikhs publishing House Put Ltd

Bugleski,R.B (1971) The Psychology of Learning Applied to Teaching ,Newyork: The bobbis marril campany,inc

Bender, M.L. et al (eds).1976:.Amharic Language in Ethiopia. London: Oxford university

Cooper. R, (1976) The spreed of Amharic” in Bender etal Language in Ethiopia. Oxford university press.

Cronbach. (1954) Educational Psychology .NEW york :Mc. Grow Hill Book campany.inc

Gagne.R.M.(1976) The Condtion of Learning .New York: Holl,Rinehart and Winston.

Girma Awgichew. ((2009)The origin of Amharic, Addis Ababa French Center For Ethiopian studies. Pankhurst.Richard. H.P (1972) Education in Ethiopia During Italian Facist Occupation, The international journal of Afirca Historical studies

Spolsky ,B.(1969) , Attitudinal Aspects of Second Language Learning journal of Applied linguistic : Language Learning vol. 19.No 3.

Skinner.E.C (1985) Educational PPerguson Charles A. 2011. A Sociolinguistic survey of language and attitude in Ethiopia. Washington D.C. George Town universitysychology. 4ed,Prentic- Hall,inc

Tadele Adamu. (1990), Individual difference in Second Language Learning in Formal Context, Thesis submitted for the degree of PhD Departmente of linguistic Science.

Mehrens & Lehmann (1991) measurement and evaluation in education and psychology

(2nd ed.),Newyork,

# አባሪዎች

## አባሪ 1

### ጅማ ዩኒቨርስቲ

### ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

### የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

### የድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር

### በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

### የመጠይቁ ዓላማ

የዚህ መጠይቅ ዓላማ በቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድ የእናንተ የተማሪዎች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎቹን በትክክል አንብባችሁና ተረድታችሁ ትክክለኛ መልስ እንዲትሰጡኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ ጊዜያችሁን በመሰዋት ይህንን መጠይቅ በመሙላታችሁ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>

በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

**ክፍል አንድ**፡- በክፍት ቦታዎች ላይ ትክክለኛ መረጃ ሙላ/ዪ/

1. የት/ቤት ስም-----------------------------------------------------------

2. ክፍል-----------------------------------

3. ፆታ-------------------------------------

4. ዕድሜ-----------------------------------

5. የአፍ መፍቻ ቋንቋ-------------------

**ክፍል ሁለት**፡- ለዕያንዳንዱ ጥያቄ በመመዘኛ መስፈርቱ ላይ በተቀመጡት መግለጫዎች አማካይነት ተገቢ ነው የሚትሉትን መልስ የ"X" ምልክት በማድረግ አመልክቱ

ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ለቀረቡ ጥያቄዎች

5 = በጣም እስማማለሁ፣

4 = እስማማለሁ፣

3 = መወሰን ያስቸግረኛል፣

2 = አልስማማም፣

1 = ፍፁም አልስማማም በማለት ጥያቄውን በተረዳችሁት ልክ መልስ ስጡ

| ተ/ቁ | የመመዘኛ ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለሚጀምርበትና ለሚያጠናቅቁበት ክፍል ደረጃ ያላቸው አስተያየት** | | | | | |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ መሰጠቱና በ10ኛ ክፍል ላይ ማብቃቱ በቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ ምንም ዓይነት ጫና አላሳደረብኝም ፡፡ | | | | | |
| 2 | የአማርኛ ትምህርት ክፍለጊዜን እጅግ በጉጉት እጠብቃለሁ፡፡ | | | | | |
| 3 | በአማርኛ ትምህርት ክ/ጊዜ ላይ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች የበለጠ እሳተፋለሁ | | | | | |
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ትኩረት ሰጥቼ ስለምከታተል ያስመዘገብኩት ውጤት አርኪ ነው፡፡ | | | | | |
| 5 | የአማርኛ ትምህርት ክ/ጊዜ ካመለጠኝ እንደሚጎዳኝ ስለማውቅ እጠነቀቃለሁ፡፡ | | | | | |
| 6 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ገፍቼ ደራሲ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ | | | | | |
| 7 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ ውስጣዊ ስሜት አለኝ፡፡ | | | | | |
| | **ተማሪዎች በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ያላቸው አመለካከት** | | | | | |
| 8 | አፍ የፈታሁበት የዳውሮኛ ቋንቋ አነጋገር ስልት/ንበት/ በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ ምንም ተጽእኖ አላሳደረብኝም፡፡ | | | | | |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ የአነጋገር ስልት/Pronounciation// ቢያስቸግረኝም የአማርኛ ቋንቋ ጽሑፎችን ሳነብና ስናገር ምንም አልሸማቀቅም፡፡ | | | | | |
| | **ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ያላቸው አመለካከት** | | | | | |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አቀራረብ በጣም ምቹና በሚገባን መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡ | | | | | |
| | **ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ያላቸው አመለካከት** | | | | | |
| 11 | የአማርኛ ቋንቋ መ/ራን የትምህርት አቀራረብ በጣም የሚያነቃቃ ነው፡፡ | | | | | |
| 12 | መ/ራን ተማሪዎች በላጎታቸው መሠረት ተደስተው እንዲማሩ ይመክራሉ፡፡ | | | | | |
| 13 | መ/ራን ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲወዱ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ | | | | | |
| 14 | መ/ራን ተማሪዎች ያልገባቸውን ትምህርት እንዲጠይቁ ዕድል ይሰጣሉ፡፡ | | | | | |
| 15 | መ/ራን ተማሪዎችን ለማብቃት በአማርኛ ቋንቋላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ | | | | | |

## አባሪ 2

### ጅማ ዩኒቨርስቲ

### የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

### የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

### ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

**በቶጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ የቀረበ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና**

**I መመሪያ አንድ ፡- ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1-20 ድረስ ለቀረቡ ለተለያዩ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘ ሆሄ በመምረጣ መልሱ**

1.ቋንቋ ስርዓታዊ ነው ስንል ------------------ማለታችን ነው፡፡

ሀ/ መዋቅራዊ ለ/ ፍቺያዊ ሐ/ ዘፈቀደ መ/ሀ እና ለ መልስ ናቸው

2..የቋንቋ መሰረቱ------ነው፡፡ ሀ/ድምፅ ለ/ ቃል ሐ/ ሀረግ መ/ ዐ.ነገር

3.ጠንክሮ መማር------ ተግቶ መሥራት ሰውን ያስከብራል፡፡ ለባዶ ቦታ የሚስማማው

አያያዥ ቃል ሀ/ስለዚህ ለ/በመሆኑም ሐ/ ና መ/ከዚህ

4.ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ ሁለት ትርጉም የሚሰጡ ቃላት------

ሀ/አለ ለ/ዋና ሐ/ ገና መ/ሁሉም

5.አላፊ ጊዜን የሚያመለክተው ዐረፍተ ነገር የትኛው ነው?

ሀ/ ብርቱካን እንጨት እየፈለጠች ነው፡፡ ሐ/ ይሻሙ ነገ ወደ ሸዋ ትሄዳለች፡፡

ለ/ ህመምተኛው ወተት ይጠጣል፡፡ መ/ በጦርነት ብዙ ንብረት ወድሟል፡፡

6.ብዙ <u>ታዳሚዎች</u> በሠርጉ ተገኝተዋል፡፡ ለተሠረበት ቃል ትርጉሙ -------------------ነው፡፡

ሀ/ተጋባገሮች ለ/ እንግዶች ሐ/ መንገደኞች መ/ ሀ እና ለ መልስ ናቸው

7. /አክስቷን ለመጠየቅ ወደ መቀሌ ሄዳለች/ የሐረጉ መሪ ቃል ----------

ሀ/ አክስቷን ለ/ ለመጠየቅ ሐ/ ወደ መ/ ሄዳለች

8. /እንደ ወንድሟ ጎበዝ/ የዚህ ሐረግ ዓይነት -------------------ነው፡፡

ሀ/ ቅጽላዊ ለ/ ስማዊ ሐ/ ግሳዊ መ/ መስተዋድዳዊ

9. ግጥም ምን ዓይነት ግጥም እንደሆነ የሚታወቀው በ-------------- ተለክቶ ነው፡፡

ሀ/ ስንኝ ለ/ ቀለም ሐ/ ሐረግ መ/ አንጓ/አርኬ

10. የሰንጎ መገን ግጥም በየሐረጉ ስንት ቀለማትን ይይዛል?

ሀ/ሶስት ለ/ አራት ሐ/ አምስት መ/ ስድስት

11. ቀጥለው ከቀረቡት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ተራ ዐረፍተ ነገር የትኛው ነው?

ሀ/ ታፈሰ ሳር አጨደ፡፡ ሐ/ ልጁ ምሳውን እንደ በላ ወደ ት/ቤት ሄዷል፡፡

ለ/ አልማዝ ከት/ቤት እንደገባች ወደ ገበያ ትሄዳለችመ/ለማ ከአርሲ እንደገባ ድሬሄደ፡፡

12. በአንቀጽ ውስጥ ኃይለቃል ----------- ነው፡፡

ሀ/የአንቀጹ ማዕከላዊ ሀሳብ የያዘ ሐ/የአንቀጹ መንደርደሪያ ዐረፍ ነገር

ለ/ የአንቀጹ መሪ ዐረፍተ ነገር መ/ ሁሉም

13. በላይነሽ የብርቱካን ጭማቂ አዘውትራ ትጠጣለች፡፡የዚህ ዐረፍተ ነገር ዓይነት----ነው፡፡

ሀ/ ሐተታዊ ለ/ ትዕዛዛዊ ሐ/ ጥያቄዊ መ/ አጋኖኣዊ

14. ከልቦለድ አላባውያን ውስጥ ታሪኩ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ የሚገለፀው በ-------ነው፡፡

ሀ/ገፀባህርይ ለ/ መቼት ሐ/ ትልም መ/ ግጭት

15. አንድን ድርሰት ስንጽፍ በውስጡ ከሌላ ሰው የፈለቀውን ሃሳብ የተጠቀምን መሆኑን ለማመልከት የምንገለገለው ሥርዓተ ነጥብ ------------- ነው፡፡

ሀ/ ትዕምርተ ጥቅስ ለ/ አራት ነጥብ ሐ/ ትዕምርተ ሥላቅ መ/ቃለ አጋኖ

16. የቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ስንል ---- ማለታችን ነው፡፡

ሀ/ ቀጥተኛ ፍቺ ለ/ የመዝገበ ቃላት ፍቺ ሐ/ ምስጢራዊ ፍቺ መ/ ሁሉም

17. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን በማዳመጥ መረጃ ማግኘት እንችላለን፡፡

ሀ/ ዜና ለ/ ትምህርታዊ ገለፃ ሐ/ ንግግር መ/ሁሉም

18 .ከሚከተሉት ውስጥ የከንፈር ድምፅ የትኛው ነው ፡፡ ሀ/መ ለ/ ቀ ሐ/ ደ መ/ ከ

19. እሮሮ ማለት--- ማለት ነው፡፡ ሀ/ብሶት ጫወታ ሐ/ ትከዜ መ/ ውይይት

20. እንደተናካሽ ውሻ እየተቅለበለበ የተናገረው ንግግር አጥንት ይሰብራል፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ በተነፃፃሪ ዘይቤነት የገባው ሐረግ------------ የሚለው ነው፡፡

ሀ/እየተቅለበለበ የተናገረው ሐ/ እንደተናካሽ ውሻ

ለ/ አጥንት ሰብራል መ/የተናገረው ንግግር

**II መመሪያ ሁለት፡- ቀጥለው ለቀረቡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

21. ድመት መንኩሳ ----------- ሀ/ ትሄዳለች አጎንብሳ ሐ/ አመሏን አትርሳ

ለ/ ስትፀልይ አልቅሳ መ/ ለነፍሷ ትሳሳ

22. ፈረሰኛ የወሰደውን----አይመልሰውም፡፡ ሀ/ጦረኛ ለ/እግረኛ ሐ/መንገደኛ መ/ ነገረኛ

23. አህያን ፈርቶ--------ይመታል፡፡ ሀ/መጫኛውን ለ/ዳውላውን ሐ/ኮርቻውንመ/አፍንጫውን

24. አለባብሰው ቢያርሱ ----------

ሀ/ እህልን ያፍሱ ለ/ በአረም ይመለሱ ሐ/ እንደ ጎመን ይጎርሱ መ/ ይተርፋል ለከርሱ

25.ሲሮጡ የታጠቁት ---------ይፈታል፡፡ ሀ/ ሲያርፉ ለ/ ሲደርሱ ሐ/ ሲሮጡ መ/ሲተኙ

**III መመሪያ ሶስት፡- በትርጉም የማይገናኘውን ቃል የያዘ ሆሄ በመምረጥ መልሱ**

26. ሀ/ውበት ለ/ ደም ግባት ሐ/ ቁንጅና መ/ እርድና

27. ሀ/ ውህደት ለ/ ጥምረት ሐ/ ህብረት መ/ ውጥረት

28. ሀ/ ጉልምስና ለ/ እርግና ሐ/ ሽምግልና መ/ እርጅና

29. ሀ/ጅል ለ/ ቂል ሐ/ ሞኝ መ/ልል

30. ሀ/ ከነዳ ለ/ ለካ ሐ/ መተረ መ/ ከተረ

**IV ቀጥሎ ለቀረቡ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ትክክለኛውን ፍቺ የያዘ ሆሄ በመምረጥ መልሱ**

31..ሀሞቱ ፈሰሰ ሀ/ሰነፈ ለ/ሀሞቱ ተደፋበት ሐ/ ወኔው ተቀሰቀሰ መ/ጀግንነት ተሰማው

32. ሐረግ መዘዘ ሀ/ ሐረግ ቆረጠ ለ/ ሐረግ ጠቀለለ ሐ/ ዘር ቆጠረ መ/ ሐረግ ሳበ

33. ሆደባሻ ሀ/አኩራፊ ለ/ በቶሎ የሚቀየም ሐ/ቦርጫም መ/ ሀ እና ለ

34. መቀስ አፍ ሀ/ምላሱ መቀስ የሆነ ለ/ ነገረኛ ሐ/ ምላሱ ፀጉር የሚቆርጥ መ/አኩራፊ

35. ባፍንጫዬ ይውጣ ሀ/ይቅርብኝ ለ/ አልፈልግም አንገሽግሾኛል መ/ሁሉም

**V መመሪያ አምስት ከተራ ቁጥር 35-40 ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ የሆነውን ቃል የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡**

36. ዕድገት ሀ/ለውጥ ለ/ልማት ሥልጣኔ መ/ድቀት

37. ባላንጣ ሀ/ባላጋራ ለ/ደመኛ ሐ/ ጠላት መ/ ወዳጅ

38. መፈንደቅ ሀ/ መፍነክነክ ለ/ መሞላቀቅ ሐ/ መፍለቅለቅ መ/መተከዝ

39. ጦሰኛ ሀ/ ነገረኛ ለ/ ትዕቢተኛ ሐ/ ጠንቀኛ መ/ ቀልደኛ

40. ደግ ሀ/ ርህሩህ ለ/ የዋህ ሐ/ ገር መ/ክፉ

## አባሪ 3

**Correlations**

| | | attitude | Score |
|---|---|---|---|
| Attitude | Pearson Correlation | 1 | .955** |
| | Sig. (2-tailed) | | .000 |
| | N | 100 | 100 |
| Score | Pearson Correlation | .955** | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | |
| | N | 100 | 100 |

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

**Descriptive Statistics**

| | N | Minimum | Maximum | Mean | Std. Deviation |
|---|---|---|---|---|---|
| Attitude | 100 | .45 | 3.15 | 1.6632 | .56040 |
| Score | 100 | 10.00 | 75.00 | 38.4750 | 13.76157 |
| Valid N (listwise) | 100 | | | | |

**Correlations**

| | | sex | Age | attitude | Score |
|---|---|---|---|---|---|
| Sex | Pearson Correlation | 1 | .105 | .077 | .086 |
| | Sig. (2-tailed) | | .300 | .445 | .393 |
| | N | 100 | 100 | 100 | 100 |
| Age | Pearson Correlation | .105 | 1 | .088 | .096 |
| | Sig. (2-tailed) | .300 | | .383 | .344 |
| | N | 100 | 100 | 100 | 100 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| Attitude | Pearson Correlation | .077 | .088 | 1 | .955** |
| | Sig. (2-tailed) | .445 | .383 | | .000 |
| | N | 100 | 100 | 100 | 100 |
| Score | Pearson Correlation | .086 | .096 | .955** | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .393 | .344 | .000 | |
| | N | 100 | 100 | 100 | 100 |

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

## አባሪ 4

**Reliability Statistics**

| Cronbach's Alpha | Cronbach's Alpha Based on Standardized Items | N of Items |
|---|---|---|
| .746 | .752 | 15 |

**Item-Total Statistics**

| | Scale Mean if Item Deleted | Scale Variance if Item Deleted | Corrected Item-Total Correlation | Cronbach's Alpha if Item Deleted |
|---|---|---|---|---|
| Q1 | 42.6500 | 66.472 | .318 | .652 |
| Q2 | 42.6000 | 64.970 | .366 | .646 |
| Q3 | 42.5700 | 68.106 | .187 | .670 |
| Q4 | 42.5900 | 66.507 | .256 | .660 |
| Q5 | 42.5800 | 65.579 | .357 | .647 |
| Q6 | 42.2500 | 65.745 | .350 | .648 |
| Q7 | 42.5600 | 63.946 | .452 | .635 |
| Q8 | 42.7300 | 64.603 | .466 | .636 |
| Q9 | 42.6200 | 63.046 | .507 | .629 |
| Q10 | 42.5500 | 64.008 | .425 | .638 |
| Q11 | 41.9700 | 70.757 | .105 | .678 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Q12 | 42.2400 | 64.811 | .328 | .650 |
| Q13 | 42.4000 | 71.434 | .038 | .691 |
| Q14 | 42.4300 | 69.237 | .092 | .688 |
| Q15 | 42.4000 | 67.778 | .173 | .673 |

**Scale Statistics**

| Mean | Variance | Std. Deviation | N of Items |
|---|---|---|---|
| 45.5100 | 74.555 | 8.63455 | 15 |

# አባሪ 5

## የእያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ አመለካከት ውጤትና የፈተና ውጤት

| ተ/ቁ | የአመለካከት ውጤት | የፈተና ውጤት | ተ/ቁ | የአመለካከት ውጤት | የፈተና ውጤት | ተ/ቁ | የአመለካከት ውጤት | የፈተና ውጤት | ተ/ቁ | የአመለካከት ውጤት | የፈተና ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **1** | 0.85 | 25 | **26** | 1.56 | 37.5 | **51** | 2.43 | 55 | **76** | 2.16 | 47.5 |
| **2** | 2.24 | 45 | **27** | 1.13 | 27.5 | **52** | 2.14 | 50 | **77** | 1.16 | 25 |
| **3** | 1.20 | 27.5 | **28** | 3.06 | 72.5 | **53** | 1.06 | 27.5 | **78** | 1.44 | 35 |
| **4** | 1.79 | 40 | **29** | 2.24 | 50 | **54** | 2.06 | 42.5 | **79** | 2.01 | 55 |
| **5** | 1.38 | 27.5 | **30** | 1.77 | 47.5 | **55** | 1.16 | 22.5 | **80** | 1.55 | 35 |
| **6** | 1.04 | 20 | **31** | 2.20 | 47.5 | **56** | 2.34 | 60 | **81** | 1.49 | 40 |
| **7** | 1.09 | 20 | **32** | 1.32 | 30 | **57** | 2.41 | 55 | **82** | 1.37 | 30 |
| **8** | 1.03 | 30 | **33** | 2.25 | 55 | **58** | 1.42 | 35 | **83** | 2.37 | 60 |
| **9** | 0.88 | 25 | **34** | 1.92 | 40 | **59** | 2.40 | 57.5 | **84** | 2.09 | 47.5 |
| **10** | 1.44 | 30 | **35** | 1.98 | 55 | **60** | 1.69 | 37.5 | **85** | 1.04 | 27.5 |
| **11** | 1.25 | 22.5 | **36** | 3.15 | 70 | **61** | 2.27 | 40 | **86** | 0.91 | 20 |
| **12** | 1.71 | 37.5 | **37** | 3.08 | 75 | **62** | 2.50 | 60 | **87** | 2.07 | 45 |
| **13** | 0.93 | 22.5 | **38** | 2.45 | 62.5 | **63** | 1.67 | 40 | **88** | 1.57 | 32.5 |
| **14** | 1.14 | 27.5 | **39** | 1.83 | 47.5 | **64** | 1.50 | 40 | **89** | 0.45 | 10 |
| **15** | 1.32 | 30 | **40** | 1.62 | 40 | **65** | 1.58 | 32.5 | **90** | 1.12 | 30 |
| **16** | 1.33 | 27.5 | **41** | 2.29 | 47.5 | **66** | 1.99 | 45 | **91** | 1.54 | 45 |
| **17** | 1.17 | 22.5 | **42** | 2.30 | 52.5 | **67** | 1.70 | 35 | **92** | 2.77 | 67.5 |
| **18** | 1.33 | 35 | **43** | 2.23 | 52.5 | **68** | 1.72 | 40 | **93** | 0.69 | 15 |
| **19** | 2.16 | 52.5 | **44** | 1.42 | 30 | **69** | 2.04 | 45 | **94** | 1.04 | 22.5 |
| **20** | 2.27 | 52.5 | **45** | 1.68 | 32.5 | **70** | 0.84 | 15 | **95** | 1.12 | 25 |
| **21** | 2.04 | 45 | **46** | 1.26 | 30 | **71** | 1.90 | 50 | **96** | 1.60 | 42.5 |
| **22** | 1.25 | 27.5 | **47** | 1.68 | 32.5 | **72** | 1.20 | 27.5 | **97** | 1.28 | 27.5 |
| **23** | 1.26 | 25 | **48** | 1.48 | 35 | **73** | 1.46 | 32.5 | **98** | 1.34 | 37.5 |
| **24** | 1.38 | 27.5 | **49** | 1.10 | 22.5 | **74** | 2.39 | 57.5 | **99** | 0.92 | 30 |
| **25** | 1.62 | 32.5 | **50** | 0.95 | 20 | **75** | 2.03 | 45 | **100** | 2.31 | 57.5 |